

የዶክተር ዐብይ
“ካሪዝማ”

“የኦሮሞ ምሁራን የግዕዝ ፊደላትን እንዲጠቀሙ ጥሪ አቀርባለሁ”
ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው



እስክንድር ነጋ እንዴት ሄደ፤ ለምን ተመለሠ?


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 5 ሚያዚያ 2010 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


በተለይ ለግዮን ብቻ



# “ህወሓት አሠረን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈታን”

- “ዋልድባ ገዳም 40 አመት የዘለቀው የታጋዮች ቂም በቀል”
- “ራቁታችንን በሰው ፊት ያለ ርህራሄ ተገርፈናል”
- “ለእምነታችን ለቤተክርስቲያን ክብር ስንል ተዋርደናል ተሰቃይተናል”

አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት

ቅጽ 1 ቁጥር 5 ቅዳሜ ሚያዝያ 20 2010 ዓ.ም



ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ግንቦት 4
ይጠብቁን!




ቁጥር 4 ዕትም


17 **"ህወሐት አሰረን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈታን"**
*አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት*

7 **ዶክተር አብይ "ካሪዝማ"**

8 **የፍርሐት እና ተስፋ ድባብ ከጦላይ እስከ ጣውላ ቤት**

10 **ኢትዮጵያዊነት በማበብ እና በንቅለ - ተከላ መካከል**

12 **ሚያዝያ ወር በታሪክ ውስጥ**

13 **አስከሬን አጃቢው እና ሹም አጃቢው**

14 **የአዲስ አበባ መንግሥት ከተማዋን ያውቃታልን?**

22 **የታምራት ደስታ ያልተሠሙ ዕዉነታዎች**





3 **እስክንድር ነጋ እንዴት ሄደ፤ ለምን ተመለሠ?**

20 **‹የአንዲት፣ ገናና› ኢትዮጵያ ራዕይ እና የአጤ ቴዎድሮስ ፍጻሜ**

24 **ይድረስ ለፌስቡክ ጸሐፊያን ወገኖቼ**

28 **"15 ዓመት እንደሚፈረድብኝ ከዳኞች በፊት ደሕንነቶች ነግረውኛል"**




አቶ ኦልባና ሌሊሳ


30 **"የኦሮሞ ምትራን የግዕዝ ፊደላትን እንዲጠቀሙ ጥሪ አቀርባለሁ"**
ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው

32 **አንዱ ለሁሉም ሁሉም ለአንዱ**

# አንዷለም አራጌ መኪና ተሸለመ



በኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለውና ለመብታቸው "ዕምቢ" የሚሉ በርካታ ወጣቶች እንዲፈጠሩ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተው አቶ አንዷለም አራጌ ላደረገው ሠላማዊ ትግል የመኪና ሽልማት ተበርክቶለታል::

በአሸባሪነት ተከሶ ለሠባት ዓመታት ያህል በእስር ላይ የቆየውና በቅርቡ የሕዝብ ጥያቄና ግፊትን ተከትሎ ኢህአዴግ ሲፈታው የተገደደው የቀድሞው የአንድነት ፓርቲ አመራር አቶ አንዷለም አራጌ "ለሕዝብና ለሀገር ለውጥና ዕድገት ላደረከው ትግል እናመሠግናለን" በሚል 450ሽህ ብር ዋጋ የሚወጣ ዘመናዊ ያሪስ መኪና ከቀድሞ የትግል አጋሮቹና አድናቂዎቹ ተሸልሟል::

ለዓመታት በገዥው ፓርቲ የሚፈፀምበትን የሰብዐዊ መብት ጥሰትና ተዛማጅ ጉዳዮች ተቋቁሞ ለህዝብና ለሚወዳት ሀገሩ ነጻነትና ፍትህ ሲል ከባድ መስዋዕትነት እንደከፈለ ብዙዎች ይናገሩለታል::

በእስር ላይ እያለ በተለያየ መንገድ ከደረሰበት ድብደባና ስቃይ ባሻገር የመግደል ሙከራ ደርሶበት እንደነበር የሚናገረው አንዷለም "ዛሬ በሕይወት ተርፌ በሕዝብ ፊት ቆሜ ለመናገር የበቃሁት ቸርነቱና ተዐምሩ በማያልቀው እግዚአብሔር ፍቃድ ነው" ሲል ገልፆ ነበር::

የፕሮግራሙ አዘጋጆች ከአንዷለም በተጨማሪ ለአበበ ቀስቶ እናት የሀገር ባህል ልብስ፤ ለናትናኤል መኮንን ባለቤት የአንገት ሐብል በስጦታ ሲያበረክቱ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ በዕለቱ ለተገኙ ታዳሚያን በሙሉ የአንገት ስካርፕ ሸልሟል::

# ደራሲ ይስማዕከ ወርቁ የወገኖቹን ድጋፍ ይሻል

"ዴርቶጋዳ" በተሰኘው መጽሐፉ ሺዎች የሚያውቁት ወጣቱ ደራሲ ይስማዕከ ወርቁ የደረሠበት የመኪና አደጋ መናገር እንዳይችል አድርጎታል። ነገሮችንም ወደ ኋላ መለስ ብሎ ብዙ ለማስታወስ ተቸግሯል።

በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ሽያጭ ታሪክ ሪከርድ ሆኖ የተመዘገበው ዴርቶጋዳ የተሰኘው መጽሐፉ ከ200 ሺህ ኮፒ በላይ የተሸጠለት ይስማዕከ ወርቁ ከስምንት ወር በፊት ሐዋሳ አካባቢ የመኪና አደጋ በደረሰበት ወቅት ጭንቅላቱ ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶበት ሕክምናውን በወቅቱ ቢከታተልም ለወጥ ሳያሳይ ቆይቶ ቀስበቀስ የማስታወስና የመናገር ችግሩ እየተባባሰበት ይገኛል።

የ31 ዓመቱ ወጣት ደራሲ እስካሁን ድረስ አስራ ሶስት ያህል መጽሐፍቶችን ጽፎ ለአንባብያን አበርክቷል። ሁሉም ሥራዎች እጅግ የተወደዱለት ይስማዕከ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነው። ጭንቅላቱ ከፍተኛ ጉዳት ስለደረሰበት መናገር የማይችለው



ደራሲ ይስማዕከ በአስቸኳይ ለተሻለ ህክምና ውጪ ሀገር መሄድ እንዳለበት ታውቋል። በዚህም መሠረት ወጣቱን ደራሲ ለመታደግ የምትፈልጉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 1000243275408 የሂሳብ ቁጥርን መጠቀም ትችላላችሁ።

# ኢትዮጵያ በጋዜጠኞች መብት አያያዝ 150ኛ ደረጃን ያዘች

ድንበር የለሹ የጋዜጠኞች ድርጅት ባወጣው መግለጫ የፕሬስ ነፃነት ከማይከበርባቸውና ጋዜጠኞች ከሚንገላቱባቸው 180 ሀገራት መሀል ኢትዮጵያን በ150ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል።

ተቋሙ የጋዜጠኞችን የመገናኛ ዘዴዎችን መብት በተመለከተ ባወጣው ዝርዝር መግለጫ ሰሜን ኮሪያ የመጨረሻውን 180ኛ ደረጃ ስትይዝ ኤርትራ 179ኛ ሆና ትከተላለች።

ዓለም ዓቀፉ ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች ድርጅት በእነዚህ ሀገራት ውስጥ ያሉ አምባገነን መሪዎችና ባለሥልጣናት ጋዜጠኞችን ይገድላሉ ያስራሉ ያሰቃያሉ ከሀገራቸው እንዲሰደዱ ያደርጋሉ ይሄ ደግሞ ከሰብዐዊነት የወጣ ሊቆም የሚገባው ድርጊት ነው ብሏል።

ድርጅቱ ሠሞኑን ባወጣው መግለጫ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ለጋዜጠኞች ምቹ ሀገር በመሆን በመሪነት ያለችው ኖርዌይ ስትሆን ስዊድን፣ ኔዘርላንድና ፊንላንድ ተከታዩን ደረጃ ይዘዋል። አሜሪካ አምና ከነበረበችበት 43ኛ ደረጃ በማሽቆልቆል 45ኛ ሆናለች። ለዚህም ምክንያቱ ዶናልድ ትራምፕ "ጋዜጠኞች የሕዝብ ጠላት ናቸው" በማለት በተደጋጋሚ በአደባባይ መወረፋቸው እንደሆነ ተጠቁማል።

# በኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል ህዝባዊ ተቃውሞው አልበረደም

በሶማሊ ክልል የአስተዳደር ብሉሽነት ሙስና ተንሰራፍቷል በሚል የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ ከጀመረ ቀናት አስቆጥሯል:: ህዝባዊ ተቃውሞው ያተኮረው የክልሉ አስተዳዳሪ አቶ አብዲ ዐሊ ላይ ሲሆን ሥልጣናቸውን ለህዝባዊ መሪ እንዲያስረክቡ ተጠይቀዋል::

ካለፈው ሳምንት አርብ አንስቶ ኤረር፣ ቪኒሌ፣ አዲጋላ፣ መልካጀልዱ እና እና አብዛኛው ኢሳዎች በሚገኙበት እየተስፋፋ የመጣው ህዝባዊ ተቃውሞ "ፍፁም ግልጽ በሆነ ሁኔታ የክልሉ ፕሬዝዳንት አቶ አብዲ ዓሌ በሁሉም አካባቢዎች ላይ የራሳቸውን ሰው በማስቀመጥ ከተሞች በአካባቢው ተወላጅ እንዳይተዳደሩና ህዝቡም በቂ ፍትህ እንዳያገኝ አድርገዋል" ማለታቸውን ዶቼቨሌ ዘግቧል::

የጀርመን ራዲዮ አማርኛው ክፍል ያነጋገራቸው የተቃውሞ ድምጽ ያነሱት ዜጎች እንደሚሉት "በየወሩ በአማካይ 12% ያህል ከደመወዛችን ላይ ያለምንም ፍቃድ ገንዘባችን ይቆረጣል የፔሮል አሠራራቸውም ሕገወጥ ነው ያለ አገባብ በሚሰበሥቡት በድሃ ገንዘብ ባለሥልጣናት ልጆቻቸውን ወደ ውጭ ልከው ያስተምራሉ፤ ቪላቤትና መኪና ይገዛሉ ሠርግና ሕክምናቸውን የፈለጉት ሀገር በመሄድ ያከናውናሉ በማለት" ተናግረዋል

# እስክንድር ነጋ እንዴት ሄደ፤ ለምን ተመለሠ?

ላለፉት 25 ዓመታት በነጻው ፕሬስ ዘርፍ ከፍተኛ ሥራ የሠራውና ለሙያው ክብር ተቆጥሮ የማያልቅ መስዋዕትነትን የከፈለው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ዓለም ዓቀፉ የሠብዐዊ መብት ደርጅት አምንስቲ ኢንተርናሽናል 50ኛ ዓመት ክብረ በዐሉን ሲያከብር የፕሮግራሙ የክብር እንግዳ ሆኖ ተገኝቷል::

ላለፉት ስድስት ዓመታት ተኩል በእሥር ላይ የነበረው ጋዜጠኛ በሚጽፋቸው ጽሑፎች የተነሳ ከስምንት ጊዜ በላይ ታሥሯል፤ ተገልብጦ ተገርፏል:: ብዙ ቀናትን በጨለማ ቤት እንዲያሳልፍ ተገዷል:: ለዘመናት በዓላማው ጸንቶ ሠላማዊ ትግሉን ያጠናከረው ይህ ጽኑ ጋዜጠኛ በክብር የተጋበዘበት ሆላንድ ሲደርስ የአምኒስቲ ኢንተርናሽናል መሪዎች፣ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ዓለም ዓቀፍ የሚዲያ ተቋማት አቀባበል አድርገውለታል::

የሠብዐዊ መብት ጥሠትን በእጅጉ የሚኮንነው አምንስቲ ኢንተርናሽናል ሀምሣኛ ዓመት ክብረ በዐሉን በድምቀት ነበር ያከበረው:: የሆላንዱ ንጉስን ጨምሮ ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ የነፃነት ታጋዮች፣ የሠብዐዊ መብት ድርጅቶች፣ ዓለምአቀፍ ሚዲያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል::

በዚህ ዓለምአቀፍ ደማቅ በዐል ላይ እንዲገኝ የተጋበዘው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋም እኚህን ታላቅ የሆላንድ ንጉስ በግል የማግኘት ዕድሉ ገጥሞታል:: እስክንድር በወቅቱ በሀገሪቱ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን የሠብዐዊ መብት ጥሠት አስመልክቶ ለንጉሱ ለመግለጽ ሞክሯል:: ለሌሎች የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናትም ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ጭቆና በቂ መረጃ አስተላልፏል::

የአምንስቲ ኢንተርናሽናል 50ኛ ዓመት ክብረ በዐል በሆላንድ ያማረ ገጽታ ይዞ መጠናቀቁ ተነግሮለታል:: በዚህ ልዩ ፕሮግራም ላይ በኢትዮጵያ ስላለው የሠብዐዊ መብት አያያዝ ገለፃ እንዲያደርግ በመድረኩ ላይ የተጋበዘው ጋዜጠኛና የሠብዐዊ መብት ተሟጋች እስክንድር ነጋ "ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ በእጅጉ አሳሳቢ ነው፤ ሰዎች የሠብዐዊ መብታቸው እየተጣሰ ነው፤ ብዙዎች ከሀገር እየሠተደዱ ነው ፤ፍትህ ይስፈን፤ ጭቆና ይወገድ፤ የሚሉ ደግሞ በየጊዜው እየታሠሩ እየተደበደቡና እየሞቱ ነው፡" በማለት ያለውን ችግርና የሥርዐቱን አምባገነንነት ለጉባዔው ታዳሚያን መግለጹን ከሆላንድ መልስ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ባደረገው ቆይታ ገልፆልናል::

"የኢትጵያውያን መብት በትክክል ሊከበር የሚችለው ዴሞክራሲ ሲሠፍን ብቻ ነው፤ ዴሞክራሲ ሳይኖር የሠብዐዊ መብትን ማስከበር አይቻልም" የሚለው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ 50ኛ ዓመቱን ያከበረው የአምኒስቲ ኢንተርናሽናልን ፕሬዝዳንትም ሆነ ሌሎችም ከፍተኛ አካላት በኢትጵያውያን ላይ የሚደርሠው ግፍና በደል እንዲቆም መንግስትን አጥብቀው ሊያሳስቡ እንደሚገባቸው ጠቁሟል:: በተለይም ይህንን በተመለከተ አምኒስቲ ወደፊትም ጠንክሮ መስራት እንደሚገባው የዓለም አቀፍ ድርጅቱን መሪ ባነጋገረበት ወቅት አሳስቧል::

ለኢትዮጵያዊያን መብትና ነፃነት ያለመታከት በብዕሩ ሲታገል የቆየው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ወደ ሆላንድ መሄዱን ተከትሎ በዚያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለክብሩ ደማቅ ዝግጅት በማድረግ ‹‹እንወድሀለን፣እናከብርሀለን›› ብለውታል:: ከዝግጅቱ በኋላ በኢትዮጵያውያኑ ግብዣ ላይ የታደመው እስክንድር ነጋ በሆላንድ



*እስክንድር ነጋ ከሆላንዱ ንጉስ እና ከአምንስቲ ፕሬዝዳንት*

የሚኖሩ ወገኖቹ ለሠጡት ክብር ልባዊ ምስጋና አቅርቧል::

"ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ የኔን መምጣት ተከትሎ ያዘጋጁት የግብዣ ፕሮግራም ፍጹም ያማረና የተዋጣለት ነበር:: ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍነው፤ በርግጥ እነሱም የሠላማዊ ትግሉ አባል ናቸው፤ እኛ ሀገር ቤት እነሱ ባህር ማዶ ቢሆኑም በሠላማዊ ትግሉ ላይ ከጎናችን በመቆም የበኩላቸውን አበርክተዋል" የሚለው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ "ኢትጵያውያን ያደረጉልኝ አቀባበል ትልቅ ዋጋ ያለው ነው፤ ግን አቀባበሉና ክብሩ ለኔ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው ትግል ነው:: ጭቆናን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት የታገሉ የሠላማዊ ትግል ጓደኞቼ እና ሠላማዊ ትግሉ ነው የተከበረው" ብሏል::

በሆላንድ ቆይታው ላገኛቸው የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና የሀገራት ተወካዮች ባለፉት 27 ዓመታት በኢህአዴግ አምባገነን አገዛዝ የደረሱትንና አሁንም እየተፈፀሙ ያሉትን የሠብዐዊ መብት ጥሠቶች በበቂ ሁኔታ የገለፀው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ኢትዮጵያ ዜጎች በፍትህ ፊት እኩል የሚታዩባት፣ ዴሞክራሲ የሠፈነባት፣ ሠው በሠውነቱ የሚከበርባትና የተሻለች ሀገር ሆኖ የማየት ፍላጎቱ ዕውን እስኪሆን ድረስ ሠላማዊ ትግሉን እንደሚቀጥልና የሚጠበቅበትን መስዋዕትነትም ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ገልጧል::

ቀደም ሲል በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን "እኔ የትም ብሄድ ተመልሼ እመጣለሁኝ፤ አልቀርም፤ ሠላማዊ ትግሌን ከዚህች ሀገር ርቄ ማድረግ አልፈልግም" በማለት ለህዝብ ቃል በገባው መሠረት ከቀናት የሆላንድ ቆይታው በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሷል::

በኢትዮጵያ ያለው የሠብዐዊ መብት ጥሠት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሠ መምጣቱ ያሳሠባቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሠብዐዊ መብቶች ኮሚሽነር ዘይድ ረኢድ አል ሁሴን አዲስ አበባ ተገኝተው በቅርቡ ከእሥር የተፈቱ ፖለቲከኞች፤ ጋዜጠኞች፣ የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትንና መነኮሳቱን በሠብዐዊ መብት ጥሠት ዙሪያ ሲያነጋግሩ የዚህ ፕሮግራም አባል የነበረው እስክንድር ተመሣሣይ በሆነ መልኩ አምባገነንነት በሥርዓቱ በኩል እስካልቀረ ድረስ ዜጎች ወደ ፊትም አስከፊ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል ያለውን ሥጋት ለኮሚሽነሩ ገልጿል::

ባለፈው ሣምንት ሐሙስ ሌሊት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በተደረገለት ግብዣ መሠረት ወደ ሆላንድ ለመሄድ አስፈላጊውን ፎርማሊትና ፍተሻውን ካለፈ በኋላ ፓስፖርቱ ተነጥቆ ከጉዞው እንዲመለስ ተደርጎ ነበር:: እስክንድር በማግስቱ ተጠርቶ ፓስፖርቱ የተመለሠበትን ሂደት ሲያስታውስ "ሐሙስ ሌሊት ወደ ሆላንድ ለመሄድ አየር መንገድ ስደርስ ፓስፖርቴን ቀምተው ወደ ቤትህ ተመለስ፤ ከሀገር መውጣት አትችልም፤ ሲመችህ ኢምግሬሽን ዋናው መስሪያ ቤት ቢሮ ቁጥር ዘጠኝ ሄደህ መጠየቅ ትችላለህ አሉኝ:: አይ ይሄ ነገር መንግስት ላይ ብዙ ችግር ያመጣበታል፤ እባካችሁ አጣርታችሁና አለቆቻችሁን ጠይቃችሁ መልስ ብትሠጡኝ ይሻላል እንጂ አደጋው ከባድ ነው የሚሆነው፤ ስላቸው ከበላይ የመጣ ትዕዛዝ ነው አሉኝ:: እርግጠኛ ናችሁ ከበላይ የመጣ ትዕዛዝ ነው? ብዬ ደጋግሜ ጠይቄአቸው የያዙኝ ሠዎች "ታዘን ነው" ስላሉ ምንም ማድረግ ስላልቻልኩ ከቦታው ተመልሻለሁ:: በሰአቱ በግማሽ ቀን ውስጥ በዓለም ዙሪያ የነበረውን ጫና እና መከልከሌ አግባብ አለመሆኑን የቀረበውን ግፊት ተከትሎ፤ አርብ ምሳ ሠዐት አካባቢ ከኢምግሬሽን ተደውሎልኝ፤ ‹‹ፓስፖርትህን መውሠድ ትችላለህ፣ ከሀገር መውጣትም ትችላለህ›› አሉኝ:: የመጀመሪያው ትኬት ስለተቃጠለ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል እንደገና ሁለተኛ ትኬት በፍጥነት ቆርጠው ላኩልኝ:: ሆላንድ አየርመንገድ እንደ ደረስኩ በቀጥታ ወደ ስብሠባው ነው የሄድኩት፤ ይህ ታላቅ በዐል ሊያመልጠኝ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነበር የቀሩት፤ቦሌ ኤርፖርት የተፈለገውም ከስብሰባው እንድቀር ነው" በማለት በአየር መንገድ የደረሠበትን እንግልት ለዝግጅት ክፍላችን ገልፆልናል::

# ለሚፈለገው የዜጎች ሰላም፣ ፍቅር፣ ዕድገትና ብልጽግና ቁርጠኝነት የግድ ነው !

ኢትዮጵያ በለውጥ ሂደት ላይ ነች ተብሏል:: ይሁን እንጂ ለወጡ የፖለቲካ እና የህሊና እሥረኞችን በመፍታት ረገድ ተጨባጭ የሆነ ምልክት ይበል በሚያሰኝ ሁኔታ እየተስተዋለበት ከመሆኑ ባሻገር፤ ዐበይት እና ወሳኝ ከሆኑ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች አንፃር ገና እጅግ ብዙ የሚጠበቅበት ነው:: ለምን? መሠረታዊ ናቸው የሚባሉትና ነባራዊነት ያላቸው፣ ወቅታዊ የሆኑትና ጊዜ ሊሰጣቸው የማይገባው አንኳር ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እንዳሉ ናቸውና:: ያም ሆኖ በቃል ደረጃ ሀገራዊ ችግሮች በጊዜ ሂደት ሊፈቱ እንደሚችሉ በኢዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር አንደበት መነገሩና በተደጋጋሚ መለፈፉ፣ ለሁሉም ብሔራዊ ችግሮች መፍትኄ ይገኝ ዘንድ በኢሕአዴግ ደረጃም ይሁን ‹‹ጠብመንጃ አንስተዋል›› እስከተባሉ ተቀናቃኝ የፖለቲካ አቋም አራማጆች ድረስ አሳታፊ የሆነ፣ ቀናናነትና ከሴረኝነት አመለካከት የፀዳ አመለካከት የሰፈነበት ሁሉአቀፍ የሆነ ትብብር እንደሚያስፈልገው መገለጹ፤በድቅድቅ ጨለማ የተዋጠ ሆኖ ይታይ ከነበረው ብሔራዊ አረንቋ ኢትዮጵያን ሊያወጣት የሚችል የተስፋ ቀንዲል መሆኑ አሌ አይባልም::

አሁን ከብዙ፣ አታካች፣ አወዛጋቢና ተሰናባቹ ጠቅላይ ሚኒስቴር ኃይለማርያም ደሳለኝ እንዳሉት ‹‹የቡድነኝነት›› አዝማሚያ ይስተዋልበት ከነበረው የኢሕአዴግ ድርጅታዊ ስብሰባ፣ የተሃድሶን አቅጣጫ የመከተልና ያለመከተል ንትርክ፣ አንገብጋቢ ዎቹን ሕዝባዊና ሀገራዊ ጥያቄዎች አጀንዳ አድርጎ ደርጅታዊ ጉባኤዎችን ከማካሄድ ቀጥሎ፤ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር እስከመሾም፣ ከጅጅጋ አምቦ እስከ መቀሌ ጎንደር፣ ከባሕር-ዳር ሃዋሳ እስከ ሀገሪቱ ማዕከል አዲስ አበባ ከሕዝብና ‹‹የሕዝቡ ወኪል ናቸው›› ከሚባሉ ወገኖች ጋር እስከመገናኘት፣ የንግዱን ማኅበረሰብ አባላትም በገጽ እስከማወያየት ደረጃ የዘለቀ ንቅናቄ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ አድርገዋል:: በየመድረኩም ለብሔራዊ ለውጥ እንደሚሠሩ፣ የሀገሪቱን ችግር ለመፍታት እሳቸውና መንግሥታቸው የበኩላቸውን ጥረት እንደሚያደርጉ፣ ፍቅርና ዕርቅ በምድሪቱ ይሰፍን ዘንድ መደረግ የሚገባው ነገር ሁሉ መደረግ እንደሚገባው ቃል ገብተዋል:: ‹‹የእኔ›› ያሉትንም ካቢኔ መሥርተዋል::

ምንም እንኳ ከካቢኔው ምሥረታና ከሹመቱ ሂደት አንፃር የተስተዋለው ‹‹አዲሱን የወይን ጠጅ በአረጀው መጥመቂያ›› እንዲሉ ዓይነት ገጽታ ያለው ቢሆንም፤ ከተገባው ቃል ብዛት አኳያ የተግባራዊነቱ ግዝፈት በግልጽ የሚታይ ነውና፤ ለሚፈለገው የዜጎች ሁሉ ሰላም፣ ፍቅር፣ ዕድገትና ብልጽግና የሚበጀውን የተግባር ጎዳና ለመተለም ቁርጠኝነት የግድ መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን:: በአንዳንድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት መድረክ እንደተጠቆመውም ቃል መግባት ቃልን የመከወን ያህል ቀላል ባለመሆኑ፤ በኢሕአዴግ ሠፈር ይስተዋላል የሚባለውን ‹‹የቡድነኝነት›› አዝማሚያ በአስተዋይነትና በብልሃት ጭምር ታግሎ በማሸነፍ ለሚጠበቀው እና ሀገራዊ ተቀባይነት ለሚኖረው ተግባር መዘጋጀት፤ ዛሬም፣ ነገም ይሁን ከነገ ወዲያ የኢትዮጵያችን መልካም ተስፋ እንዳሳለፍናቸው ዘመናት ሁሉ ‹‹ላም አለኝ በሰማይ...›› ሆኖ እንዳይቀር የሚረዳ ነው:: ስለዚህም ለተፈላጊው ሀገራዊ ለውጥ ተግባራዊነት፤ ከኢሕአዴግ አባልና አጋር ፓርቲዎችና ደጋፊዎች ጀምሮ፤ ተቀናቃኝ ከሚባሉት የፓለቲካ ኃይሎች፣ የተሻለውን ነገ ለሀገሪቱና ለዜጎቿ ከሚመኙ ለውጥ ፈላጊ ወገኖች፣ ብሎም ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዕግስትና አስተውሎት የተመላበት ትብብር የሚያስፈልግ መሆኑ ለውይይት መቅረብ የሚኖርበት አጀንዳ አይደለም::

በተረፈ በዚህ የመጽሔታችን ዕትም የተለያዩ ወቅታዊነት ያላቸውን ጉዳዮች አስተናብረናል:: ‹‹ያለ ጥፋታችን አሸባሪ ተብለን ለእሥርና ለዕንግልት ተዳርገን ነበር...›› የሚሉት የዋልድባ መነኮሳት፤የግዮን ልዩ ዕንግዶች ናቸው:: እነዚህ የኃይማኖት አባቶች በእሥር ላይ ባሉ ጊዜ ‹‹ተፈፀመብን›› ስላሉት በደል በዝርዝርና ልዩ በሆነ ስሜት ያጫወቱንን ለአንባቢያኖቻችን አቅርበነዋል:: እንደነሱም ሁሉ በፖለቲካዊ አቋሙ ዓመታትን በእሥር ያሳለፈው ወጣቱ ፖለቲከኛ አቶ ኦልባና ሌሊሣ የመጽሔታችን ሌላው ዕንግዳ ነው:: የአፄ ቴዎድሮስን 150ኛ ዓመት የልደት ቀን በተመለከተ እንደ ቁጥር 4 ዕትማችን ሁሉ በዚህም ዕትም፤ ልዩና ጠለቅ ባለ ሁኔታ የንጉሡን ዓላማና ተግባር የሚዳስስ ፅሑፍ ይዘናል:: በኪነ-ጥበብ ዐምዳችን የድምፃዊ ታምራት ደስታን ጉዳይ ተመልክተናል:: የኢትዮጵያ የግዕዝ ፊደል፤ የኦሮምኛን ቋንቋ ይበልጥ ለማበልፀግና በኢትዮጵያ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ሊያገለግል የሚችልበትን ዕድል በማስፋት ረገድ የሚረዳ ስለመሆኑ አንድ ምሁር ያቀረቡትን በሳይንስ የተደገፈ አማራጭ ሐሣብ በተመለከተም ግዮን ያቀረበችው ማዕድ አላት:: አምንስቲ ኢንተርናሽናል በሆላንድ አምስተርዳም ባዘጋጀው በዓል በክብር ዕንግድነት የተጠራው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ስለታደመበት ዓለም አቀፍ መድረክ የሚለውም ሲኖር፤ ሌሎች ወቅታዊነት ያላቸው ጉዳዮችም በመጽሔቷ ገጾች ላይ ሠፍረዋል:: አስተያየታችሁና አብሮነታችሁ አይለየን:: መልካም ንባብ!


ግዮን መጽሔት
ኢትዮ ሐበሻ ሕጎመትና
ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
በየ 15 ቀኑ ለኅትመት
የምትበቃ መጽሔት

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋና አዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

ክርኤቲቭ ዲዛይን
ሀብታሙ መኮንን

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

አታሚ
ቢኒያምና በቀለ የሕትመት አገልግሎት
አድራሻ
ክ/ከተማ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07
የቤት ቁጥር 363
ስልክ ቁጥር 0922446324

# ጠ/ሚ ዐብይ በጎንደርና ባሕር ዳር ምን ተጠየቁ ምን መለሱ



*ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሠሞኑን በጎንደርና በባህር ዳር በነበራቸው ህዝባዊ ውይይት ከነዋሪዎቹ የተነሱላቸውን ጥያቄዎችና የሰጡትን መልስ በጥቂቱ ለንባብ በሚመች መልኩ አዘጋጅተን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::*

### ብፁዕ አቡነ አብርሐም የተናገሩት በጥቂቱ

ክቡርነትዎን ግን አደራ የምለው፣ መናገር ቀላል ነው፤ ማድረግ ግን ከባድ ነው:: ማውራት ይቻላል፤ በአንድ ቀን ሀገርን መገንባት፣ ማልማት ይቻላል - በወሬ ደረጃ፤ መሥራት ግን ፈታኝ ነው:: ፈታኝ የሚያደርገው፣ ውስብስብ እየኾነ በተለያየ መልኩ የሚቀርበው ጣጣ ነው:: ስለዚህ ከተለያየ አቅጣጫ የሚቀርበው ውስብስብ ነገር፣ የተናሯቸውን ኢትዮጵያዊነትን፣ አንድነትን፣ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ የጋራነትን፤ ስለዚህ፣ ይህን ችግር ለመናድ፣ ይህን ችግር ለማስወገድ በተዋቡ ዐረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፏቸው ቃላት እንደው ዘወትር እንደ መስተዋት ልበል፣ እንደ ግል ማስታወሻ ከፊትዎ ሰቅለው፥ ምን ተናግሬ ነበረ፤ የቱን ሠራሁት፤ የትኛው ይቀረኛል የሚል የዘወትር ተግባር እንዲኖርዎ፣ በቤተ ክርስቲያን ስም በታላቅ ትሕትና እገልጽልዎታለሁ:: ምክንያቱም ይህን ዕድል ያገኘሁት ዛሬ ስለኾነ፣ ነገ ብቻዎን ስለማላገኝዎት አሁኑኑ ልናገር ብዬ ነው::

በሥልጣን ክፍፍልም ኾነ በአካባቢው ያሉ ሥልጣን ላይ ይቀመጣሉ፤የመንግሥት ሓላፊነታቸውን ትተው፣ የተሰጣቸውን አደራ ረስተውና ረግጠው፣ ራሳቸውን የሃይማኖት መሪ እያደረጉ ይህችን እናት አንጋፋ ቤተ ክርስቲያን በዋለችበት እንዳታድር፤ ባደረችበት እንዳትውል እንደ ጥንቱ እንደ ሮማውያን ዘመን እየኾነ ያለበትም ቦታ አለና እባክዎ ክቡርነትዎ በአስተዳደር ዘመንዎ፡- እኩልነት፣ ሰላም፣ አንድነት፣ መቻቻል ሰፍኖ፤ ይኼ በቃል፣ በቋንቋ የምንናገረው ሳይኾን ተግባራዊ በኾነ መልኩ አንተን አልይህ፣ አንተን አልይህ መባባል ቀርቶ እምነትም ከኾነ በትምህርት ላይ የተመሠረተ እንጅ በሰይፍና በጥቅምጥቅም፣ በዱላና በአባርርሃለሁ ባይነት ያልተመሠረተ፣ ሰላማዊ የኾነ ነገር እንዲሰፋ እንዲሰፍን አደራ እልዎታለሁ::

### ስለ ወልቃይት የማንነት ጉዳይ ዙሪያ አቶ አታላይ ዛፌ የተናገሩት

*ቀሪውን ዘገባ በ26 እና 27 ይመልከቱ*

# የዶክተር ዐብይ "ካሪዝማ"

"ካሪዝማ" Charisma የሚለው ቃል በአብዛኛው ተቀባይነት ያለው አመራር እና ተወዳጅ ሰብዕና ላላቸው የዓለማችን መሪዎች መገለጫ መሆን የጀመረው የጀርመን የማኅበረሠብ ጥናት ሊቅ የሆነው ማክስ ዌበር ለዚህ ቃል ዘመናዊ ፍቺ መሥጠቱን ተከትሎ ነው፡፡ ዌበር በ1921 እ.ኤ.አ ባሳተመው "ሕግ በኢኮኖሚና በኅብረተሠብ ውስጥ" በተባለ መጽሐፉ ካሪዝማን ከሥልጣን ጋር በማገናኘት ሲተነትነው "ካሪዝማቲክ ሥልጣንና ከልማድና ከህግ ከሚመነጩ ሥልጣኖች የተለየ ነው" ይለዋል፡፡ ዌበር በዚሁ መጽሐፍ ለካሪዝማ በሠጠው ዘመናዊ ትርጉም ካሪዝማቲክ መሪ የሚላቸውን መሪዎች እንዲህ ይገልጻቸዋል፡፡

"ካሪዝማቲክ መሪዎች ራዕይ አላቸው፡፡ ሰዎችን የሚያስተባብርና ለተግባር ማንቀሳቀስ የሚያሥችል ግልጽ መልዕክት የማሥተላለፍ የተለየ ችሎታ አላቸው፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ጆርጅ ዋሽንግተን፣ ፍራንክሊን ሩዝቬልት፣ ቢል ክሊንተን እና ስቲቭ ጆብስን አይነት ሰዎች ካሪዝማቲክ መሪዎች ተብለው መጠቀስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ እነዚህ መሪዎች በተሠማሩበት የሙያ መስክ የተካኑ ቢሆኑም ልዩ የሆነው ኃይላቸው የሚመነጨው በተጽዕኗቸው፣ በአማላይነታቸው እና ስኬታማነታቸውን አሣማኝ በማድረጋቸው ነው "

በሌላ በኩል ማክሚላን የተባለው መዝገበ ቃላት "ካሪዝማ" የሚለውን ቃል "ሰዎች እንዲወዷችሁ ወይም ወደናንተ እንዲቀርቡ የሚያደርግ ጠንካራ የግል ባህሪ" በማለት ይፈታዋል፡፡ ኢንሳይክሎፔዲያ ብሪታኒካ የተባለው ማጣቀሻ መጽሐፍ ካሪዝማ ማለት ከተለመደው የተለየ ሳቢነት ወይም የአመራር ችሎታ ላላቸው ሰዎች የተሠጠ አስደናቂ ኃይልና ዐቅም ነው ይለዋል፡፡ እንደዚህ ኣይነቶቹ መሪዎች በፖለቲካም ሆነ በሐይማኖት ሥርዓት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ቢሆኑም የቆየውን ልማዳዊ ሥርዓት ለበጎም ሆነ ለክፉ የሚቀይሩ ናቸው" ይላል፡፡

አማርኛ ቋንቋ በቀላል አቻ ትርጉም "ግርማ ሞገስ" ብሎ የሚፈታው ይህ "ካሪዝማ" የሚል ቃል በውስጡ የሚይዘው ሠፊ ትርጉም ህዝብ በመሪዎቹ ላይ ማየት የሚፈልገውን ዓይነት የተለየ ሰብዕና ይወክላል፡፡ በተለይም "ተከተል ንጉስህን ተመልከት ባንዲራህን" ማለትን ባህሉ ላደረገ ኢትዮጵያዊ ሊከተለው የሚችል በአስተሳሰቡና ሁሉን ዐቀፍ ዕውቀቱ ሰዎች ሊደነቁበት የሚችሉ፣ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ሥህተት የማይበዛበት፣ የሚናገረውን ቃል የሚያከብር እንዲሁም ለራሱ የመሪነት ሰብዕና የሚሰጠው ግምት ላቅ ያለ ፣ በሰዎች ተጽዕኖ ሥር በቀላሉ የማይወድቅና በተቃራኒው ብዙዎችን ከጎኑ ማሠለፍ የሚችል ባለ ግርማ ሞገስ መሪ እንዲኖረው ይመኛል፡፡

ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ በተለይም በንጉሳዊ ዘመን በህዝብ ዘንድ የተከበሩ ፣ የተወደዱ እና የተፈሩ ነገስታት መሪዎች ነበሩ፡፡ ከመጨረሻው ንጉስ አጼ ኃይለስላሴ በኂላ የሀገሪቱ የፖለቲካ ምኅዋር ሲቀየር እና ህዝብም "አከተመ የመኳንንት አገዛዝ" ሲል በመሪነት ወንበሩ ላይ የተቀመጡት ወታደራዊም ይሁኑ ሲቪል መሪዎች ከግላዊ



**አቶ ኃይለማርያም በራሳቸው ግላዊ ባህሪም ይሁን ሥልጣን ላይ በቆዩበት ወቅት በነበራቸው የወሳኝነት ሥልጣን አንጻር ሲታይ ሳቢ እና ሰው ሊከተላቸው የሚችል ኣይነት መሪ አልነበሩም**

ሰብዕናቸውና ከመሪነት ጸጋቸው አንጻር ሲመዘኑ በህዝብ ዘንድ የላቀ ተቀባይነት ያላገኙ በቀላል አነጋገር "ዓይንና ልብ ያልገቡ" ሆነው አልፈዋል፡፡

ምንም እንኳን ካሪዝማ ለክፉም ይሁን ለደግ ዓላማ መዋል የሚችል ተሰጥዖ መሆኑና ካሪዝማቲክ የሚባሉት ሰዎች ደግሞ ይህንን ተሰጥኦዋቸውን ለልማትም ይሁን ለጥፋት ሊያውሉት የሚችሉ ቢሆኑም ያለፉት የኢትዮጵያ መሪዎች እንደየሥልጣን ዘመናቸው በያዙት ዓላማ፣ ያንን ዓላማ ለማስፈጸም በሄዱበት መንገድ እና ባስገኙት ውጤት ልክ በመሪነት ሚናቸው የህዝብ ተቀባይነት ያገኙ ነበሩ፡፡

ካሪዝማቲክ መሪ ዴሞክራት መሪ ብቻ ሳይሆን አምባገነን መሪም የሚሆንበት ዕድል እንዳለ ሆኖ በሥልጣን ዘመኑ በነበረው ተቀባይነት የተነሳ ኢ-ዴሞክራሲያዊነቱም ተዘንግቶለት ተወዳጅነት ካገኙ መሪዎች ውስጥ ስሙ የሚካተትበት ዕድልም ይፈጠራል፡፡

ለምሣሌም የግራም ይሁን የቀኝ ርዕዮት አራማጅ የሆኑት ሂትለር፣ ስታሊን እና ሌኒን በዘመናቸው ተጽዕኖ መፍጠር ከመቻላቸው ባሻገር ይዘው ለተነሱት ዓላማም ብዛት ያለው የህዝብ ድጋፍ ማሰባሰብ መቻላቸው በራሱ ካሪዝማቲክ መሪዎች እንዲባሉ አድርጓቸዋል፡፡

## በኢትዮጵያ "ካሪዝማቲክ መሪ" ማነው?

በኢትዮጵያ ከሩቅ ዘመን አንስቶ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ሀገሪቱን የገዙት አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ምንሊክ፣ አጼ ኃይለስላሴ እንዲሁም ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም እና አቶ መለስ ዜናዊ በራሳቸው መንገድ በህዝብ ዘንድ በነበራቸው ተቀባይነት ሳቢያ "ካሪዝማቲክ መሪዎች" ተብለው በምድቡ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መሪዎች ከመጠሪያ ስማቸው ጀርባ ምንም እንኳን ቆራጡ መሪ፣ ባለራዕዩ መሪ፣ አርቆ አስተዋዩ ንጉስ፣ ሀገር ወዳዱ አብዮተኛ ወዘተ የሚሉ ስያሜዎችን ከአጋሮቻቸው ወይም ከህዝቡ ያገኙ ቢሆኑም ከዚህ ጀርባ ከተቀመጠውና ከስማቸው ጋር ተያይዞ በሚነሳው የመሪነት ሰብዕናቸው እንዲሁም ብስል የፖለቲካ አመራር ጥበባቸው አንጻር ካሪዝማቲክ በሚለው መደብ ውስጥ እንዲጠቃለሉ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ወይም "ካሪዝማቲክ መሪ" እንደሚያሰኛቸው ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡

እነዚህ መሪዎች በየጊዜው የሠሯቸው በህዝብ የተወደደላቸውም ይሁን ያልተወደደላቸው ፣ የሚያስመሰግናቸው እና የሚያስወቅሳቸው የሚያሸልማቸው እና የሚያስከስሳቸው አያሌ ተግባራት እንዳሉ ሆነው በአንጻራዊነት በመሪነት ዘመናቸው የነበራቸውን ካሪዝማ ብዙዎች አይስቱትም፡፡

## ኃይለማርያምን ለምን "ካሪዝማ" ራቃቸው?

ሥልጣናቸውን በገዛ ፍቃዳቸው የለቀቁት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በፖለቲካ ሥልጣን ላይ በቆዩባቸው ስድስት ዓመታት ሁሉ ከቀን ቀን ቀልብ እየራቃቸውና በህዝብ ዘንድ ሞገሳቸው እየተገፈፈ በመምጣቱ በመጨረሻ አንድ ባለሥልጣን ሊኖረው የሚገባ ተቀባይነትን የመሠለ ወሳኝ ጉዳይ እንኳን ሊኖራቸው አልቻለም፡፡

አቶ ኃይለማርያም በጊዜው በአቶ መለስ ዜናዊ ኩትኮታ ወደዚህ ወንበር እንዲመጡና ተዘዋዋሪ አገልጋይ እንዲሆኑ በጥንቃቄ ሲቀረጹ በምልመላው ሂደት የራሳቸውን ሰብዕና ተነጥቀው ሙሉ በሙሉ በአቶ መለስ ራዕይ አስፈጻሚነት ዓላማ ብቻ ተሞልተው

ብቅ አሉ። በአደባባይ ባደረጉት ንግግርም "የኔ ሥራ የመለስን ራዕይ ማስቀጠል ብቻ ነው" በማለት በራሳቸው ሊሠሩት የሚችሉት ምንም ነገር እንደሌላቸው ገለጹ። ይህን በመሆኑም ከሀያ ምናምን ዓመታት የአንድ መሪ ፊት ብቻ ከማየት ተላቅቆ አዲስ ፊት በማየቱ ጥቂት ተጽናንቶ የነበረው ህዝብም ወሽመጡ ተቆረጠ። ለውጥ ይኖራል ብሎ ተሥፋ ያደረገው ሁሉ ተስፋ ቆርጦ ወደ ውስጡ ተሰበሰበ። ሲጀመር ገና ኃይለማርያም ካሪዝማ የራቃቸውና በህዝብ ዘንድ ያላቸው ቅቡልነት አናሳ የሆነበት ምክንያትም ይኸው ነበር።

የአቶ ኃይለማርያም ሥልጣን ምስጢራዊና ዝግ በሆነው ኢህአዴግ አሠራር ተሸራርፎ ግለሠቡ እንደመሪ ለዚያውም የሀገሪቱን የመጨረሻ የሥልጣን ጣራ የያዘ መሪ ወሳኝ እንዳይሆኑ አሽመድምዷቸዋል።

አቶ ኃይለማርያም በራሳቸው ግላዊ ባህሪም ይሁን ሥልጣን ላይ በቆዩበት ወቅት በነበራቸው የወሳኝነት ሥልጣን አንጻር ሲታይ ሳቢ እና ሰው ሊከተላቸው የሚችል ኣይነት መሪ አልነበሩም። ሰውየው በአንዳንድ ንግግሮቻቸው ላይ የቀድሞ ዐለቃቸውን አደራ ማስቀጠል ብቻ ሥራቸው እንደሆነ መናገራቸው በብዙዎች ዘንድ ኢህአዴግ ለገዛ ጥቅሙ አሻንጉሊት መሪ ያደረጋቸው ሰው ናቸው ወደሚል መደምደሚያ አሸጋግሮታል። ህዝቡም ኃይለማርያም እንደ አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር በብዙ ነገሮች ላይ ወሳኝ እንዳይሆኑ ያሽመደመዳቸውን የኢህአዴግ አሠራር ተችቶ ነገር ግን ኃይለማርያም በመጨረሻው ሠዐት ይህንን የሥልጣን መልቀቂያ መወሰናቸው ብልጥነት ነው ሲል አድንቋል።

በብዙዎች ዘንድ ሥልጣን እንደሌላቸውና ቦታው ላይ ብቻ ለሥም መጠሪያ እንደተቀመጡ መሪ የሚታዩት ኃይለማርያም እዚህ ግባ የሚባል ሚና ሳይኖራቸው ዘመናቸውን ቢገፉም በመጨረሻ ግን በርግጥም ታሪክ ሊያስታውሰው የሚችል ተግባር ፈጽመዋል። የርሳቸው ከሥልጣን ለመነሳት መጠየቅ በብዙዎች ዘንድ በቀና ታይቷል። አሳሪው የፓርቲያቸው ዝግ አካሄድ ብቻ ሣይሆን የራሳቸው የኃይለማርያም እስሩን ደፍሮ ለመፍታት አለመሞከር በሂደት በህዝብ ዘንድ ያላቸውን ዋጋ አውርዶ ያስከፈላቸውን መስዋዕትነት የተገነዘቡ የመሰሉት አቶ ኃይለማርያም ይህንን አዲስ ግፊት መጋፈጥ የሚችል መሪ ቀና ቀና ሲል ጊዜ ጠብቀው ሥልጣን መልቀቂያ ደብዳቤ አስገብተዋል። ራሳቸው እንዳሉት ሥራቸውን በገዛ ራሳቸው ለቀቁ እንጂ ግፊት አልነበረባቸውም። አንደንድ የፖለቲካ አዋቂዎች እንደሚናገሩት ግን ኃይለማርያም የማይወስኑ አሻንጉሊት ጠቅላይ ሚኒስተር መሆን ሰልችቷቸው ነው ሥልጣኑን የለቀቁት ይላል። ለማንኛውም ሰውየው አሁን ተራ ዜጋ ሆነው ሕይወትን ማጣጣም ሲጀምሩ ምናልባት በዚህኛው የሕይወት ጥግ የሚታይላቸው ባህሪ ይኖራልና የተገፈፈ ሞገሳቸውን ለመገንባት ብዙ ጊዜ የሚወስድባቸው አይሆንም።

## የዶክተር ዐብይ "ካሪዝማ "

ዶክተር ዐብይ ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው ቀደም ብሎ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሰው ሥለመሆናቸው ይነገር ሥለነበር፣ በዚህም የተነሳ የብዙኃን ትኩረት አቶ ለማ እና ዶክተር ዐብይ ላይ ስለነበር ኃይለማርያም ሲለቅቁ ኢህአዴግ ከነዚህ ሁለት ሰዎች አንዱን ቦታው ላይ እንዲያስቀምጥ በህዝቡ ብዙ ተወትውቷል። በኢትዮጵያ ታሪክ የጠቅላይ ሚኒስትር ምርጫ እንደ እግርኳስ እንዲህ በጉጉት ተጠብቆ አያውቅም ነበር ማለት ማጋነን አይሆንም። ያም ሆነ ይህ ዶክተር ዐብይ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ህዝቡ በደስታ ተቀብሏቸዋል።

ሰውየው በኢህአዴግ ተኮትኩተው በኢህአዴግ ጸድቀው እዚህ የደረሱ መሪ መሆናቸው ዕውነት ሆኖ ህዝቡ ግን ቢያንስ ያለበት ድረስ ሄዶ የሚያነጋግረው፣ የሚናገረው ነገር መሬት ጠብ የማይል፣ "ውስጤ ሠላምና ፍቅር አለ" ብሎ ሀገሪቱን ከመከፋፈል ለማዳን የሚሮጥ መሪ በማግኘቱ በደስታ ተቀብሏቸዋል። ኢህአዴግን የሚቃወም ሁሉ ዶክተር ዐብይን እንደ አንድ ሪፎርሚስት በመመልከት ድጋፍ መቸሩና ከርሳቸው ጋር መወያየት መጀመሩ ፣ ዶክተሩ በተለያዩ ክልሎች ዞረው ከህዝቡ ጋር መተዋወቃቸው፣ ለዳያስፖራው ጭምር ተሥፋ መስጠታቸው ከዚህ ቀደም የነበሩ መሪዎች ያላደረጉት ተግባር ስለሆነ ተቀባይነት ማግኘታቸው ጥርጥር አልነበረውም።

## የካሪዝማቲኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ባህሪያት አንደበተ ርቱዕነት

ዶክተር ዐብይ አንድ መሪ ሊታደለው የሚገባው ዓይነት ምናልባትም ባለግርማ ሞገስ መሪ ከሚወደስባቸው ዋና ምክንያት የሆነውን በቀላሉ ሰውን ለማሳመን የሚያስችል የንግግር ክህሎት እና ጥበብ መታደላቸው ለካሪዝማቲክ መሪነታቸው እንደ አንድ ነጥብ መገለጽ ይችላል።

ዶክተር ዐብይ የካሪዝማቲክ አመራር ቁጥር አንድ መለያ የሆነውን የንግግር ክህሎት ተክነዋል። መናገር ብቻ ሳይሆን ሰውን በሚያውቀው እና በተለይም በሚፈልገው ዋና ጉዳይ ውስጥ ገብቶ የጋራ ሀሳብ መፍጠር ፣ የሰውን ሥሜት ወደራስ በመሳብ፣ ደጋፊ በማከማቸት፣ የራስ ግምትን ከፍ በማድረግ በቀላሉ ዕምነትን መፍጠር ችለዋል። የአንደበተ ርቱዕነታቸው ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ የተደነቁበት በመሆኑ በዚህ ብቻ የሰውን አመኔታ ማግኘታቸውን አሥረግጦ መናገር ይቀላል።

## ወሳኝነት

ውሳኔ ማሳለፍ እንደ ባለ ሥልጣን ልዩ ችሎታንና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ሥራ ነው። ዶክተር ዐብይን በቢሮ ተቀምጠው በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲያሳልፉ ባናያቸውም ቅሉ ከተለያዩ የኅብረተሠብ ክፍሎች ጋር ባካሄዱት ውይይት ላይ በጉዳዮች ውሳኔ ለማሳለፍ ብቁ መሆናቸውን በዘወርዋራ ገልጸዋል። በተለይ ከንግድ ማኅበረሠብ አካላት ጋር በሸራተን አዲስ በተካሄደ ውይይት ላይ መረር ያለ እና ቁጣ የተቀላቀለበት ተግሳጽ ሲሰጡ በዚህም አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንደሚያሳልፉ ሲናገሩ እኚህ ሰው ከካሪዝማቲክ መሪነት ጎራ ስለመሠለፋቸው እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል።

## ባለራዕይነት

ባለራዕይ መሆን የአንድ ባለሥልጣን ትልቁ መለኪያ ነው። ሊፈጸም የሚችል ራዕይ መያዝ እና እሱንም ለህዝብ ማጋራት፣ ሥራውን በጋራ ሠርቶ ወደ ውጤት መምጣት ተፈላጊ እና ህዝብ የሚወደው ባለሥልጣን ችሎታ ብቻ ነው። ይህን የሚታደሉ መሪዎች ካሪዝማቲክ ናቸው ተብሎ ይደመደማል። በዚህ ረገድ ዶክተር ዐብይ ከጅምሩ የያዙት የኢትዮጵያዊነት መንፈስን የማደስና አንድነትን የማምጣት ራዕይ ከወዲሁ የመሥራቱ ምልክት እየታየ ነው። በአብዛኛው ብሔር ተኮር የሆኑ ንግግሮች ሁሉ ወደ ብሔራዊ ደረጃ አድገው ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ወደ ማለቱ ተሸጋግረዋል። በብዙው ኢትዮጵያዊ ህሊና እኚህን አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ያገዘፋቸው ልኬትም ይኸው የኢትዮጵያዊነት ራዕይ ነው። ዶክተር ዐብይ ሙስና ከኢትዮጵያ እንዲጠፋ ፣ ባለስልጣናት በህዝብ ሀብት መነገድ እንዲያቆሙ፣ የስራ ባህል እንዲዳብር፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር እንዲሁም በሀገሪቱ ሠላምና ዕርቅ እንዲሠፍን የያዙትን ራዕይ ይፋ በማድረግ ጉዳዩን ወደተግባር ለማውረድም የፖለቲካ እስረኞች ከመፍታት ውሳኔዎችና ተግባራት ጋር ብቅ ብለዋል። ይህ የሰውየውን ካሪዝማ ከፍ የሚያደረግና ህዝቡ ለርሳቸው ያለውን ክብር የሚጨምር ነው።

## ቁርጠኝነት

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሸራተን አዲስ ተካሂዶ በነበረው የንግዱ ማኅበረሠብ ውይይት ላይ የተናገሩት ነገር ምን ያህል የያዙትን ዓላማ ወደ መሬት ለማውረድ ፍላጎት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። "እኔ በሳምንት ሰባት ቀን እሠራለሁ። እናንተም ሠርታችሁ አሳዩኝ፤ ከዚያ በኋላ በሚዳብር የሥራ ልምድ ሀገር እንቀይራለን" ብለዋል።

የሥራ ባህል እንዲዳብር ቆርጠው የተነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስብሰባ ከስራ ሠዐት ውጪ ብቻ እንዲካሄድ፣ አመራሮች ሥራቸውን በውጤት ላይ ተመርኩዘው እንዲሠሩ ፣ የውጭ ጉዞ እና አንዳንድ ቅንጦቶች እንዲሠረዙ፣ የተዘረፈ የሀገር እና የህዝብ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት እንዲመለስ ወዘተ እንደሚሠሩ ቁርጥ ያለ አቋማቸውን አሳውቀዋል። በዚህ በኩል የካሪዝማቲክ መሪን ሚና እየተጫወቱ ነው ለማለት ያስችላል።

## ተክለ ሰውነት

የካሪዝማቲክ መሪ አንዱ መገለጫ በአካል ሲታይ ሰው ዐይን ውስጥ መግባት የሚችልና ተጽዕኖ ፈጣሪ ተክለ ሰውነት ማዳበር / መታደል/ ነው። በርግጥ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ታሪክ የሰው ዐይን የሚያርፍባቸው ብዙ ባለሥልጣናት ኖረዋል። ከነአለባበሳቸው ጭምር ህዝብ የሚያደንቃቸው ባለሥልጣናት ነበሩን። ይህ ዐይነግቡነት በቀላሉ በሰው ህሊና ውስጥ ለመቀረጽ እና ቀለል ብሎ ለመታሠብ መሠረት ነው።

ዶክተር ዐብይ ቀለል ያለ ተክለ ሰውነት ያላቸው፣ የማይከብዱ፣ ከመፈራት ይልቅ ለመከበር የሚቀርቡ፣ ፈገግታ ብርቃቸው ያልሆነ፣ በኢትዮጵያ የመንግስት ሥልጣን ታሪክ ወጣቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናቸው። ህዝቡ እንደ ልጁ፣ ወጣቶች እንደ ወንድማቸው፣ የሚያዩዋቸው መሆናቸው እንደ ባለግርማ ሞገስ መሪ ያስቆጥራቸዋል። በአሜሪካ እንደ ኦባማ እና ክሊንተን ያለ ተክለሰውነቱ ለግርማው ምክንያት የሆነ መሪ አልተፈጠረም ይባላል። በኢትዮጵያም አጼ ኃይለስላሴ ተክለሰውነታቸውና የፊታቸው ገጽታ በሰዎች ላይ በቀላሉ ተጽዕኖ ለማሳረፍ እና ለክብር አብቅቷቸዋል። ዶክተር ዐብይም የዚህ ትኩረት እና ካሪዝማ ተቋዳሽ ናቸው።

ከላይ የሠፈረው ሀሳብ ሲጠቃለል እንደ መሪ ሥነልቡና የዶክተር ዐብይን የውስጥ ሀሳብ ማንበብ ባንችልም እንደ ካሪዝማቲክ መሪ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለዚህ ስያሜ ብቁ ናቸው።



ስዩም ተሾመ

# የፍርሐት እና ተስፋ ድባብ ከጦላይ እስከ ጣውላ ቤት

የካቲት 29/2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 በዕለቱ አጣዳፊ የሆነ ስራ ስለነበረብኝ በጠዋት ተነስቼ ወጥቼ ቁርሴን ከበላሁ በኋላ ሥራዬን ለመሥራት መዘጋጀት እንደጀመርኩ የመኖሪያ ቤቴ በር ተንኳኳ:: በበሩ ቀዳዳ አሾልኬ ስመለከት ክላሺንኮቭ መሣሪያ የታጠቁ ፊታቸው የተኮሣተረ ቀይ ቦኔት ያደረጉ አየር ወለድ ወታደሮች የፊልድ ጃኬት የለበሠ ጀነራል (ጀነራል መሆኑን በኋላ ነው ያጣራሁት) እንዲሁም ሸንቃጣ ቁመና ያለው ኮሎኔል ቆመዋል:: በእርግጥ በዛን ሠሞን ልታሠር እንደምችል ገምቼ ነበር:: በመሆኑም ቀደም ብዬ መታሠሬን የሚገልፅ የጽሑፍ መልዕክት አዘጋጅቻለሁ:: ለዚህም የሚሆን የጽሑፍ መልዕክት የሚላክላቸውን ሰዎች ለይቻለሁ:: ይህን መልዕክት ለመላክ የሚያስፈልገውን የመልዕክት ጥቅል ገዝቼ እየተጠባበቅኩ ነበር:: ከላይ በጠቀስኩት ዕለት ፖሊሶች በሩን ሲያንኳኩ የመጀመሪያው ተግባሬ ሞባይሌን ከፍቼ ሴንድ (send) የሚለውን ቁልፍ መጫን ነው:: በዚህ መልኩ ከመታሠሬ በፊት መታሠሬን አሳወቅኩ:: በእርግጥ ብዙዎቻችሁ ሰው እንዴት መታሠርን ቀድሞ አውቆ ለመታሠር አቅዶ ይጠባበቃል የሚል ጥያቄ ልታነሱ ትችላላችሁ:: አዎ ባለፈው ዓመት አጋጥሞኝ ከነበረ ተመሳሳይ ሁኔታ የቀሰምኩት ልምድ ነው::

ብዙዎቻችሁ እንደምታስታውሱት መስከረም 20/2009 ዓ.ም ከቤቴ በተመሳሳይ መልኩ ታስሬ ነበር:: በወቅቱ ሞባይሌ ሳንቲም አልነበረውም:: መታሠሬን ቢያንስ ለወዳጅ ዘመዶቼ በግል ለማውቃቸው ሰዎች የት እንደታሠርኩ በማን እንደታሠርኩ ለምን እንደታሠርኩ ሳይቀር ማወቅ አልተቻለም ነበር:: ከዚህ ልምድ በመቅሠም እነሆ ዘንድሮ ከመታሠሬ በፊት መታሠሬን ገምቼ ለማሳወቅ እየጠበቅኩ ነበር:: በጠበኩት መሠረት ወታደሮች መጥተው ቤቴን ከበረበሩ በኋላ ወደ አደስ አበባ ተወሠድኩ::

በአምናና በዘንድሮው እስራቶች መካከል ከላይ ከጠቀስኩት ሁኔታ በሥተቀር ፈፅሞ ልዩ ነው:: ምክንያቱም በ2009 ዓ.ም ያሰሩኝ የኦሮምያ ፖሊሶች ሲሆኑ ዘንድሮ ያሰረኝ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ናቸው:: አምና ያሰሩኝ ፖሊሶች ሁሉም የኦሮምኛ ቋንቋ ይናገራሉ:: ዘንድሮ ያሰሩኝ ወታደሮች በሚገርም ሁኔታ ሁሉም የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው:: አምና ስታሰር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አልፀደቀም ነበር ዘንድሮ ስታሰር የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፀድቋል:: አምና ታስሬ የተወሰድኩት (በእርግጥ መጀመሪያ በወሊሶ ፖሊስ ጣብያ ነበር ቆይታ ያደረጉኩት) ከዚያ ቀጥሎ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወደ ጦላይ ጫካ ነው የተወሰድኩት:: ዘንድሮ ደግሞ ወደ መሃል አዲስ አበባ ወደሚገኘው የማዕከላዊ እስር ቤት ነው:: አምና የታሠርኩት ለ80 ቀናት ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ ለ40 ቀናት ነው:: በሁለቱም ጊዜ የታሰርኩበት ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመተላለፍ ሲሆን የታሠርኩበት ሁኔታ ግን ፈፅሞ የተለያየ ነው:: ቅድም እንደገለፅኩት የታሠርኩት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት 8 ቀኖች ቀደም ብሎ ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከወጣ ከ20 ቀናት በኃላ ነው::

ስለዚህ አምና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ሲታወጅ የማውቅበት ዕድል አልነበረኝም:: ስለዚህ አምና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወጥቶ ተግባራዊ ከሆነ በማንኛውም አግባብ እንደምጥስና ተገዥ እንደማልሆን አቋሜን ገልጫለሁ::

በአጠቃላይ በአምናውና በዘንድሮው እስራቶች መሃከል ቀጥተኛ የሆነ ልዩነት አለ:: አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ከተከሰስኩባቸው ሁለት አጋጣሚዎች የታሠርኩበት ሂደት ይሄን ያህል የሠፋ ቢሆንም የታሠርኩበት ምክንያትና ዓላማ ግን ፍጹም አንድና ተመሳሳይ ነው:: የአምናው ጦላይ በሚገኘው ጫካም ሆነ የዘንድሮው ማዕከላዊ በሚገኝ ጣውላ ቤት የታሠርኩበት ምክንያትና ዓላማ የሀሳብና የአመለካከት ነፃነቴን ለመገደብ ነው:: ምክንያቱም እንደ ጸሐፊ ሀሳቤን በነፃነት በመግለፅ የዘለለ የፈፀምኩት ጥፋት የለም:: የሰው ሕይወት አላጠፋሁም፤ ንብረት አላወደምኩም፤ የሰው መብት አልጣስኩም፤ በወንጀል የተጠቀሰ ተግባር አልፈፀምኩም:: ከዛ ይልቅ ሀሳብና አመለካከቴን በነፃነት ከመግለፅ የዘለለ ወንጀል አልሠራሁም::

እኔ ከምንም በላይ ነፃነቴን አፈቅራለሁ:: በተመሳሳይ ከምንም በላይ ፍርሐትን እፈራለሁ የአሳሪዎች ዓላማ ነፃነቴን በጉልበትና በፍርሃት መቀማት ነው:: ሰለዚህ ነገሩ የምወደውን ነፃነት የማሳጣት የምፈራውን ፍርሐት የማፍቀር ነው:: በእስራት የምወደውን ማጣቴ ብቻ ሳይሆን የምፈራውን መውደድ ይጠበቅብኛል:: የአሳሪዎቼ ዓላማ እጥፍ ድርብ ነው እኔም ለነፃነት ያለን ፍቅር ለፍርሐት ያለኝ ፍራቻ ያንኑ ያህል ነው::

ባለፈው ዓመት በጦላይ በነበረኝ ቆይታ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ስቃይና መከራ ደርሰብኛል:: በመሆኑም ከዚያ በወሰድኩት ልምድ ለዱላና ድብደባ ተገዥ አይደለሁም ዱላና ድብደባ አልፈራም:: አካላዊ ድብደባን መቋቋም እችላለሁ:: በእርግጥ ከአንድ ነገር በስተቀር:: ማዕከላዊ ከገባሁ በኋላ ጦላይ ያላጋጠመኝ አንድ ነገር ያጋጥመኛል ብዬ ዘወትር እፈራ ነበር:: እርሱም “ጥፍር መንቀል” የሚሉት የስቃይ ምርመራ ነው:: በማዕከላዊ እስር ቤት የመጀመሪያ ሠሞን ይህን የስቃይ ምርመራ በዐይነ ልቦናዬ እያሠብኩ ስቅጥጥ ይለኝ ነበር:: ውስጤን ያሰቃየኝ ነበር ስለዚህ ነገር ባሠብኩት ቁጥር በውስጤ ፍርሐት ይገባው

ጀመር:: ነፃነቴን ካፈቀርኩ ፍርሐትን ከጠላሁ ይሄን ጥፍር መንቀል የሚሉትን ፍርሐት ከውስጤ አንቅሬ ማስወጣት ነበረብኝ:: ፍርሐቴን ማሸነፍ ለማሸነፍ ስል ይህንን ስቃይ መለማመድ ነበረብኝ::

የቀኝ እግሬን ከአውራ ጣቴ ጎን ያለውን ጣት ጥፍር በእጄ ሠነጠቅኩት ከዛም ጥርሴን ነክሼ አይኔን ጨፍኜ የራሴን ጥፍር በእጄ ስቤ ነቀልኩት:: ደሜ በጣም ሲፈስ ቀዝቃዛ ውሃ ደፋሁበት አልቆም አለኝ በሶፍት እንቅ አድርጌ ያዝኩት:: አብሮኝ የታሠረው ከቆቦ የመጣው ወዳጄ ጥፍሬን በእጄ ነቅዬ ይገፄ ደሙን ለማስቆም ስታገል አይቶ የደነገጠው ድንጋጤ መቼም ከፊቴ አይጠፋም:: ለምን እንዳደረኩት ጠየቀኝ:: እኔም ፍርሐቴን ማስወገድ እንዳለብኝ ነገርኩት:: ጥፍሬን ነቅዬ በስቃይ መከራውን ተለማመድኩት ፍርሃቴን አስወገድኩት::

በዚህ መልኩ ጥፍር መንቀል የሚባለውን ስቃይ በመለማመድ በውስጤ ያቆጠቆጠውን ፍርሐት በጭካኔ አስወገድኩት:: ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት የስቃይ ምርመራ አልተደረገብኝም:: የደረሠብኝ ነገር ቢኖር በተለይ የእስረኞች ኃላፊ ከሆነው ኮማንደር የሚሠነዘርብኝ ስድብና ጥላቻ ነው:: እሱንም ቢሆን በጎሪጥ እያየሁ ታገስኩት:: ማዕከላዊ ውስጥ የስቃይ ምርመራ የለም እያልኩ አይደለም:: የደርግም መንግሥት “በቀይ ሽብር ዘመቻ” የኢህአዴግም መንግሥት “በፀረ ሽብር አዋጁ” አማካይነት በማዕከላዊ እስር ቤት ለሰው አዕምሮ በሚከብድ እጅግ አሰቃቂ ስቃይና ምርመራ አድርገዋል:: ሆኖም ግን እንዲህ ያለ ተግባር መቆሙን ታዝቤአለሁ::

በማዕከላዊ ካሉት አንዳንድ የጥበቃ ሠራተኞችና ሌሎች ባልደረቦች ስለጉዳዩ ጠይቄ እንዲህ ያለ የስቃይ ምርመራ ከወራት በፊት መቆሙን መረዳት ቻልኩ:: በማዕከላዊ ጣውላ ቤት ተብሎ በሚታወቀው ክፍል ሶስት ኮለን ላይ የተለጠፈ ወረቀት “የተጠርጣሪ እስረኞች መብትና ግዴታ” ይላል:: ይህ ወረቀት የተፃፈው በቀን 10/5/2010 ዓ.ም ነው:: ወደ 3ኛ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ከተዛወርኩ በኃላ በተመሳሳይ ቀን ተመሳሳይ ይዘት ያለው ወረቀት በየኮሪደሩ ላይ ተለጥፎ ታዝቤያለሁ::


ከዚህ በመነሳት ለዘመናት ሲካሄድ የነበረው የስቃይ ምርመራ ከላይ በጠቀስኩት ቀን በፖለቲካ ውሳኔ እንደቆመ ገመትኩ:: ከእስረኞች ኃላፊው ሲሠነዘርብኝ የነበረው ስድብና ጥላቻም ቢሆን ብዙ አልዘለቀም:: ከ25 ቀናት በኂላም ይሄ ነገር እንዲቆም ለመታዘብ ችያለሁ:: ለምን ቆመ ለሚለው በሆነ ምክንያት እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ:: የአሳሪዎች ስድብና ዛቻ ብቻ ሳይሆን በማዕከላዊ በዓይነ ቁራኛ ሲመለከቱኝ የነበሩ ኃላፊዎች እኔን ማየት፣ ማፍጠጥ፣ ማስፈራራት ትተው አቀርቅረው ቆዝመው ሲሄዱ ታዝቤአለሁ:: ያየሆነው የዶክተር ዐብይ አሕመድ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆኖ ከተመረጠ ጀምሮ ነው:: የዶክተር ዐብይን መመረጥ ተከትሎ ማዕከላዊ እስርቤት የሚገኙ መርማሪዎችና ኃላፊዎች በሰዎች ላይ ሲያደርሱት የነበረው ስድብና ጭቅጭቅ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሲሄድ ታዝቤያለሁ:: ስለዚህ የዶክተር ዐብይ መመረጥ ሌላው ቀርቶ እስር ቤት ውስጥ ያለውን ድባብ ቀይረዉታል ማለት እችላለሁ::

ከዚህ በተጨማሪም ማዕከላዊ ጣውላ ቤት የነበርነው እኔና ኮሎኔል እያሱ አንጋሱን ጨምሮ ሌሎች ሁለት እስረኞች ከጣውላ ቤት ወደ 09 ወይም በተለምዶ ሸራተን ተብሎ ወደሚታወቀው ክፍል ተዛወርን:: ውጭ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ማዕከላዊ ውስጥ ያሉትን ፖሊሶች እንደቆዘሙ አቀርቅረው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል:: እስረኞች ላይ ስለሚፈፀሙ ሸር እና ሻጥር፤ ድብደባና ስቃይ ይልቅ የራሳቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያሳሠባቸው ይመስላል:: ትኩረታቸውን ከእኛ ወደ ራሳቸው አድርገዋል::

ከጣውላ ቤት ወደ ሸራተን መዛወራችን የመፈታት ያህል ነበር:: ጣውላ ቤት ፀሐይ የምንሞቀው ለ10 ደቂቃ ብቻ ነበር:: ከዛ በተጨማሪም እርስ በርስ ከሌሎች ታሳሪዎች ጋር መነጋገር ቀርቶ ከጥበቃ ሠራተኞች ጋር እንኳን ሀሳብ መለዋወጥ ፈፅሞ የተከለከለ ነበር:: ሸራተን ስንገባ ግን ሁሉ ነገር ዝብርቅርቅ አለብን:: በተለይ እኔና ኮማንደር እያሱ የተፈታን ያህል ደስ አለን:: ከሌሎች እስረኞች ጋር መነጋገር ቻልን:: ጠዋት እስር ቤቱ ከተከፈተበት እስከሚዘጋበት 12 ሠዐት ድረስ ፀሐይ መሞቅ ቻልን:: ከሌሎች እስረኞች ጋር መጨዋወት ጀመርን:: በዝምታ ታፍኖ የነበረ አንደበታችን ተከፈተ:: ሸራተን ከገባን በኂላ ካገኘናቸው እስረኞች አንዱ ታየ ደንደሃ ነበር:: ታየ የሚገርም ፅናት የሚገርም ግንዛቤ እና አመለካከት ያለው ሰው ነው:: እዛ ከገባን በኂላ በነበረን ቆይታ በወቅታዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች፤ በአገራችን ታሪክ፤ በየግላችን ስለደረሠብን ስቃይ፤ በጦላይ ስለደረሠብኝ የምርመራ ዓይነት፤ በዜጎች ላይ እየደረሠ ያለው መከራና ስቃይን አስመልክቶ በዝርዝር አስረዳሁት:: የኦሮሚያ ክልል የፍትሕ ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እንደመሆኑ ጉዳዩ ይመለከተዋል:: ስለዐብይ ተከራከርን ብዙ ሃሳብ ተለዋወጥን ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍን:: ሸራተን እያለሁ ዶክተር ዐብይ የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ሲሾም ያደረገውን ማራኪ ንግግር ነበር ቀጥታ ሥርጭት ተመለከትኩት:: ኢትዮጵያዊነት እንደዚህ ሲዘመር አይቼ አላውቅም:: እርግጥ ነው ዶክተር ዐብይ የተናገረውን ነገር እንዲናገር ዶክተር መራራ ታስሯል:: ስለ ህዝቦች አብሮነትና አንድነት የተናገረውን እንዲናገር ኦቦ በቀለ ገርባ በእስር ተሠቃይቷል:: ስለ ህዝቦች አንድነት ስለ ፍቅር ስለ ወንድማማችነት የተናገረው ነገር እንዲናገር እስክንድር ነጋ አሸባሪ ተብሏል:: አንዳዷለም አራጌ ተሠቃይቷል:: ተመስገን ደሳለኝ መከራ አይቷል:: ብዙዎች ሰዎች ታሥረዋል፣ ተሠደዋል፣ ተገለዋል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል:: ዶክተር ዐብይ ወደ ሥልጣን የመጣው በራሱ ጥረትና ትግል ብቻ ሳይሆን በብዙዎች መስዋዕትነት፤ በብዙዎች መከራና ስቃይ ነው:: በእርግጥ ድል ከተባለ ይሄ ድል የህዝብ ድል ነው:: ዶክተር ዐብይ የያዘውን ዕድል ተጠቅሞ የአገራችንን ፖለቲካዊ ሁኔታ ወደ ተሻለ ምዕራፍ ያሸጋግረዋል ብዬ ተሥፋ አደርጋለሁ:: ይሄ በሂደት የምንታዘበው ሆኖ ሳለ አንድ በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ነገር ቢኖር የዶክተር ዐብይ መመረጥ እስር ቤት ውስጥ ያለውን ድባብ ሙሉ ለሙሉ ቀይሮታል:: በአገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ድባብ በተመሳሳይ ይቀይረዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::



*አቶ ታዮ ደንደአ እና ስዩም ተሾመ ከአ.አ. ፖሊስ ኮሚሽን ከእስር በተፈቱበት ወቅት የተነሱት ፎቶ*



ሙሐመድ እንድሪስ (ዶ/ር) ዕጩ

# ኢትዮጵያዊነት በማበብ እና በንቅለ - ተከለ መካከል

'የኢትዮጵያ ታሪክ' እና ኢትዮጵያዊነት ሾላ በድፍኑ ሲሆኑ እንጂ ሲገለጡ እንደ ድር የሚተረተሩ ያልጠሩ እና መፃኢ እጣ ፈንታቸውም በውል ያልታወቁ ባህሪያት አሏቸው:: ለዚህም ነው ብዙሀኑ 'ኢትዮጵያን እናስቀድም ሁሉም ያለ ኢትዮጵያ ጎዶሎ ነው' በሚለው እሳቤ ስር ሾላ በድፍኑ የሆነ የአንድነት ጥሪ ይታያል ሲባል የሚደመጠው:: ለዚህም ነው በታሪክ እና ማንነት ነክ ጉዳዮች ላይ በድፍኑ መርጦ የማንገስ እና መርጦ የመርሳት ስልትን እንደተሻለ አማራጭ የሚቀርቡት:: ይህ አካሄድ ግን ለአንድ ወቅት ወይንም ትውልድ ይሰራ ይሆናል እንጂ ለሁሉም ዘመን እና ትውልድ ቋሚ መርህ ሊሆን አይችልም:: ምናልባትም መርሁ ለግዜው እና ለትውልዱ የማይገጥም በሚሆንበት ወቅት አስተሳሰቡ ተቀባይነት እንዲያገኝ በብርቱ የሚለፋለት፣ ድሩ የቀጠነ፣ ብዙሀኑ የገፉትና ጥቂቶች የቆሙለት አስተሳሰብ ወደ መሆን ሊያዘግምም ይችላል:: ይህ የፖለቲካ አሰላለፍ እና የትውልድ ልዩነት የሚያመጣው ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁነት ነው::

'የኢትዮጵያ ታሪክ' እና ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚሰጡ አስተያየቶችና የሚሰነዘሩ ትችቶች ኢትዮጵያ ላይ እና ኢትዮጵያውያን ላይ የተሳቡ ቃታዎች አድርጎ የመውሰድ እሳቤ የሚያግባቡ እውነታዎች እንዳይመጡ እንቅፋት ሆነው ከቆዩ ምክንያቶች ዋናው ነው:: የዚህ መነሻው ደግሞ በታሪክ ውስጥ ማዕከላዊ ቦታ ለመጨበጥ በሚደረገው ጥረት ኢትዮጵያ የምትባለዋን እመቤት እስትንፋስ እና ደም ግባት የነገስታቱ ታሪክ ብቻ አድርጎ የማቅረብ ህዝብን የዘነጋ ቁንፅል የታሪክ አረዳድ የፈጠረው እንደሆነ መገመቱ አይከብድም:: ለነገስታቱም የተወሰነ ባህል እና እምነት በማውረስ የአቢሲኒያ ነገስታት ታሪክ በመፅሀፍ መልክ ተሰድሮ ሲዘጋጅ አንድ ራዕይ የነበራቸው፣ ዛሬ ያለችውን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የትግሉን ባንዲራ እየተቀባበሉ ያለፉ ተደርጎ ለመሳል ጥረት ይደረጋል::በነዚህ ነገስታት መካከል የግዜ ክፍተት የሌለው መተካካት የነበረበት ፍፁም ወጥ የሆነ የታሪክ ሰንሰለት መኖሩን ለማሳየትም ይጣራል::

ከላይ የጠቀስነው አይነት የታሪክ አቀራረብ የግዜ ቅደም ተከተልን ብቻ የሚያመላክት በነበረ ወርድ እና ስፋት በማይለካ መልኩ አቀራረቡ ላይ መስማማት ባልከበደ:: ከዚህ የነገስታት ታሪክ ሰንሰለት በስተጀርባ ሳይልም እንዲዋጥ የሚቀርበው ጉዳይ ግን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ታሪክ ይህን ሰንሰለት የተከተለው ሲሆን የሌሎች ህዝቦች ታሪክ ከዚህ ሰንሰለት አንፃር ብቻ እየተቃኘ የሚለጠፍ፣ ተቆርጦ የሚገባ እና ተንጠልጥሎ የሚሄድ የታሪክ ዳርቻ የማስመሰል ተልዕኮን ያነገበ ነው:: የታሪክን ማዕከላዊነት እና ዳርቻን ለማሳየት የሚደረገው ጥረት የታሪኩ ባለቤት ነን የሚሉትንም በዚያው መጠን በሀገሪቱ ላይ ያላቸውን ቦታ ወደ መወሰን ይሸጋገራል:: የአፄዎቹ ዜና መዋዕል እና የንግስናቸው ሰንሰለት የኢትዮጵያ ታሪክ መሀል ተደርጎ ስለሚወሰድ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዚህ ጋር በማስታከክ መተረክ እንደ ህግ እንዲቆጠር ይጠበቃል:: ሌሎች ታሪኮች የሚተነተኑት ከ'ማዕከላዊ' ታሪክ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት፣ መሀሉን እንዴት ተፅእኖ እንዳሳደሩበት፣ 'መሀሉ' እንዴት ቅርፃቸውን እንደ ለወጠው....አይነት የአተራረክ መንገድን በመከተል ነው:: ይህን የአተራረክ ስልት ብዙዎቹ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ምሁራን ተከትለውታል::

እነ ስርግው ሐብተስላሴ ዓፄ ምኒልክን የዛሬይቱን የኢትዮጵያ ካርታ የቀረፁ በሚለው ሳያቆሙ ተልእኳቸውም በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት የጀመረው ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ተልዕኮ ማጠናቀቅ እንደነበር ወጥነት ያለው ምስል ሊሰጡን ሞክረዋል:: ፕሮፌሰር መስፍን መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ሲሉን ለሰንሰለቱ ተጠብቆ አለመቆየት የተከራከሩትን ያህል ለይዘቱ ክሽፈት የሚመጥን ስፍራ አልሰጡም ብዬ እሞግታለሁ:: Trimingham, Islam in Ethiopia በሚለው መፅሀፉ 'የእስልምና ታሪክ በኢትዮጵያ ያለ ክርስቲያን አቢሲኒያ ታሪክ ባዶ ነው-ቦታ የለውም' ሲል በታሪክ ውስጥ ማዕከላዊ እና ዳርቻ የሚባሉ ስፍራዎች እንዳሉ እመኑኝ እያለ ነው:: በሌላ በኩል የአቶ አለባቸው ታላቁ ተቃርኖ የሀገረ-መንግስት ምስረታ ላይ ያሉ የታሪክ ተቃርኖዎችን በማሳየት አዲስ ፍኖት ጠቁሞናል:: አቶ ዩሱፍ ያሲን በአሰባሳቢ ማንነት ስራቸው ላይ የማይነኩትን እየነካኩ ስለኢትዮጲያዊነት ባለን ግንዛቤ ከገባንበት ቀለበት ወጣ ብለን ማየት እንዲችሉ ሁሉንም ወገኖች ተጣርተዋል:: ግብረመልሱ ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም-በተለይም ፍቃደኝነት እና ተራማጅነት የሚስተዋልበት ግብረመልስ የለም ማለት ይቻላል:: በማህበረሰብ የለውጥ ሂደት ላይ ነባር እና አዲስ አስተሳሰብ ሁሌም በግጭት ውስጥ ናቸው ብሎ ማመንና አዲስ አስተሳሰብ ቀድሞ የነበረን አስተሳሰብ ተክቶ እንጂ በጋራ የሚቆምበት ቦታ የለውም የሚል መሰረተ ቢስ ስጋት ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል::

እንዲህ ባለው የገነገነ ስህተት ውስጥ በገባ የታሪክ አተራረክና የማንነት ማካለል ሂደት ውስጥ ያልተጠኑ የህዝብ ታሪኮች ወደገበያ ሲመጡ እጣ ፈንታቸው አይታወቅም:: የዚያ ታሪክ ባለቤት ህዝቦች ሚናም እንዲሁ:: የኢትዮጵያ ታሪክ እና የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሞልተው የተረፉ ይመስል አዲስ የሚጠና የህዝቦች ታሪክ እና የሚጎለብት የማንነት ስነልቦና የዳር ተመልካች ብቻ እንደሚሆኑ በተፈጠረው ምስል ሳቢያ ብዙዎች የተናጠል ጉዞ ጀምረው የብሔር ፖለቲካው አፈር ላይ የበቀለ አዲስ የማንነት እሳቤ እና አሰላለፍ እንዲፈጠር በር ተከፍቷል:: ምክንያቱም ህዝብ ታሪኩን ሲፅፍ መፃዒ እድሉንም አያይዞ መወሰን ይፈልጋልና:: መዘዙ ደግሞ የታሪኩን እና የታሪኩን ባለቤት እጣ ፈንታ የጋረደ የታሪክ ግድግዳ ሲያጋጥም ያለው አማራጭ መሀል የሚባለውን ታሪክ ዳር አድርጎ የማቅረብ የፉክክር ታሪክ አፃፃፍ ውስጥ መግባት ይሆናል:: መሀሉን ስትነካው ዳሩ መሀል ይሆናል እንዲሉ::

## ቅፅበታዊው የኢትዮጵያዊነት 'ማበብ'

ኢትዮጵያዊነት የፖለቲካ አሰላለፍን የሚሻገር ብዙሀኑ የሚግባባበት ማንነት ሊሆን ባለመቻሉ እንደማንኛውም የጋራ ስምምነት እንደሌለበት ጉዳይ ወሳኝ የፖለቲካ መሳሪያ እና በፖለቲካ ሚዛን የሚሰፈር እንዲሆን አድርጎታል:: በተለይም ኢትዮጵያ የረዥም ግዜ ታሪክ ያላት አገር ህዝቦቿም በተናጠል ሰፊ ታሪክ እያላቸው ፤የጋራ ታሪካቸውም ገና በወጉ ተዳሶ ተገቢውን ስፍራ ባለመያዙ ኢትዮጵያዊነትን ማቁለጭለጭ እና በኢትዮጵያዊነት ማስፈራራት ሁነኛ የፖለቲካ ገመድ ቢሆን የሚገርም ላይሆን ይችላል:: አሁን ደግሞ ይህ የገመድ ጉተታ በቅፅበት ትኩረት የመሳብ አቅሙ ጨምሮ 'ሱስ' የመሆን ማማ ለይ ተሰቅሎ፣ 'የመደመር' ውበት ተሰኝቶ የወቅቱ ፖለቲካችን አንዱ መዘውር ሆኗል:: መሰረታዊው ጥያቄ ግን ይህ ቅፅበታዊ ማንሰራራት ቀድሞ ሲተረክ የኖረው ኢትዮጵያዊነት 'ማበብ' ሊባል የሚችል ይሆን? የሚለው ሲሆን መልሱ አሉታዊ እንደሆነ እየሞገትኩ በማስከተል የሚወለደው ጥያቄም ስለ የትኛው አይነት ኢትዮጵያዊነት? የሚለው ላይ ሀሳቦችን ለማንሸራሸር ልሞክር::

## የብሔር ፖለቲካ የሚገነባ አገራዊ ብሔርተኝነት ጅምር ሂደት

በሀገራችን የአሀዳዊው ስርዓት በታሪክ በነበሩበት ግድፈቶች እና የማንነት ጥያቄ ካለው የፖለቲካ ሚና የተነሳ ባለፉት 3 አስርት አመታት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የመጣው የሁሉም ብሔሮች ethnic consciousness እንዲሁም የአንፃራዊ መሰረት ከያዙት ብሄር ተኮር መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ተቋማት መስፋፋት አንፃር የብሔር ፖለቲካ በማንነት ቀረፃው ላይ ረዥም ርቀት ሲጓዝ አጭር ለማይባል ግዜም ተፅእኖው የሚቀጥል እንዲሆን አድርጎታል:: የኢትዮጵያዊነትን ካባ ደርበው በአገሪቱ አራቱም አቅጣጫ የማሰባሰብ ፖለቲካ እየሰሩ ያሉት ጠቅላይ ሚንስትርም ከዚሁ ምንጭ የፈለቁ ናቸው:: ጠለቅ ብለን ካየነውም ትናንት የተጣለ እርሾ አዲስ እንጀራ እንጂ የቂሮ ትግል አፍለኛም አይደሉም-ጠቅላይ ሚንስትሩ:: ጥቂት ላፍታታው፡-

ኦባማን ያነገሰው የ21ኛው ክፍለ ዘመን የዴሞክራት እና ሪፐብሊካን ፓርቲዎች ፉክክር ሳይሆን የጥቁር አሜሪካውያን የነፃነት ትግል እንደሆነው ሁሉ ከኦሮሞ ህዝብ ታሪክ አንፃር ስናየው ዶክተር አብይንም ለስልጣን ያበቃቸው በዋናነት የረዥም ዘመን የኦሮሞ ህዝብ ትግል ነው:: ይህ ትግል በየዘመናቱ ያለፈባቸው ሂደቶች ቢኖሩም በማንነት ላይ ያለመደራደር ቋሚ መገለጫው ነው:: በማንነት ላይ ያለመደራደር ስነልቦናውን ፅኑ መሰረት ላይ ያቆሙ ምሁራን እድሜያቸውን በዚያ ላይ አሳልፈዋል:: የፕሮፌሰር መሐመድ ሀሰን የግል ሲቪው ድግግሞሽ ያልበዛበት የነጠሩ ስራዎቹን ይዞ 20 ገፅ ሲሆን የሚናገረው ነገር ግልፅ ነው:: የእውቀት ማምረቱ ሂደት ብዙ ርቀት ተጉዟል:: በግሌ ሀሳቡን ባልገዛውም በኢትዮጵያ የአገር ምስረታ ሂደት ላይ የቅኝ ግዛት ቴሲስ የሚያቀነቅኑ ምሁራን ከወጣትነት እስከ ጎልማሳነትና እርጅና እድሜያቸውን በኦሮሞ ጥናት ላይ ማሳለፋቸው ሳያንስ ልጆቻቸው የጥናትና ማእከላቱ ተተኪ ኃላፊ እየሆኑ መምጣት ሁለተኛ ትውልድ የደረሰ ምሁራዊ የማንነት ግንባታ እየተካሄደ ነው የሚለውን ይነግረናል::

ዛሬ ላይ የቁቤ ትውልድ እና ቄሮ እየተባለ የሚጠራው ወጣት የብሄር ፖለቲካ የፈጠረው ብቻ አድርጎ ማሰብ ወደ እውነታው ስለማያመራን የማንነት ግንባታው ያለፈበትን ረዥም ሂደት እውቅና በመስጠት ነባራዊውን ሁኔታ የሚመጥን አቋም መያዙ የተሻለ ነው:: በዚህ በማንነት ላይ መደራደር በማይፈቅድ ትውልድ ትግል የመጣ የፖለቲካ ለውጥ ነው ኢትዮጵያዊነት እየተቀነቀነ የሚገኘው:: ይህ ኢትዮጵዊነት ግንዱ እና ስሩ የከረመ ነገር ግን የ27 አመት የብሔር ፖለቲካ ቅጠሉን ሊያደርቀው ሲል በተአምር በቅፅበት ያበበ ኢትዮጵያዊነት አይደለም:: በባህሪው አዲስ ነው:: ጠቅላይ ሚንስተሩ በተጓዙባቸው ቦታዎች ስለ ኢትዮጵያ እና አብሮነት ይሰብካሉ እንጂ ጎንደር ላይ የሚተርኩት ኢትዮጵያዊነትን አምቦ ላይ አይደግሙትም፣ ለሶማሌዎች የሚነግሯቸውና ትግራይ የሚያወሱት ይለያል:: መለያየቱ ግን የጋራ የሚያደርጉትን ባህሪያት ሙሉ ለሙሉ አያሳጡትም:: ልዩነቱን እውቅና ሰጥተው ለልዩነቱ እውቅና የቸረ ትርክት ነው የሚያቀርቡት፣እንዲያቀርቡም እድሉ ያላቸው:: በተለምዶ ሸላ በድፍኑ የሆነው የአንድነት አስተሳሰብ አቀንቃኝ የሚባሉ ክፍሎችም እንደ ወትሮው እኔን ያልመሰልክ ጥግ ያዝ የሚሉበት ስነልቦና ላይ አይደሉም:: ውጥረቱ የፈጠረውን አደጋ በመገንዘብ አልያም ለአመታት ውጤታማ መሆን ያልቻለውን መንገድ በመተው የማርያም መንገድ ፍለጋ ላይ መሆናቸው አንዱ መልካም ነገር ሆኖ የሚታይ ነው:: ስሩ እና ግንዱ ህዝብ እና የህዝብ ታሪክ የሆነ አዲስ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ እያረበበ እንደሆነ ያስታውቃል::

ኢትዮጵያዊነትን አዲስ ቅኝት እንዲይዝ ያደረጉ ሂደቶች ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ብቻ የተሳሰሩ አይደሉም:: በድህረ 1966 አብዮት የጀመረ እና በቅርብ አመታት አሰርቲቭ ሊባል በሚችል መልኩ እያንሰራራ የሚገኝ የሀገራዊ ብሔርተኝነት ከሙስሊሙ ማሕበረሰብ በኩልም ይታያል:: በሀገራዊነት ላይ የሚታይ ጉልህ ተቃርኖ ባለማሳየት የሚታወቀው ይህ የማህበረሰብ ክፍል በታሪኩ እና እሴቶቹ የአገራዊ ብሄርተኝነት መገለጫነት ውስጥ ተንፀባርቆ የማየት ራዕይን በተለይም የሙስሊሙ የመብት ማስከበር እንቅስቃሴን የማስከተል እድል አለው:: ምክንያቱም ድምፁ መቀነሱ የሚፈለገው ሲያራምድ ከነበረው የአንድነት አስተሳሰብ እንጂ አንድነት ከሚለው ፅንሰ ሀሳብ አይደለምና:: በሌላ በኩል Ethnic politics ብዙውን ግዜ በአንድ መልኩ እውቅና ሲያገኝ ይበልጥ እየጠነከረ እና የብሄር አጥሩ ውስጥ ብቻ ታጥሮ ወደ አክራሪ ብሄርተኝነት የመቀየር ባህሪ እንዳለው ይታመናል:: የብሔር ፖለቲካ አራማጆች እና መሪዎችም እውቅናቸው የሚመነጨው ለብሔር መብት በመታገላቸው በመሆኑ ያንን ብሔርተኝነት ዶዙን እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር ተቀባይነታቸው ይጨምራል:: ለዘብተኛ መሆን በጀመሩ ቁጥር ተቀባይነት የማጣት አደጋ ሊያጋጥማቸው ስለሚችል ከብሔር ማዕቀፍ ለመውጣት አይደፍሩም:: ለዚህም ነው ብሔር ላይ የተመሰረተ የሀገር አንድነት ተግባራዊ መሆን አይችልም የሚሉ ድምፆች የሚሰሙት:: ይህን መላምት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ስንገመግመው ግን የብሔር ፖለቲካው እራስን የማስከበር ግቡን

> **በተለይም ኢትዮጵያ የረዥም ግዜ ታሪክ ያላት አገር ህዝቦቿም በተናጠል ሰፊ ታሪክ እያላቸው ፤የጋራ ታሪካቸውም ገና በወጉ ተዳሶ ተገቢውን ስፍራ ባለመያዙ ኢትዮጵያዊነትን ማቁለጭለጭ እና በኢትዮጵያዊነት ማስፈራራት ሁነኛ የፖለቲካ ገመድ ቢሆን የሚገርም ላይሆን ይችላል**

ተከትሎ ገበያው ላይ በስፋት ይታያል:: በአገር ምስረታ ሂደት ዘግይተው የተካተቱ የተቀሩት የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ አካባቢ ህዝቦችም ቀድሞ የነበረው ከባለመሬቱ ይልቅ መሬቱን እውቅና የሚቸር አገራዊነት እራሳቸውን ነፃ እያወጡ አዲስ የአገራዊነት እና የአገራዊ ማንነት ግንባታ ሂደት ውስጥ እያለፍን እንደሆነ ማሳያ ናቸው:: ይህን መሰሉ አዲስ አሰላለፍ ደግሞ በዶክተር ደረጄ ፈይሳ አገላለፅ reformed Ethiopian polity በመገንባቱ ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል::

## የኢትዮጵያዊነት ንቅለ-ተከላው መዳረሻ

ኢትዮጵያዊነትን አስመልክቶ እየታየ ያለውን ለውጥ የአንዱ ወገን ‘ኢትዮጵያዊነት አፈር ልሶ ተነሳ’ ሙግትም ሆነ የሌላው ወገን ‘ያለ ፍቃዴ የተሸከምኩት ቀንበር ሆነብኝ’ ስሞታ ትርጉማቸውን የሚያጡበት ሂደት እሩቅ እንዳልሆነ ሂደቱ ይመሰክራል:: ምክንያቱም እየተካሄደ ያለው የነባሩ ስታተስኮ ቅጥያ ሳይሆን አንፃራዊ በሆነ መልኩ ንቅለ-ተከላ ባህሪ ያለው አዲስ ስሪት ሊባል የሚችል ነውና::

አሁን ሁሉም ወገን ማረፊያ እየፈለገ ነው:: የሾላ በድፍኑ አንድነት ጥሪው ድምፅ እየመነመነ ይገኛል:: ይህ ግን በዩን ጠብቆ እንዲፈስ ካልተደረገ ጥቅምም ጉዳትም ከመታ እና በማንነቱ የማይደራደርበት አገራዊ ብሔርተኝነት መምጣቱን ካረጋገጠ ለኢትዮጵያ ስጋት አለመሆኑንን ይመስላል:: እነዚህ ሁለቱም መልካም አጋጣሚዎች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው::

የማንነት ጥያቄዎችን ባለቤቶቹ የማያስነኩበት የንቃት እና የአቅም ደረጃ ላይ ከደረሱ እንዲሁም የሾላ በድፍኑ የአንድነት አስተሳሰብ በሌሎች ማንነት ላይ አደጋ የመሆን አቅሙ ከተዳከመ የማንነት ጥያቄዎች ዋና (ብቸኛ) የትግል ሞተር መሆናቸው በመቀነስ ሁሉም አካል የጋራ ፍላጎት ሊባሉ በሚችሉት(ሰላም፣ ፍትህ፣ ነጻነት፣ ልማት….ወዘተ) ላይ ሲያተኩር የህዝቦች መቀራረብ እና የ political actors አብሮ መስራት የሚበረታታበት አየር ይፈጠራል:: የብሔር ፖለቲካው የደረሰበትን ነባራዊ ተጨባጭ እውቅና በመስጠት እና አደረጃጀቱን በተናበበ መልኩ በመጠቀም በግዜ ሂደት የፖለቲካ ምህዋሩ በጋራ ፍላጎቶች ላይ ይበልጥ እንዲያተኩር ለመስራት ሰፊ እድል ይፈጥራል:: ለዘብተኛ ድምፆች ከሁሉም ካምፕ እንዲዘወተሩ በማድረግ እየተካሄደ ያለውን የኢትዮጵያዊነት ንቅለ ተከላ ከዳር እናድርስ የፅሁፌ ዋና መልእክት ነው::

በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ ውይይቶች የሚመጡ ከሆነ ለማስተናገድ ፈቃደኛ እንደሆንኩ ለመግለፅ እወዳለሁ::

ቸር እንሰንብት

# ሚያዝያ ወር በታሪክ ውስጥ

### ሚያዝያ 2 ቀን 1860

በጀነራል ናፒር የተመራው የእንግሊዝ ጦር መቅደላ አምባ በታች አሮጌ በትግሬ ስፍራ ከአፄ ቴዎድሮስ ጦር ጋር ተዋጋ ፤በውጊያው ፊታውራሪ ገብርዬ ተገደሉ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 505

ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ሊቅ መሃሌታዊው ቅዱስ ያሬድ ተወለደ

ሚያዝያ 28 ቀን 1874

አምባቦ በተባለ ስፍራ የሸዋው ንጉስ ሚኒልክ ሰራዊት ከጎጃሙ ንጉስ ተክለሃይማኖት ሰራዊት ጋር ተዋጋ፤ በጦርነቱ ንጉስ ተክለሃይማኖት ተማርኩ፤ ጦርነቱ በሚኒልክ አሸናፊነት ተጠናቀቀ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1903

ከአፄ ሚኒልክ ሞት በኋላ የአልጋ ወራሽ የልጅ እያሱ ሞግዚትና ጥብቅ ገዢ ራስ ተሰማ ናደው ከዚህ አለም በሞት ተለይተው ደብረ ሊባኖስ ተቀበሩ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1918

በአሜሪካዊው ሚሲዮናዊ በዶክተር ራምሴ አማካይነት አዲስ አበባ ውስጥ የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ፤ ወይንም በቀድሞ ስሙ ቤተሳይዳ ሆስፒታል ተቋቋመ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1941

የአዲስ አበባ የሊሴ ገብረማሪያም ትምህርት ቤት ተመርቆ ስራ ጀመረ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1943

ከኢትዮጵያ ክቡር ዘበኛ ጦር የተውጣጣ አንድ ሻለቃ ጦር ቃኘው በሚል መጠሪያ ተሰጥቶት፤ ሰላም ለማስከበር ወደ ኮሪያ ዘመተ:: ዘመቻ ሰራዊቱ ወደ ጅቡቲ በባቡር ሲጓዝ ቀዳሚው ሃይለ ስላሴ ባቡር ጣብያ በመገኘት አሰናብተውታል::

### ሚያዝያ 6 ቀን 1860

የትንሳኤ ማግስት መቅደላ አምባ ላይ  አፄ ቴዎድሮስ ከጥቂት መቶ ታማኝ ወታደሮች ጋር በጄኔራል ናፒር ከሚመራው የእንግሊዝ ጦር ጋር ተዋግተው በጀግንነት ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1966

በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን የሚመራው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ህገ መንግስታዊ የዘውድ ስርአት ለመመስረት ህግ እንዲያረቅ፤ የታዘዘውን አጥኚ ሸንጎ በአስፈላጊው ሁሉ እንደሚተባበር አሳወቀ::

ጠቅላይ ማኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ካቢኔ መሬትን በተመለከተ በአገሪቱ  ውስጥ ማንም ዜጋ ለማልማት ከሚችለው በላይ መሬት መያዝ እንዳይችልና ለወደፊቱም ከአርሶ አደሮች በስተቀር የእርሻ መሬት ለማንም እንዳይሰጥ ለማድረግ የሚያስችል ህግ እንደሚወጣ አሳወቁ::

### ሚያዝያ 6 ቀን 1966

ቀዳሚው ሃይለ ስላሴ በእንግሊዝ አገር በህክምና ላይ የሚገኙት ልጃቸው አልጋወራሽ መርዕድ አስፋውን ሃይለስላሴን በመተካት በተጠባባቂነት የልጅ ልጃቸው ልዑል ዘርአያዕቆብ እንደሚሆኑ አሳወቁ፡

### ሚያዝያ 9 ቀን 1917

በአዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ አጠራር እንጦጦ የቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሚገኘው የቀድሞ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተመርቆ ተከፈተ::

### ሚያዝያ 2 ቀን 1958

በአምስቱ አመት የፋሺስት ወራር ወቅት የኢጣሊያን ጦር ለፈፀመው ጉዳት ካሳ በከፈለው ገንዘብ የተገነባው የቆቃ የመብራት ሃይል ማመንጫ ጣብያ ግድብ በንጉሰ ነገስቱ ተመርቆ ስራ ጀመረ::

### ሚያዝያ 27 ቀን 1928

የፋሽስት ኢጣልያ ጦር በጄነራል ገዶሊዮን መሪነት አዲስ አበባን በቁጥጥር ስር ማድረጉንና ኢትዮጵያን በሙሉ ቀኝ መያዙን አወጀ::

### ሚያዝያ 27 ቀን 1933

ከአምስት አመታት የአርበኞች በዱር በገደሉ ፍልሚያና ትግል በኋላ አፄ ኃይለስላሴ በእንግሊዝ ጦር እርዳታና በአርበኞች ተጋድሎ በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማቸው የገቡበት የድል ቀን ሆነ::

### ሚያዝያ 27ቀን 1938

የጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት ቀደም ሲል የፋሽስት ኢጣልያ ጦር የራድዮ መገናኛና የሬድዮ ጣብያ በመሆን በአገለገሉ፤ የተበታተኑ አሮጌ ቤቶች ውስጥ ከመላው ኢትዮጰያ የመጡ 26 የመጀመሪያው ተማሪዎችን በአዳሪነት ተቀብሎ በማስተማር ስራ ጀመረ::

### ማያዝያ 2 ቀን 1958

አፄ ቴዎድሮስ ጃማይካን ለመጎብኘት ኪንግስተን ሲገቡ በመቶ ሺዎች የሚቀጠር ህዝብ አደባባይ በመውጣት አቀባበል አደረገላቸው::

### ሚያዝያ 29 ቀን 1957

በሶቪየት ህብረት ባለሙያዎች ድጋፍና እርዳታ የተገነባው የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ ጣብያ የመሰረት ድንጋይ ጣለ::

### ሚያዝያ 9 ቀን 1985

በግንቦት 17 ቀን 1983 ኤርትራን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው ህዝባዊ ግንባር ኤርትራ(ሻዕቢያ) ለሁለት አመታት በጊዜያዊ መንግስትነት ሲያስተዳድራት በነበረችው ኤርትራ ህዝብ ውሳኔ ተካሄደ::
በመላው ኤርትራ በተካሄደው ህዝበ ውሳኔ አብዛኛው የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ተነጥሎ በነፃነት ራሱን ለማስተዳደር መምረጡን አወጀ::



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

# አስከሬን አጃቢው እና ሹም አጃቢው

‹‹በአዲሱ ሚንስትር፤ በወግ አዋቂው፤
ይኼን አስረሽ - ምቺው ብተውት ምነው!?

እዛኛው ክፍል አዝማሪ እያንጎራጎረ ነው:: ጨዋታውን ተከትሎ የጠጪዎች ሳቅ ሲያጅበው ይሰማል:: (ይኼ ነገረኛ! ግጥሙን ከየት እያመጣው ይሆን?)

‹‹እኔ ያንቺ ወዳጅ እኔ ያንቺ አፍቃሪ፤
እያደርኩ ገረጣሁ እንደ ቻይና ሱሪ::››

ይለዋል ደግሞ መሃል መሃል ላይ:: …የመጠጥ ቤቱ ቋሚ ተሰላፊዎች ዋናውን ክፍል ይዘን፣ መለኪያችንን ጨብጠን ቁጭ ብለናል:: ዛሬ የደመወዝ ቀኔ ነው:: ‹‹የአስከሬን አጃቢው የደመወዝ ቀን ዛሬ ነው›› ብሎ ማን እንደለፈፈ እንጃ ሰዉ ሁሉ አሰፍስፎ እየጠበቀኝ ነው::

እፍረት ጠፍቷል ጎበዝ:: አዎ! ዘንድሮ እፍረት ጠፍቷል:: ገና ለገና በዚህ ዘመን የረከሰው ሞት ብቻ ነው ተብሎ ብዙ ወዳጆቼ ጥሩ ደመወዝ እምበላ ይመስላቸዋል:: እውነቱ ግን እንደሱ አይደለም:: “‹አገርህ በለፀገች› ቢሉት እኔ የት ሄጄ?” እንዳለው ለምኖ አዳሪ ነው ኑሮዬ:: …በደንብ እንተዋወቅ፤ አስከሬን አጃቢ ነኝ፤ በአንድ ቀብር አስፈፃሚ ውስጥ ተቀጥሬ የዕለት ጉርሴን የማገኝ አስከሬን አጃቢ::

ዛሬ እዚህ መጠጥ ቤት የተገኘው አብዛኛው ሰው የእኔን ግብዣ ይጠብቃል:: እህ! የደመወዝ ቀን ነዋ! የእኔን የደመወዝ መቀበያ ዕለት ከእኔ በላይ የሚያውቋት እነሱ ናቸው:: ሹም አጃቢውም ጭምር::

ለነገሩ ከሹም አጃቢው ጋር ፀብ ነን:: ጥሎበት አይወደኝም:: እሱ የሚመካበትን ሙያ ያህል እኔም ሥራዬን በመውደዴ በጣም ይበሳጫል:: ኤዲያ! አጃቢነት ግን ምኑ ይወደዳል!? (…እንዳይሰማኝ)

‹‹ፓርላማ እንደገባ ባለጊዜ ሹም፤
አትጋደሚብኝ እየሔድሽ የትም::››

ይሄ አዝማሪ ጠጪዉን በሳቅ እየገደለው ነው::

‹‹በተሠራው መንገድ ገንዘብ በወጣበት፤
ሳይፈራርስ ቶሎ ልመላለስበት::››

ሆ! …ባለፈው አንድ አምስት መለኪያ ሳይሉት ጋበዘኝ፤ ማን? ሹም አጃቢው:: እኔም ከሹም ጋር የሚውል የትልቅ ሰው ግብዣ አይናቅም ብዬ ስጨልጥ፣ ስጨልጥ፣ ስጨልጥ… የማይቀረው ስካር መጣ:: ደሜ ሲሞቅ ድንገት በመሃል ተምዘግዝጌ ተነሳሁና፣ ‹‹አመሠግናለሁ የሥራ ባልደረባዬ!›› አልኩት:: …ቤቱ በሳቅ አውካካ:: ሹም አጃቢውን ማሳዘን የፈለገ ሁሉ አውቆ ሳቁን አረዘመው:: …ይባስ ብለው፣ ‹‹ሬሳ አጃቢው ሹም አጃቢውን የሥራ ባልደረባዬ አለው!›› ተባብለው ለሦስት ለአራት ቀን ሳቅ መፍጠሪያ አደረጉኝ:: ሹም አጃቢው በዚህ ንግግሬ ሆዱ ሻከረ::

‹‹ባሏን ማሳዘን ያማራት ሚስት ዘይት ደፋች!›› ሲል አንድ ጠጪ ተረተብኝ::

‹‹እግዚኦ! በዚህ ጊዜ!?›› ስብርብር ያለ የሰካራም ድምፅ ተረቱን አጋነነው:: የተረቱ መልዕክት ልቤ ደረሰ:: ሹም አጃቢው እግር ስር ሔጄ ድፍት ማለት አማረኝ:: ሕዝብ በአስቸኳይ አዋጅ በታሰረበት በዚህ አጉል ጊዜ ሹም አጃቢውን መዳፈሬ አግባብ አልነበረም::

ድንገት ሲሔድ ያለው ሹም አጃቢ ቁጭ ብሎ ሌላ መጠጥ አዘዘ:: …ብስጭቱ ጥቂት መለስ ያለለት ስለመሰለኝ ደስ አለኝ:: ወዲያው አስታራቂ በመሃላችን ገባ:: ‹‹ሬሳ አጃቢውም ተው፤ ሹም አጃቢውም ተው!›› ተባልን:: እኔም ተውኩት:: ሹም አጃቢውም የተወ መሰለ::

እነሆ በግልግል ጠቡ በርዶ ዛሬ ላይ ደርሷል:: እሱም ማዶ ጥግ ላይ ተቀምጦ የእኔን ግብዣ እየተጠባበቀ ነው፤ …ይገርማል::

‹‹ቅሪብኝ፤ የኔ ዓለም፤ የኔ ዓለም ቅሪብኝ፤
ደካማው አባቴን መንግሥቴን ጧሪ ነኝ!››

ከወዲያኛው ክፍል የሚሰማው የአዝማሪ ጨዋታ ቀጥሏል:: አዝማሪው ከብሶት ጋር የተሰፋ ይመስል አሁንም እዚያው ላይ ነው::

‹‹አቶ መንግሥቴን ደካማ ያደረገው ማን ነው?›› አለ አንድ ነገረኛ ጠጪ የአዝማሪውን ግጥም መነሻ አድርጎ:: ያለቅጥ ሰዉ አውካካ፤ ጓዳው ተተራመሰ:: የአዝማሪው ጨዋታ በሽልማት ብዛት ተደነቃቀፈ:: እዚህ እኛ ቁጭ ብለን፣ የጓዳውን ጨዋታ እያዳመጥን በመጠጣት ላይ ነን::

አጨበጨብኩ፤ ‹‹ከዛ መልስ የሚፈልጉትን ድገሚያቸው!›› አልኩ ድንበሬን ሹም አጃቢውን አድርጌ:: ቁልሌ (‹‹ቁልሌ›› የአስተናጋጃችን ስም ሲሆን፣ መቀመጫዋ ትልቅ ስለሆነ የወጣላት ስም ነው) መቀመጫዋን ከወዲያ ወዲህ እያማታች መታዘዝ ጀመረች::

‹‹የሹመኛ ሌባ ይባላል ሙሰኛ፤
ፍቅርሽ መትቶ ጣለኝ ልክ እንደ መጋኛ::››

ከዚህ ጨዋታ በኋላ እኔም ባዝማሪው በኩል ሹሙን በደንብ ለመታረቅ መላ መታሁ:: ‹‹ማነህ አዝማሪ! ኧረ አዝማሪ!›› ጮኽ ብዬ እየተጣራሁ ነው:: እሱ ሽቀላ ላይ ስለሆነ በምን ጆሮው ሰምቶኝ!? …ተበሳጨሁ::

‹‹ክረምቱ ከገባ አይሠራም ፍርድ ቤት፤
ያንቺን በደለኛ ለማን ልበል አቤት!?

ይኼ አዝማሪ ነገር ሊያመጣ ነው:: እንጀራውን የሚጋግረው እንዲህ ባለ የአመፃ እንጉርጉሮ ብቻ መሆኑ አናደደኝ:: (አይ ፖለቲካ እንዲህ እንጀራ መብያ ሆነሽ ትቀሪ!?)

‹‹አንተ አዝማሪ ና ወዲህ!›› እጄን ወደ ደረት ኪሴ እየሰደድኩ ተጣራሁ:: ፀበኛ ግጥሙን ጥሎት ወደ እኔ መጣ:: …ህም! መቼም የዘመኑ ጨዋታ ይኸው ነው:: እጅ እጅን ማየት፤ ‹‹ና ወዲህ!›› ሲባሉ መምጣት::

አዝማሪው ወደኔ እየመጣ ሳለ የቁልሌ መቀመጫ አንዳች ቁልል መስሎ በአፍጫው ስር እልፍ አለ፤ ሥጋ ደካማ አይደል፣ ቆም አለና ማሲንቆውን እየገዘገዘ አንጎራጎረለት::

‹‹ደግሞ መጣሽብኝ፤ ደግሞ መጣሽብኝ፤
የልጆቼን እናት ልታባርሪብኝ!››

…አለ:: ሰዉ ሳቀ:: ሹም አጃቢውም ጭምር:: በዚች ቀዳዳ ተጠቅሜ የእርቅ ደብዳቤዬን በግጥም መልክ ለማሰማት፤ ‹‹ተቀበል!›› አልኩ:: ተቀበል!

‹‹ገዳዬዋ ነይ ነይ!›› አለ አዝማሪው የማሲንቆውን ቅኝት እያበጀ::

‹‹ገዳዩንም ሟቹንም ከበር ወዲያ ተወውና ይልቅስ ተቀበለኝ!›› አልኩት ለብልሃቴ እጄን ከደረት ኪሴ ሳላነሳ::

‹‹ገዳዬዋ ነይ ነይ!›› አለ አመል ሆኖበት::

‹‹አይ አንተ! ገዳይ ባይኖር ኖሮ ምን ትበላ ይሆን!?›› ወረፍኩት:: የቤቱ ሰው በሙሉ ሳቀ::

‹‹እሺ ቀጥል!›› አለ በሚገዘግዘው ማሲንቆ መሃል በአፀፋው ተበሳጭቶ::

‹‹እኔም አጃቢ ነኝ፤ አንተም ነህ አጃቢ› በል!››

‹‹ገዳዬዋ ነይ! ነይ!›› አዝማሪው ግጥሜን ተጠይፎት ሊያስቀይሰኝ ሞከረ፤ …ተቆጣሁ::

‹‹በሰላም አገር የምን ገዳዬዋ ነይ ነይ ነው? አርፈህ ተቀበል አንተ! …የእርቅ ግጥም ነው!›› አልኩት ግጥሙ እንዳይጠፋኝ እየተቻኮልኩ::

‹‹እሺ!›› አለ::

‹‹እኔም አጃቢ ነኝ፤ አንተም ነህ አጃቢ፤› በል!››

‹‹እኔም አጃቢ ነኝ፤ አንተም ነህ አጃቢ፤››
ያንተ ባለሱፍ ነው፤ የእኔ ባለጋቢ::››

አዝማሪው ገና ግጥሜን ተቀብሎ ከማውረዱ ሰዉ በሳቅ ተጫረሰ:: ቤቱ ባንድ እግሩ ቆመ::

‹‹ጃኖ ስለለበሱት ሹም ማለቱ እኮ ነው›› አለ አንድ ነገረኛ ወደ እኔ እያየ::

ደነገጥኩ:: ነገሩ ወዴት እየኼደ ነው? ጃኖ እና ጋቢን ምን አገናኘው? …ሹም አጃቢው በብስጭት የሚያደርገውን አሳጣው:: ወደኔ እየተንደረደረ መጣ:: ቤቱ ተተራመሰ:: ለሁለት ሰው ጠብ ሺህ ገላጋይ መሃል ገባ:: ‹‹ሬሳ አጃቢው ከሹም አጃቢው ጋር ተጋደሉ!›› ተባለ::

‹‹ሁለቱም አንድ ዓይነት ሥራ ነው የሚሠሩት አሁን ምን አጣላቸው!?›› ተባልን:: ጥቂት ቆየት ብሎ እንደ ሁልጊዜው ጠቡ በግልግል በረደ::

‹‹እንደ ፓርላማ አባል እንቅልፍ ወዳድ ናት፤
ድንገት ትነቃለች እሺ ለማለት::››

አዝማሪው ጨዋታውን ቀጥሏል:: የእኔ ተጋባዦችም ያለሐሳብ እየጠጡ ነው:: የጠላት ገንዘብ ይመስል እያንደቀደቁት ነው:: …

‹‹ስማ ሬሳ አጃቢው!›› አለኝ ሹም አጃቢው አንድ ሦስቱን መለኪያ ካጎደለ በኋላ::

‹‹አቤት አለቃዬ!›› አልኩ አሁን እንኳን ልብ ለመግዛት እየጣርኩ::

‹‹እስከዛሬ ስንት ሬሳ አጅበሃል!?››

ዐይኔን ወደ ጣራው ተክዬ ጥቂት አሰብኩ:: ቀስ በቀስ የሰዎች ሳቅ ሲከተል ግን ከየት መጣ ሳይባል ሞቅታ ያመጣው ብስጭት ውስጤን ናጠው:: …ለካ ይሄ ሰውዬ የጠየቀኝ ለቤቱ ሊያስቅብኝ ኑሯል፤ ተበሳጨሁ::

‹‹እየሰማኸኝ ነው?›› አለኝ ደግሞ::

‹‹አቤት!›› አልኩት::

‹‹እስከ ዛሬ ስንት ሬሳ አጅበሃል!?››

‹‹የፈለገ ቢበዛ አንተ ከምታጅባቸው አይበልጡም!››

‹‹በለው!›› አለ አንድ ጠጪ በማጋነን ዓይነት ጮኽ ብሎ፤ ‹‹በለው! ሹሞቹን ከሙታን ደባለቃቸው!››

ፀባችን እንደ አዲስ ተቀሰቀሰ:: እንደተለመደው ገላጋይ መሃል አድርገን ጥቂት ተወናቸርን:: እህ! ኧረ እንደው ምን ይሻለናል!?

# የአዲስ አበባ መንግሥት ከተማዋን ያውቃታልን?



ሁሴን ከድር



ዓምድይሁን ሁላላ ይባላል:: (ለባለ ታሪኩ ነፃነት ሲባል ስምና አድራሻው የተቀየረ) በኮልፌ አጠና ተራ አካባቢ የታጠቡና ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰልባጅ ልብሶችን በመተኮስ ይተዳደራል:: አዲስ አበባ ከመጣ ጥቂት ዓመታትን አስቆጥሯል:: በሕይወት መንገድ ላይ በርካታ አስቸጋሪ ጋሬጣዎችን አልፎ ነው አሁን በአንጻራዊ መልኩ የተረጋጋ ሕይወትን መምራት የጀመረው:: ዓምድይሁን የትውልድ አገሩን ዞር ብሎ ማስታወስ አይፈልግም:: አባቱን በልጅነቱ እናቱን ደግሞ የ8ኛ ክፍል ተማሪ እያለ ነው በበሽታና ማሰብን በሚያስመርር ችግር ያጣው:: ወንድሙ በደምቢዶሎ አንድ የሸቀጥ ሱቅ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሲሆን እህቱ ተድራ አላባ ቁሊቶ ከገባች ወዲህ አንድም ቀን ወደ ቤተሰቦቿ ፊቷን አዙራ አታውቅም::

በእህት ወንድሞቹ የተማረረው አምድይሁን የተወለደበትን አዳዘር ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ዳግም ላለማየት ‹‹ድንጋይ ወርውሬ ነው የወጣሁት›› ይላል:: አሁን ያለበትን ሕይወት ከገጠሩ ኑሮ አንጻር ሲያስተያየው የምድርና የሰማይ ያህል ይራራቁበታል:: አዲስ አበባ ጾሙን ብታውለው ጾም አታሳድረውም:: ቁርሱን ቢቸገር ለምሳው አያጣም:: ከጓደኞቹ ጋ አስኮ አካባቢ ለአምስት በተከራዩት ቤት አድሮ ሲኖረው በአውቶብስ ሲቸገር በእግሩ ወደ ሥራው ያዘግማል::

ከአያት ቅድመ አያቶቹ የወረሰው የገጠር መሬትና ቤት ወራሽ በማጣት ውድማ ሆኗል:: በየዓመቱ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር ፣ባቄላ.... እየተዘራ ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግሮ የነበረ መሬት ወራሽ ገበሬ በማጣት ስንደዶ ይበቅልበት ጀምሯል:: ያ በወላጆቹና መንደርተኞቹ ሞቆ የነበረው ቀዬ ዛሬ ጭርታ ወርሶታል:: የእናቱ የእንሰት ማሳ ተነቃቅሎ ሴጣውን ቀርቷል:: በእንጨት አጥር ተከልሎ የነበረው ግቢያቸው ሰው የማይኖርበት ጋጥ መስሏል:: ከአባቱ መሬት እንዴት እንደተለየ ሲናገር፡-

‹‹ለተወሰነ ጊዜ አጎቴ ዓመታዊ የመንግሥት ግብር እየከፈሉ፣ የማዳበርያ እዳ እየገፈገፉ ቆዩ:: መሬቷ የሰጠችን ጸጋ ሲሟጠጥ፣ ወላጆቼ አፍርተውት የነበረ ሃብት ሲሸረሸር አጎቴ ትርፍ ለጋራ ለመጠቀም መሬቱን አከራየው:: ተከራዮቹ ግን ቀርከሃ እየሰበሩ፣ባልተከሉት ባሕር ዛፍ ማውደም ሲጀምሩ አጎቴ ተናድዶ አባረራቸው:: ...እሱ ከሞተ በኂላ መሬቱ ተንከባካቢ አጣ:: እኔን የተለያዩ ሰዎች ቢለምኑኝም አንዴ ገጠሩን ስለጠላሁት ዞር ብዬ ማየትም አልፈለግኩም:: እዚያ ሃብታም ከምሆን አዲስ አበባ ጎዳና ተዳዳሪ ብሆን ይሻለኛል››.....

ወርቁ ዱላም ከአምድይሁን ጋ ተመሳሳይ ታሪክ አለው:: ገጠር የነበረውን ሃብት ንብረታቸውን ትተው ወላጆቹ ከተማ የገቡት ከ10 ዓመታት በፊት ነበር:: የወርቁ ቤተሰቦች በንግድ ሥራ መተዳደር ጀምረው ሕይወት ስለ ሰመረላቸው የገጠሩን መሬትና ንብረት ለሌላ አካባቢ ተወላጅ ያከራያሉ:: ተከራዮቹ በቋንቋም ፣በሃይማኖትም ከአካባቢው ነዋሪዎች የተለዩ በመሆናቸው ዘመዶቻቸውን ከሃገራቸው ጠርተው በማስመጣት የሌላ ሰው መሬት በተመሳሳይ እንዲከራዩ አደረጉ:: ከጥቂት ዓመታት በኂላ ከቀዬው ሰው ባልተናነሰ በዝተው ታዩ::

የአካባቢው ማኅበረሰብ በየጊዜው ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከሚያደርገው ፍልሰት ያልተናነሰ ከሌላ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች መንደሩን ይቆጣጠሩት ጀመር:: ሁኔታው ያላማረው የሃገሬው ነዋሪ ‹‹መሬታችን በሌሎች ዘሮች ሊወሰድብን ነው›› በሚል ፍራቻ በከተማ የተደላደሉትን የወርቁ ቤተሰቦችንና ሌሎች አከራዮችንም በመጥራት ሰዎቹን እንዲያስለቅቁ ይነግሯቸዋል:: አዲስ መጤዎቹ

ግን የሚበገሩ አልሆኑም:: በሰላማዊ መንገድ ቀርቶ በጉልበትም ሊበገሩ አልቻሉም::.....

እንደ ዓምድይሁንና ወርቁ ዱላ ዓይነት ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው እርስታቸውን ትተው አዲስ አበባ ገብተው የውሃ ሽታ የሆኑ በርካታ ሰዎች አሉ::

አዲስ አበባ በተለያዩ በሮቿ ገብተው የተደላደሉባት ነዋሪዎች አብዛኞቹ ተመሳሳይ የችግርን ሽሽት ተረክ ያሰማሉ:: የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ለጽሑፉ ማደራጃ ካለፉት አሥር ዓመታት ወዲህ በገፍ ወደ ከተማዋ የገቡ ፍልሰተኞችን ለማነጋገር ሞክሯል:: በደቡብ በርም 200 ኪሎ ሜትር በአጋጣሚ በመሄድ የገጠሩን ሁኔታና በራቸውን ዘግተው አዲስ አበባ የመጡ ሰዎች ታሪክን ሰምቷል፤ በዓይኑም ተመልክቷል::

## ፍልሰት ወደ ከተማ

በመሬት ጥበት፣ በተለያዩ ችግሮች ወደ አዲስ አበባ የሚገቡ ፍልሰተኞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅጉን ጨምሯል:: አማላይ የከተማ ወሬዎች፣ የገጠር መልከዓምድርን በተደጋጋሚ በማየት መሰላቸት፣ በከተማ መጠጊያን ማግኘት፤ ሰዎች የትውልድ አካባቢያቸውን ጠልተው ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች መካከል የተወሰኑት ናቸው:: ከሁሉም የከፋው ግን ድህነት አስመርሯቸው የቤተሰብ ይሁኝታ ሳያገኙ በመኪና ተንጠላጥለው አዲስ አበባ በመግባት ጎዳና የሚኖሩ ወጣቶች ሕይወት ነው:: የከተማዋን መግባቢያ ቋንቋ እንኳ የማያውቁ ከመሰሎቻቸው ጋ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ታዳጊዎችና ወጣቶች አሉ:: በሂደት ከተሜውን ለመምሰል የሚጥሩ::

አዲስ አበባ ተቆጣጣሪ ያላት ከተማ ባለመሆኗ በሁሉም የከተማዋ በር የገቡ ፍልሰተኞች ገንዘብ ባይኖራችውም፣መታወቂያ ሳያስፈልጋቸው እንደነገሩ መኖር ይጀምራሉ:: ቀስ በቀስም ዓይናቸውን በመግለጥ ፣መሰሎቻቸውን በመቀላቀል የሕይወት መስመራቸውን አወላግደውም ቢሆን መሳል ይጀምራሉ::

የአፍሪካ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ በቂ የመጸዳጃ አገልግሎት መስጫ ባይኖራትም፣ የችግረኞች መቀለቢያ ጣቢያ ባታዘጋጅም፣ለተቸገሩ ማደርያ ዳስ ባትጥልም፤ በማታውቃቸው በሚናፍቋት እንግዶቿ ትወረራለች:: ወረራውን የሚከላከልላት አሊያም በሰላማዊ መንገድ አስገብቶ የሚያስተናግድላት አስተዳደር ከተማዋ ማፍራት አልቻለችም::

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ከ30ዓመት በፊት የመጀመርያ ደረጃ ተማሪ ሆኖ ከተማዋን ሲያውቃት፡- የቀበሌ መታወቂያ ሳይኖረው የሚንቀሳቀስ በድንገት ከተያዘ ለእስር የሚዳረግባት ብሎም ለውትድርና የሚታፈስባት፣ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርጉ የመንግሥት ሰዎች ድንገት ሊከሰቱ ይችላሉ በሚል በፍርሃት በጥንቃቄ የሚኖርባት፣ የሕዝብ ብዛት አሁን ካለው በሁለት እጥፍ የሚያንስባት፣ የአንድ ቀበሌ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የሚተዋወቁባት ከተማ ነበረች::

ዛሬ የከተማዋ መንግሥት ከየወረዳው የሚቀርብለትን ሪፖርት እንጂ ከተማዋን በቅጡና በምልኣት ስለማወቁ እጅጉን ያጠራጥራል:: በከተማዋ ምን ያህል ሰዎች በትክክል እንደሚኖሩ፣ ለምን ያህሉ መጸዳጃ ቤት እንዳላቸው፣ ምን ያህሉ በቀበሌ ቤት እንደሚኖሩ ምን ያህሉ የግል ቤት እንዳላቸው፣ ምን ያህል ወጣት ፣አዛውንት ፣በሥራ ላይ የተሰማራ፣ሥራ አጥ መሆናቸውን ያውቃል ለማለት ይቸግራል:: የአዲስ አበባን መሬት በካርታ እንጂ በቦታ ስለማወቁም ያጠራጥራል:: ዋናና ንዑስ መንገዶች፣ ቋሚና ጊዜያዊ ነዋሪዎች በአዲስ አበባ ተለይተው አይታወቁም:: የከተማዋ መንግሥት ከከተማዋ ጋ አብሮ ያደገ ባለመሆኑ በሥራው ውጤት ሳይሆን በመንግሥት ባለው ታማኝነት የሚሾም በመሆኑ ከተማዋ ብታድግ ባታድግ ደንታም የሚሰጠው አይመስልም::

እምዬ ምኒልክ እና እትጌ ጣይቱ ከተማዋን ከቆረቆርዋት ከ1878 ወዲህ አዲስ አበባ ኢትዮጵያን የሚመራ ባላሥልጣን እንኳ ያፈራችው አንድ ኮሌኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ብቻ ነው:: በሀገሪቱ ርዕሰ መዲና የሚቀመጡ የሃገሪቱ መሪዎች ከወሎ (ልጅ እያሱ)፣ ከሐረር (አፄ ኃይለሥላሴ)፣ ከመቀሌ (መለስ ዜናዊ) ከወላይታ (ኃይለማርያም)፣ ከጂማ (አብይ አህመድ) ሲመጡ ብቸኛው የከተማዋ ተወላጅና የሀገሪቱ መሪ ሆነው የነበሩት መንግሥቱ ኃይለማርያም ናቸው:: ከተማዋ ላፈራቻቸው ልጆቿ ሳይሆን ለምትፈራቸው መሪዎች ነው ምቾትን የምትሰጠው::

የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን ሳታመቻች ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠረች፣ ዓመታትን መቁጠር እንጂ ዘመናዊነት ለመላበስ አሳሯን የምታይ፣ ነዋሪዎቿ የሌሎች አዳዲስ ከተሞች ነዋሪዎች በሰለጠኑበት የመንገድ አጠቃቀም እንኳ መሰልጠን የተሳናቸው፣ የጋማ እንስሳት ከሰዎች እኩል መጓዝ ባቆሙበት ማግሥት ሰዎች ከአውቶሞቢሎች በመሃል መንገድ እየተጋፉ የሚሄዱባት፣ ለላንቲካ የተቀመጡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ታኒካዎች፣ገረወይና፣ ቅርጫቶች ቢሰለፉም ቆሻሻ ከባቸው ባዷቸውን የሚታይባት ኋላ ቀር ከተማ ነች::

አዲስ አበባ ጥቂት ሕንፃዎችን ብታበቅልም በቂ የመኪና መንገድና የሰዎች መጓጓዣ መሥራት የተሳናት ንዑስ ከተማ ናት:: ሰውነቱ ተወጣጥሮ የለበሰው ጨርቅ እንደሚተረተርበት ወፍራም ሰው፤ ሞልቶ በተትረፈረፈው ነዋሪዎቿ ምሬት የተሰላቸች መዲና ናት:: በትራንስፖርት ችግር የሚማረሩ ሠራተኞች፣ በንጹሕ ውሃ አቅርቦት የሚታመሙ ታዳጊዎች፣ ለራሳቸው ብቻ በሚያስቡ ከንቱ ዜጎች፣ማደርያ አጥ ምንዱባኖች፣ ጮሆ አዳሪ መከረኞች መለየዋ ሆኗል የአዲስ አበባ::

ታዳጊዎች የጨዋታ አምሮታቸውን መወጫ ሜዳዎችን ከማመቻቸት ይልቅ የቀደሙት የከተማዋ መንግሥታት አመቻችተውት የነበሩትን ሜዳዎች ወደ ገንዘብ መለወጥ ዓይነተኛ ሥራው ሆኗል የከተማዋ መንግሥት:: ለአዲስ አበባ መንግሥት ፎቅ መትከል የሥልጣኔ መሠረት ነው የሚመሥለው:: በመልሶ ማልማት የፈረሱ ቦታዎች ወደ ቀድሞ ጫካነታቸው እንዲለወጡ የተፈለጉም መሥለዋል:: ከተማዋን ጤነኛ ሰው የሚመራትም አትመስልም:: በእርግጥ የከተማዋ መንግሥት ብቻም ሳይሆን የፌዴራል መንግሥቱም በዚህ ረገድ ተጠያቂ ነው:: ቤቶች ሲፈርሱ በምን ያህል ቀን ልዩነት ሊሰሩ እንደሚችሉ ቀድሞ አይተልምም:: በአንድ በኩል የፈረሱ ሰፈሮች በሌላ በኩል የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች፣ በአንዱ የተተረማመሰ መንገድ፣ በሌላው ለእግረኞች ያልተዘጋጁ መንገዶች ከመኪኖች ጋ ሲጋፉ፣ በሌላው ደግሞ ከመጠን ያለፈ ሕዝብ..... በአጠቃላይ ትርምምስምሱ የወጣ ሁኔታ ነው የምንታዘበው::

የከተማዋ መንግሥት በቴሌቪዥን መስኮት በቀረበ ቁጥር የአሃዝ ስሌትና የመላምት ሪፖርት ከማቅረብ ታቅቦ፤ ትክክለኛውን የከተማዋን ገጽታ አሳይቶ ‹‹እኔም እንደ ኃይለማርያም በብቃት ማነስና በስንኩል አመራር ከዚህ በላይ መቀጠል አልችልም ተረከቡኝ›› ብሎ የሚደፍረው መቼ ይሆን?

## እንደ መውጫ

የከተማዋ መንግሥት በቅድሚያ የከተማዋን ችግሮች በነዋሪው ጠቋሚነትም ሆነ በባለሙያዎች በማስጠናት ዘርዝሮ መመዝገብ:: ችግሩን አያውቀውም ለማለት ሳይሆን ለመፍትሄውም ከማኅበረሰቡ ጋ ተመካክሮ መሆኑ ለተግባራዊነቱ ሊተጋገዝ ይችላልና:: በጫት ገራባዎች የሚደፈኑ ትቦዎች ክረምት በመጣ ቁጥር የከተማዋ ወሳኝ ቦታዎችን ጭምር ስለሚያጥለቀልቁ ከፍተኛ በጀት ተመድቦ የፍሳሽ ማስወገጃ ትቦዎችን ማጽዳት፣ ዳግም ወደነዚህ ትቦዎች ደረቅ ቆሻሻ እንዳይጣል በድራማ ብቻ ያልተወሰነ አስተምህሮ ማድረግ:: በክረምት የሚፈነዱ መጸዳጃ ቤቶችን ታውቆ ይሁን ወይም በችግር ለይቶ ዘላቂ መፍትሄ ማበጀት:: ሕዝብን እንደ አጥፊና እንቅፋት ቆጥሮ ከመግፋት እንደ የእድገት አጋር አድርጎ ማቅረብ ተገቢ ነው::

የመንገድ ላይ ንግዶች የከተማዋን ጤና አቃዋሽ በመሆናቸው ነጋዴዎቹን በዱላ ከማባረር ይልቅ፣ ንብረታቸውን በፖሊስ ከማስወሰድ የተሻለ ስልትን መከተል:: በሻጮቹ ላይ ሳይሆን ሕገ ወጥ ንግድን በሚያበረታቱ ሸማቾች ላይ ቅጣት መውሰዱ ንግዱን ሊያስቆመው ይችላል:: ግን ደግሞ ቀላልና ሁለቱንም ወገን ሊያስማማ የሚችል መፍትሄ ተፈልጎ ቢሆን መልካም ነው:: የፈረሱ መንደሮችን በአስቸኳይ ቀድሞ ወደታሰበው ሥራ እንዲገቡ ቢሮክራሲያዊ ማጓተቶችን አስቀርቶ ለባለሃብቶቹ ማመቻቸት:: አንድ አካባቢ ከመፍረሱ በፊት ከነዋሪው ጋር በእብሪት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ውይይት ማድረጉ የአካባቢው መፍረስና ለተሻለ አገልግሎት መልሶ መገንባቱን አስረግጦ ማሳመን:: ሰዎች ከኖሩበት አካባቢ በእልህና በጉልበት መውጣትን አይፈልጉም፤ ከቦታው ሲነሱ በምትኩ የተሻሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የከተማዋ መንግሥት ግዴታም ጭምር ነው መሆን ያለበት::

ከተማዋን ዘመናዊ ማድረግ የሚቻለው ፎቆችን በመትከል ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብን ማስወገድ፣ ከተማዋ የመዝናኛ መናፈሻዎች፣ የስፖርት ማዘውተርያ ትላልቅ ጂሞች፣ የመዋኛ ገንዳዎች፣ አዳራሾች፣ የኳስ ሜዳዎች፣ ሰፋፊ ቤተ-መጽሐፍት፣ የሕጻናት መጫወቻ ሥፍራዎች፣የሜዳ ቴኒስ፣ የቅርጫት ኳስ መጫወቻ ሜዳዎች፣ የወጣቶች መዝናኛ ቦታዎች፣ የንግድ ማእከላት .... ያስፈልጋሉና ከፎቅ ባሻገር ባለሃብቶች ፕሮጀክቶችን አቅርበው ቦታ መፍቀዱ የተሻለ ነው:: በአጭር ጊዜ ፎቅ ሰርቶ ፎቁን እያከራየ በኪራዩ ገንዘብ ሌላ ፎቅ መሥራት ማሰብን ማስቀረት ያስፈልጋል::

ወደ ከተማዋ የሚደረጉ ፍልሰቶችን መቆጣጠር ወይም ሥርዓት ባለው መንገድ ማስኬድ ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት:: ከተማዋን ባለቤት አጥ ከሚያስብሉ ሁኔታዎች አንዱ ይሄ ነው:: በከተማዋ አደጋ ባንዣበበ ቁጥር በየበሮቹ ጥብቅ ፍተሻ ማድረግን ብቻ እንደ መፍትሄ ከመውሰድ ባሻገር የከተማዋን ነዋሪ በቀበሌም ሆነ በወረዳ ጠንቅቆ ማወቅ፣ የቀበሌ አመራሮች የፖለቲካ ታማኝ የሆኑ ካድሬዎችን ከመሰብሰብ ይልቅ ሙያተኞችን በየወንበሩ ላይ በማስቀመጥ የምር ለከተማዋ አስቦ መሥራት ለነገ የሚባል ተግባር አይደለም::

ይህ የባለሙያ ሃሳብ ሳይሆን የአንድ ተቆርቋሪ ዜጋ፣ ከተማዋን ለማዘመንና ከዓለም ከተሞች ተወዳዳሪ ለማድረግ ከሚያስብ አንድ ዜጋ የቀረበ ትሁት ወይም የቁጭት ሃሳብ ነው::

ቸር እንሰንብት

# “ህወሓት አሠረን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈታን”

## *አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት*



*አባ ገብረየሱስ ኪዳነ ማሪያምና አባ ገብረስላሴ ወልደኃይማኖት ገብረመድህን የዋልድባ ገዳም መነኮሳቶች ናቸው:: በአካባቢው መንግስት ‹‹ልማት ለማካሄድ›› በሚል ሰበብ የጀመረውን እንቅስቃሴ መላው መነኮሳት ሲቃወሙ አብረው ነበሩ::*

*የቅዱሳኑ አፅም ሲታረስ ያወገዙት መነኮሳት በፀጥታ ሃይሎች ተይዘው አንድ አመት ከሶስት ወራት በእስር አሳልፈዋል:: በእስር ጊዜያቸው ለበርካታ ቀናት በውድቅት ለሊት እየተጠሩ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገርፈዋል:: በእስረኞች ፊት ተደብድበዋል፣ ተሰድበዋል::*

*መነኮሳቱ ‹‹ይህ ገዳም የህዝበ ክርስቲያኑ መገልገያ ነው፤ የምትቆፍሩት ቦታም የቅዱሳን አፅም ያረፈበት ስለሆነ የቤተ ክርስትያን ህግና መብት ሊከበር ይገባል›› በማለታቸው ይህንን ሁሉ ግፍና መከራ ሲቀበሉ ጉዳዩ የሚመለከታት ቤተ ክርስቲያን ዝምታን መምረጧ ለምን ይሆን?... በህዝብ ግፊት ክሳቸው ተቀርጦ እንዲፈቱ የተደረጉት ሁለቱ መነኮሳት በተቀዳደደ የመነኩሴ ልብስ ከአመት በላይ የቆዩበት የእስር ህይወት ምን ይመስላል? በሚሉና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ የግዮን ጋዜጠኞች ፍቃዱ ማ/ወርቅና ሮቤል ምትኩ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረዋቸዋል::*

**ግዮን፡- እናንተን ለእስር የዳረጋችሁ የዋልድባ ጉዳይ መነሻ ውዝግቡ ምን እንደነበር ወደኋላ መለስ ብለው ቢያጫውቱን?**

አባ ገብረየሱስ፡- እንግዲህ የወልቃይት ስኳር ፕሮጀክት በሚል ሰበብ የዋልድባ ገዳም ቦታን ለልማት እናውላለን በሚሉ ሰአት ማህበረ መነኮሳት ደግሞ የአባቶች አፅመ ቅዱሳን ያረፈበት፣ ስብሃተ እግዚአብሄር የሚፈፀምበት ስለሆነ ይህ ቦታ ለልማት መዋል አይችልም የሚል ነው መነሻው::

ይህንን ተቃውሞ ወደ ሚመለከተው አካል ለማቅረብ ከሶስቱ ገዳማት የተውጣጡና የተወከልን መነኮሳት በሰአቱ ለነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በስማቸው የተፃፈ ደብዳቤ ለማቅረብ በምንቀሳቀስበት ወቅት ነው ውዝግቡ የተካረረው:: ከዛ በፊት ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም አዲስ አበባ ሜጋ ህንፃ ላይ የሚገኘው የወይዘሮ አዜብ መስፍን ቢሮ በመሄድ ስድስት መነኮሳት ጉዳዩን አሳውቀናል:: ምንም መልስ አላገኘንበትም፤ በወቅቱ የሆነ የውጭ አገራት መሪዎች የሚሳተፉበት ስብሰባ እየተዘጋጀ ስለሆነ ባለቤታቸውንም ማግኘት እንደማንችል ተነግሮን ተመለስን::

ግን በየጊዜው ነገሩ እያስቸገረንና እየገፋ ሲመጣ 2004 ዓ.ም ጥር 16 ቀን ያዘጋጀነውን ደብዳቤ ይዘን ጠቅላይ ማኒስትሩ ቢሮ ተገኘን:: በጊዜው ያነጋገረን ፀሃፊው ሲሆን የመለሰልን መልስ “ለእናንተ ምትክ ቦታ ይሰጣችኋል እንጂ የሚለማ ከሆነ መቃወም አትችሉም” ማመልከት ያለባችሁም ለክልሉ እንጂ ወደ እኛ ጋር መምጣት አልነበረባችሁም የሚል ነበር:: እኛም በምላሹ አዝነን ወደ ገዳማችን ተመልሰናል::

ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ ለአቡነ ጳውሎስ ግልባጭ ደብዳቤውን ይዘን ስንመጣ ልዩ ፅ/ቤት እንደደረሰን መግባት አልቻልንም:: መግባት ስላልቻልን ያንን ደብዳቤ ለልዩ ፅ/ቤት አስረክበን ተመልሰናል:: ከዛ በኋላ ነገሩ እየተጋጋለ ሲሄድ፣ እነ አሜሪካ ድምፅ የአማርኛው ፕሮግራም አጠቃላይ ዝርዝር ሂደቱን ሲያስተላለፉ ፣የዋልድባ ጉዳይ በህዝበ ክርስትያኑ ዘንድ ተደማጭነት አገኘ:: ትኩረቱ ወደ ቤተ ክህነቱ ሲዞርና ህዝቡና ቤተክህነት ሲጋጩ በመንግስት አካላት እነዚህ መጥተው የነበሩ መነኮሳት እንዲመጡ ተባለ... በጊዜው ለእኔ ነው ስልክ የተደወለው:: ‹‹እንድትመጡ የአይሮፕላን ትኬትም ተቆርጦላችኋል››

አሉኝ፤ ‹‹አይ አሁንማ ልትገሉን ካልሆነ በቀር በተደጋጋሚ ቢሮአችሁ ድረስ መጥተን መልስ አልሰጣችሁንም ፤ያኔ መልስ ሳትሰጡን አሁን ምን ተገኝና ኑ ትሉናላችሁ? ከፈለጋችሁ ከታረሰው ቦታ ድረስ ኑና አነጋግሩን›› የሚል መልስ ሰጠኋቸው::

በኋላ የጠቅላይ ቤተክህነት ስራ አስኪያጅ ተስፋዬ ውብሸት የተባለና ሌሎች ሁለት የቤተ ክህነት ሰዎች፣ የሽሬና የመቀሌ ባለስልጣናት፣ ተሰብስበው መጡ:: መጀመሪያ ላይ የአዲስ አበባ አገረ ስብከት ምክትል ስራ አስኪያጅ ሽሬ ላይ ሰብስበውን ነበር በዚያ አልተስማማንም፤ እኛም የታረሰው ቦታ ላይ ሄደን ካልተነጋገርን በቀር አንወያይም አልናቸው:: እነሱ ደግሞ ‹‹ማይፀብሪ›› ላይ እንነነጋገር አሉ፤ ‹‹ማይፀብሪ ክልላችን አይደለም፣ ሶስቱ ገዳም የሚሰበሰቡት አድርቃይ ላይ ስለሆነ እዛ ተነጋገረን ወደ ታረሰው መሬት እንሂድ፤እኛ ሶስት አራት መነኩሴዎች ብቻ በዚህ ጉዳይ ላይ መወሰን አንችልም በሶስቱ ገዳማት ያሉ መነኮሳትንም ማነጋገር አለብን አልናቸው::

በዚህ መሰረት መጋቢት 5 ቀን ‹‹አባ ነፃ›› የተባለውንና በግድቡና ስኳር ልማቱ ፕሮጀክት አማካይነት ይነሳል የተባለው ቦታ ላይ ሄደን ተሰበሰብን:: መስማማት አልቻልንም ስንወዛገብ ዋልን፤ ቦታው አይነካም የሚል አቋም በመያዛችን ሊቀጳጳሱም ሆኑ የመጡት የመንግስት ባስልጣናት ሄዱ፤ ግን ወደ መጡበት ሳይመለሱ ወዲያውኑ ፌዴራል ፖሊሶች ልከው በገዳሙ ውስጥ ቤታችንን አስፈተሹ:: የትልልቅ መነኮሳት በአት (መኖሪያ) እየተገለበጠ ተበረበረ:: በጊዜው እኔንም ይዘው ለመሄድ ፈልገው ነበር፤ ግን በአካባቢው ሊያገኙኝ አልቻሉም:: አመጣጣቸውን ስላወቅኩ ወደ በረሃው ገብቼ ተሰወርኩ::

**ግዮን፦ አባ ገብረስላሴ እርስዎስ ከመጀመሪያው የዋልድባ ገዳም ውዝግብ አንስቶ የነበሮት ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር?**

አባ ገብረስላሴ፦ ያው ጉዳዩን አባታችን አባ ገብረየሱስ ገልፀውታል:: ገዳሙ ወክሏቸው ሲወጡ ሲወርዱ የነበሩት እሳቸው ናቸው:: ግን ማህበሩ በሚሰበሰብበትና ቃለጉባኤ በሚያደርጉበት ሰአት ሁላችንም መኮሳት አብረን እንሰበሰብ ነበር:: 2004 ዓ.ም ላይ ገዳሙን ለልማት ልናውለው ነው ለእናንተ ካሳ እንስጣችሁ ብለው በመጡበት ወቅት 500 የምንሆን መነኮሳት ከመንግስት ባለስልጣናትና ከሀገረ ስብከቱ ሰዎች ጋር ተሰብስብናል:: ዙሪያችንን በመከላከያ ሰራዊት አጥረውና ከበው ነበር ያነጋገሩን፤ ‹‹ይሄ ገዳም ከመድሃኒአለም የተቀበልነው አደራ ነው፤ ስለዚህ የአደራ እቃ አይበላም፤እኛ ሳንሞት ወይም ሳንሰየፍ ይሄ ቦታ ለልማት ሊውል አይችልም:: ሃጥያት አይሻገርብሽ እህል አይብቀልብሽ ብሎ ክርስቶስ በራሱ በቃሉ የተናገረበት፤ ከኢትዮጵያ ህዝብ ባሻገር የአለም ህዝብ የሚድንበት ቦታ ነው›› ብለን መነኮሳቱ ተናገርን::

ቦታዎቹ በአራቱ አፍላጋት የተከበቡ ናቸው:: በተከዜ፣በዛሬማ፣በማይዞንና በኢንሲያ የተከበቡ ቦታዎች ናቸው:: ‹‹ይህች የእኔ ጫንቃ ናት፤ይህችን ቦታ የሚነካ፣የሚያርስ ሰው እንደ አርዮስ እንደ ይሁዳ ነው›› ብሎ ተናግሯል መድሃኒአለም እየሱስ ክርስቶስ:: ስለዚህ እኛም ከእምነትም ከታሪክም አኳያ በህይወት እያለን ቦታው ለልማት አይውልም የሚል አቃም በመያዛችን ስብሰባው ተበተነ::

ደን መመንጠር፣ የግድብ ስራ ጀመረ:: አፅመ ቅዱሳንን በግሬደር እየቆፈሩ እየወጡ ወደ ውሃው መስደድን ተያያዙት:: በጊዜው ይሄ ነገር እንዴት ነው? በማለታችን ችግሮች ተፈጥረዋል:: ገዳሙ ውስጥ ህወሃት የሚባል ድርጅት ያስቀመጣቸው መነኮሳት አሉ:: ድሮ በሰለላ ይግቡ አይግቡ አላውቅም፤ አሁን ግን የሚሰሩት ለተባለው ድርጅት ነው:: አናሳርስም ካሳም አንቀበልም ያለውን መነኮሳት ሰላዮቹ እየጠቆሙ በሚልሻ ሲያስደበድቡ ብዙ መነኮሳት ገዳሙን ትተው ወጥተዋል:: በዚህ የተነሳ በጊዜው ወንድማችን አባገብረየሱስን በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ያፈላልጓቸው ነበር::

በዚህ ችግር የተነሳ ግማሹ መነኮሰት ገዳሙን ለቆ ሲሄድ ግማሹ ደግሞ ፀሎት ያዘ፤ ያኔ መከላከያ መጥቶ ፀሎቱን አስቁሟል:: ፀሎት እንዳይፀለይ፣ ምህላ እንዳይደረግ ከለከለ “በዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ፀሎት እየተደረገ ነው” እያሉ መረጃ የሚያቀብሉና መነኮሳት በወታደሮች እንዲደበደቡ የሚያደርጉት እነዛ የስርአቱ ሰላይ የሆኑት መነኮሳት ናቸው:: እነዚህ ሁለት ሰላዮች አባ ገብረህይወት መስፍንና አባ ሰላማ የተባሉ መነኩሴዎች ናቸው:: እኛ አባቶቻችንን ያስተማሩን እኛም የምናስተምረው ስለ ሰላም፣ስለፍቅር፣ ስለአንድነት ነው፤ ሰው አብሮ እንዲበላ፣ እንዲፋቀር፣ ኢትዮጵያዊነት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ነው የምንሰብከው:: ይሄ የእኛ ብቻ ሳይሆን የቤተክርስትያንም አምነት ነው:: ግን ያለው ሁኔታ ወደ ዘረኝነት ተገልብጧል:: ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ በመከራ ነው ያለው::

**ግዮን፦ እናንተ ከታሰራችሁ በኋላ እስካሁን ድረስ ያለው የዋልድባ ገዳም በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለው መቼም እዛ ካሉ መነኮሳት ጋር በቂ የመረጃ ልውውጥ ታደርጋላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን?**

አባ ገብረየሱስ፦ በነገራችን ላይ የህወሃትና የዋልድባ ገዳም ፀብ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን የዘለቀ ነው:: በርግጥ በጊዜው እኔ የገዳሙ አባል ባልሆንም የቀደሙ አባቶች እንደነገሩኝና ሁሉም የአካባቢው ምዕመን እንደሚያውቀው፤ አሁን ሜይዴይ የሚል ትምህርት ቤት ያሰየሙበትን ቦታ አካባቢ ‹‹አባ ነፃ›› አካባቢ ያለ፣ የዘሪማ ወንዝ (ሊገደብ የተፈለገው) አካባቢን በፊትም ይመኙት ነበር:: ህወሃቶች በትግል ላይ እያሉ በ1973 ዓ.ም ‹‹እኛን የሚረዳን አካል ስለሌለ አትክልት እየተከልን እንመገብ›› በሚል ሰበብ ቦታውን እንወስዳለን በማለት ገዳሙን ያነጋግራሉ:: ማህበረ መነኮሳቱ ደግሞ ይሄ ቅዱስ ቦታ ነው አንሰጣችሁም ይሏቸዋል፡ የሚገርማችሁ ያንን ቦታ ኢህአፓ የተባለው ድርጅት አስቀድሞ ፈለጎት ነበር:: ቦታው እንደተባለው ለአትክልት ይመቻል፤ ግን ኢህአፓም አልተሳካለትም”

በጊዜው እምቢ የተባሉት ህወሃቶች “ለአንድ ሳምንት ጊዜ ሰጥተናችኋል ቦታውን ስለምንፈልገው እንደወስደዋለን፤ አስተካክሉ” ብለው ሄዱ:: የመነኮሳቱ ማህበር “እግዚአብሄር ያውቃል” የሚል መልስ ነው የሰጣቸው:: ታጋዮቹ ሲሄዱ መነኮሳቱ ለአንድ ሳምንት ሱባኤ ያዙ:: በሰባተኛው ቀን “አዳባስ” በተባለው ቦታ ላይ ደርግ መጥቶ እዛ ቦታ ላይ የነበረውን የህወሃት ሰራዊት ጨፈጨፈው:: በዛው እነሱም ከአካባቢው ጠፉ፣ነገሩም በረደ:: ገዳሙን መንካት ሌላ ችግር እንደሚያመጣ የገባቸው ይመስለኛል::

በ1980 ዓ.ም በድጋሚ ህወሃቶች መጡና የገዳሙን ቦታ እንወስዳለን፣ መንገድም ጥርጊያ እንሰራለን በሚል እንቅስቃሴ ጀመሩ:: ምልክቱ እስካሁን ድረስ አለ፤ በሰአቱ ያንን ነገር ሲያደርጉ ዘንዶና ነጭ እባብ ታጋዮችን እየገደለ ድራሻቸውን አጠፋቸው፤ አባይ ወልዱና አንዳንድ ሰዎች ከዛ የተረፉ ሰዎች ናቸው:: በህወሃቶች በኩል ይሄን እንደቂም ይዘውት ኖረዋል:: ያኔ ሊያለሙበት ይዘውት የመጡትን ዶማና አካፋ፣ መመንጠሪያ ፣ትልልቅ ጎላ ብረት ድስት ጥለው ሄደዋል::

እሱን እስከ አሁን ድረስ የአካባቢው ገበሬ እየተጠቀመበት ነው የሚገኘው:: የዋልድባን ቅዱስ ቦታ መንካቱ ለህወሃት ሌላም ጣጣ አምጥቶበታል:: ማርገፅ ጊዮርጊስ የሚባል ቦታ ላይ ጎድጓዳ ዋሻ ውስጥ ተቀምጠው ከነበሩት ታጋዮች ውስጥ በግንቦት ወር ላይ ከዚህ መጣ ያልተባለ ድንገተኛ ጎርፍ የተወሰኑትን ከእነ ሙሉ እቃቸው ጥርግርግ አድርጎ ይዟቸው ጠፍቷል:: ይሄንን ህወሃቶች ጠንቅቀው ያውቁታል:: ዛሬ ግድብ እንገድባለን፣ ልማት እናካሂዳለን እያሉ ያሉት ያንን ቂም ለመወጣት ነው፤ ከዚህ ሌላ የዋልድባ ገዳም ሰፊ ነው ወርቅ አለ፣የከበረ ማዕድን አለ፣ጥጥ፣ሰሊጥ ማምረት የሚያስችል ቦታ ነው፤ እነሱ ያንን በብቸኝነትይዘው ማልማት ይፈልጋሉ:: ግድቡ ሰበብ ነው:: በተጨማሪ ሽፍቶች መጥተው ይገባሉ የሚል ፍራቻ ስላላቸው ገዳሙን ማጥፋት ይፈልጋሉ:: ከምንም በላይ ደግሞ “ገዳሙ ኢትጵያዊነት የሚንፀባረቅበት ቦታ ነው፤ ህብረ ብሄር ነው ፤ከየትኛውም ቦታ የመጣ ሰው ይገባል፤ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት መጀመሪያ ደግሞ የዋልድባን ገዳም ማጥፋት አለብን” የሚል ነው የስርአቱ አላማ:: በገዳሙ ስለ አገር ፍቅር፣ስለኢትዮጵያ ፍቅር፣ ስለምና አንድነት በደንብ አንፀን ነው የምንሸኘው፤ ይሄ ነገር ለስርአቱ አይመችም:: አማራን ለማጥፋት የግድ ቤተክርስቲያንን ማጥፋት ያስፈልጋል ብለው ስለሚያምኑ መጀመሪያ ዋልድባን ማጥቃት ጀመሩ ማለት ነው::

ስለዚህ የዋልድባና የህወሃት ችግር አርባ አመት ሆኖታል ማለት ነው:: 40 አመት ሙሉ የተያዘ ቂም ነው፤ አሁን አዲስ የሚመስለው ችግሩ ፈጦ ስለወጣና ከህዝቡ ዘንድ ስለደረሰ ነው፤ አሁንም ይሄ ጉዳይ አልተፈታም አለማለሁ በሚል ሰበብ ይህ ቅዱስ ቦታ እየታረሰ፣ አፅመ ቅዱሳን ከአፈር ጋር ወደ ወንዝ እየተጣሉ ነው፤ ይሄ ይቁም ነው እኛ የምንለው::

**ግዮን፦ በጊዜው እርስዎ ዋናው የመነኩሴዎቹ አመፅ አስተባባሪ ኖት ተብለው ሲፈለጉና ክትትል ሲደረግብዎት ቆይተው፤ ከአንድ አመት በፊት ነበር የተያዙት እንዴትና በእነማን ነበር የተያዙት?**

አባገብረየሱስ፦ በወቅቱ እኔ የማህበረ መነኮሳቱ አደራና ውክልና ስለነበረብኝ በአቋሜ ገፋሁበት ፤በመጨረሻም ስብሰባ ላይ ከመንግስት ሃላፊዎች ጋር ስንነጋገር ‹‹ይሄ ቦታ የታረስ ብለን አንወስንም ብትገሉም ስጋችንን፣ ብትገርፉም ስጋችንን ነው፤ ግን ምንም አይነት ለውጥ አይኖርም፤ ይኸው ሜዳው ይኸው ፈረሱ›› በሚል ነው የተለያየነው:: ያኔ ያሳመፀውና መነኮሳቱ አይሆንም እንዲሉ ያደረገብን እሱ ነው፤ ደጀ ሰላም ለሚባለው ድረገፅ፣ለቪኦኤ፣ ለፍትህ ጋዜጣና ለሌሎች አካሎች መረጃ እያሰራጨ ነው በሚል እኔን ማሳደድ ጀመሩ:: በወቅቱ እኔን ፈልጎ ለያዘ ሁሉ ውለታ እንደሚከፍሉ ተናገሩ፤ መንገዶች ሁሉ ተዘጉ:: መኪናዎች ሁሉ ይፈተሹ ነበር::

የተያዝነው 2009 ዓ.ም ታህሳስ 28 ቀን ነው:: በግንቦት 7 አባልነት ተጠርጥራችኋል በሚል ነው፤ ሲይዙን የፍርድ ቤት ወረቀት አላሳዩንም፤ ቁጭ ባልንበት ነው የከበቡን፣እንደ ደረሱ አንድ ቃል ሳያወሩ ዱላ ነው የጀመሩት:: ወደ 40 የሚጠጉ ወታደሮች ናቸው፤ከባድ መሳሪያ በመኪና ላይ ጭነው በታጠቀ ሰራዊት ነው የወረሩን::

ፍፁም ርህራሄ በጎደለው ሁኔታ ያለማቋረጥ ከባድ ድብደባ ፈፀሙብን ፤እኔም ራሴን ሳትኩ እንደ ሬሳ ጭነው አምጥተው ነው ማዕከላዊ ወንጀል ምራመር ያስገቡኝ:: ብዙ ጎድተውኛል፣ የሚገርማችሁ ነገር ሂዱ

አትሄዱም የሚል ጥያቄና መልስ እንኳ የለም:: የህወሃት ወታደሮች ናቸው እንደደረሱ ያለማቋረጥ ደበደቡን:: ደህንነቶቹ ዩ.ኤን የሚል ታርጋ የለጠፈች መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው ነበር፤ በተለይ አንደኛው የደህንነት አባል በጣም መቶኛል፤ የተወሰኑት ራቅ ብለው ይመለከታሉ::

ቆቤን አውልቀው ወረወሩት፤ በቪዲየ ይቀርፁኝ ነበር:: ራቁቴን አድርገው ቀርፀውኛል ፤ሌላ የቅንብር ነገር መስራት ፈልገው ነበር መሰለኝ፤ ግን ይሄን ሁሉ የሚያደርጉት እየደበደቡኝ ነው፤ መጨረሻ ላይ ራሴን ስቼ ስወድቅ መኪና ውስጥ ከተው ወደ ማዕከላዊ አመጡኝ::

**ግዮን፦ አባ ገብረስላሴም ያኔ በቦታው አብረው ሆነው የተያዙት፤ እንዴት ነበር የአያያዝ ሁኔታው?**

አባገብረስላሴ፦ ከበድመሳሪያዎች የጫኑ ከ40 ያላነሱ ወታደሮች ናቸው መጥተው የያዙኝ:: ደብድበውኛል በጣም አሰቃይተውኛል:: የሰው ልጅ ላይ ሊፈፀም በማይገባ መልኩ ‹‹የት ነው ያለሁበት ቦታ›› ስል ማዕከላዊ መሆኑ በሰው ነው የተነገረኝ እንጂ እንዴት ወደ አዲስ አበባ እንዳመጡኝ እንኳ አላውቅም፤ በዱላ ብዛት ራሴን ስቼ ነበር::

ማዕከላዊ ከመጣን በኋላም ቢሆን ተመሳሳይና የከፋ ነገር ነው የገጠመን:: ከምሽቱ ሁለት ሰአት ሲሆን እኔንም አባንም ያወጡንና ሌሊቱን ሙሉ እየገረፉ አሳድረውን ሊነጋጋ ሲል ይመልሱናል::

**ግዮን፦ ሲገርፏችሁ ምን ነበር የሚሏችሁ?**

አባ ገብረስላሴ፦ ከአርበኞች ግንቦት ሰባት ጋር ትገናኛላችሁ፣ ከትልልቅ ባለስልጣናት ከአነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር ትገናኛላችሁ፤ እያሉ ነው በየቀኑ ለወራት ያለማቋረጥ ማታ ማታ እየጠሩ የሚገርፉን፤ የሚደበድቡን:: ስቃይና መከራው ከባድ ነው፤ አሁን ሰውነቴን ገልጬ አላሳያችሁም እንጂ ሰውነቴ ሸቶ ሰው ለመቅረብ ይሳቀቅ ነበር ለምፁ አሁንም ገላዬ ላይ አለ:: መንታ አለንጋ አለ፣ የኤሌክትሪክ ሽቦ አለ፤ በእዛ ነው ያለ ርህራሔ ራቁታችንን አድርገው የሚገርፉን::

የ21ኛው ክፍለ ዘመን ፋሽስቶች ናቸው:: በእንዲህ ያለ ሁኔታ የተሰቃየነው እኛ ብቻ አይደለንም:: ብዙ የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች በማዕከላዊ ከባድ ግርፋትና ድብደባ ተፈፅሞባቸዋል:: ዘሬ እየተጠቀሰ “አንተ አህያ” እየተባልኩ ነው የሚገርፉኝ፤ ያቺ ሰአት የጣዕረ ሞትና የስቃይ ሰአት ናት:: ከህዝብ ጋር ዳግም እንገናኛለን፣ ከእናንተም ጋር ቁጭ ብዬ እንዲህ አወራለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ግን እውነተኛው አምላክ ይሄን አድርጓል፡ እኔንም አባንም “እነዚህ መነኩሴ አይደሉም” እያሉ እየተቀባበሉ ነው የሚቀጠቅጡን:: ህክምና ቤት አዝለው ሲወስዱን እዛ ያሉትም ሰዎች ተመሳሳይ የህወሃት ሰዎች ናቸው “ለምን ትደበደባላችሁ፤ ለምን የምታውቁትን አትናገሩም” ነው የሚሉን፤ ከሚሉት ነገር ጋር ፈፅሞ ግንኙነት እንደሌለን ብንናገርም አያምኑንም፤ ማዕከላዊ ውስጥ ያሉት የህወሃት ሰዎች ከእነሱ ውጭ የሆነውን አማራውን፣ ኦሮሞውን ሰበብ እየፈለጉ ለማጥፋት የተነሱ ናቸው:: የእኛ ጥያቄ በግልፅ ይታወቃል፤ያሰረን ሕወሐት ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ የተፈታነው በህዝብ ግፊትና መስዋዕትነት ነው::

በጣም በሚያስነውር መልኩ ብዙ ግፍ በሁለታችን ላይ ተፈፅሞብናል:: ራቁታችንን ምንም ልብስ ሳንለብስ ሐፍረተ ስጋችን እየታየ ሁሉ ነው የገረፉን:: ዋልድባ ቅዱስ ቦታ ነው፤ ህዝበ ክርስትያኑ የሚድንበት የእምነት ቦታ እንዴትና ለምን ይታረሳል በማለታችን ብቻ::

**ግዮን፦ ፍርድ ቤት የቀረባችሁት ከስንት ጊዜ በኋላ ነው? ማዕከላዊስ ምን ያህል ጊዜ ታሰራችሁ?**

አባገብረየሱስ፦ በማዕከላዊ አምስት ወር በእስርና በስቃይ ቆይተናል:: እንደ ተያዝን በአራተኛው ቀን ጊዜ ቀጠሮ ፍርድ ቤት አቀረቡን:: ዳኛው 28 ቀን ሰጠ፣ ድብደባው የተጠናከረው ከዛ በኋላ ነው:: በዛ መልኩ ዝም ብለን በቀጠሮ እየተመላለስን አምስት ወር ከ13 ቀን ሳይቤሪያና ሸራተን በሚባሉት ማሰሪያ ቦታዎች ነው የቆየነው:: ለተወሰኑ ጊዜ ምርመራ የጨረሱ እስረኞች ወደ ሚታሰሩበት መልሰውን ነበር::እንደገና ደግሞ ከዛ አውጥተው መልሰው ጨለማ ቤት አሰሩን:: ከፍርድ ቤት ቀጠሮ ውጪ ብዙ ቀናት እዛው ማዕከላዊ እስር ቤት እንድንቀመጥ ተደርገናል::

ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓም በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶብን በ14 ወደ ቂሊንጦ እንድንወርድ ተደረገ:: ቂሊንጦ ዞን ሶስት አስገብተው አሰሩን:: መጀመሪያ እዛው እንዳለን መረጃ (ሰላይ) ላኩብን::እሱ ከእኛ ጋር መተኛት ጀመረ:: ሰውዬው ሙስሊም ነው፤ እኛ ሰውዬውን ባናውቀውም የሚያውቁት ሰዎች ሲናገሩ ሸዋሮቢት፣ ዝዋይ እየተዘዋወረ የሚሰልል ነው:: ይህ ሰው መሪጌታ ጌትዬ መኮንን ተብሎ ወደእኛ መጣ፤ በኋላ ሰላይ እንደሆነ አወቅን፤ ለነገሩ ራሱም ይናገራል:: ሁለት ወር አካባቢ አንድ ላይ ከታሰርን በኋላ አባ ገብረስላሴን ስድስተኛ ቤት እኔን ሰባተኛ ቤት አስገቡን::

ተለያይተን ከታሰርን በኋላ ታራሚውን እያሳመፁ ነው፣ ምክር እየሰጡ የአርበኞች ግንቦት ሰባት አላማን እየሰበኩ ነው በሚል ፊታቸውን ወደእኛ አዞሩ:: እኔን ወደ ዞን ሁለት አባን ደግሞ ወደ ዞን አምስት ወሰዷቸው፡ እሳቸውን እዛ ወስደው ክፉኛ ደበደቧቸው፤ እኔ ዞን ሁለት ስደርስ የስኳር ፕሮጀክቱን ዲዛይን የሰራው ኪሮስ የተባለና አታክልቲ የተባለው መሃንዲሶች በሙስና ታስረው እዛ አገኘኋቸው:: ‹‹ገዳማችንን ልታጠፉ፣ ልታወድሙ ነበር ፤ነገር ግን ይኸው እኛም እናንተም አብረን ነው ያለነው›› በሚል ትንሽ ውዝግብ ተፈጠረ::፡ በጊዜው ችግር ፈጣሪ የነበሩት ሰዎች እነሱ ስለነበሩና ስለምንተዋወቅ ነው የተናገርኩት:: በዚህ ምክንያት እኛ ደስ ስላልናቸው ፖሊሶችም የእነሱ ደጋፊ ስለሆኑ መልሰው ዞን አምስት አስገቡኝ፤ ሁለት ወር ከ19 ቀን እዞ ቦታ ነው የቆየሁት::

**ግዮን፦ አባ ገብረስላሴ እርስዎ ቂሊንጦ በጣም እንደ ተሰቃዩ ፣ከባድ ድብደባ እንደተፈፀመብዎ ነው የሰማነውና እስኪ ድርጊቱን ቢያስታውሱን?**

አባ ገብረ ሰላሴ፦ በማዕከላዊ ታስሬ በነበርኩበት ብዙ ከተሰቃየሁ በመሃል ከዛ አውጥተው አዲስ አበባ ፖሊስ ይዘውኝ ሄደው ነበር፤ አዲስ አበባ ፖሊስ ቆብህንና ልብስህን ካላወለቅክ አትገባም አሉኝ:: “ይሄ ልብስ አባቶች ያለበሱኝ፣መከራ ቢመጣም ልቀበልበት፣ ሞት ቢመጣም ልቀበልበት እንጂ ሐይማኖት ማለት ስንፈልግ የምናወልቀው ስንፈልግ የምንለብሰው አይደለም” የሚል መልስ ሰጠኋቸው “ጳጳሱም ቢሆን ፓትሪያሪኩም ቢመጣ አውልቆ ነው የሚገባው፤ ስለ እዚህ እናንተ የታዘዛችሁትን ፈፅሙ” በሚል ወታደሮቹ ረጅም ሰአት አውልቅ በሚል ሲደበድቡኝ አብረውኝ ወደ ፖሊስ ጣብያው የሄዱ ወደ 40 የሚጠጉ ታሳሪዎች “ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ” ብለው ሲያምፁና ጥያቄ ሲያቀርቡ ወደ ማዕከላዊ መለሱኝ::

እዛ እንደ ደረስኩ ኮማንደር መብራህቱና ኮማንደር ሐዱሽ የሚባሉ ተቀብለው ጨለማ ቤት አስገብተው ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ሲደበድቡኝ አምሽተው ወደ አባ ገብረየሰሱስ መለሱኝ:: እሳቸውንም ምርመራ አለብዎት ብለው ወስደው ሲያሰቃይዋቸው ውለው ከመለሷቸው በኋላ እየታሹ ነው ያገኘኋቸው::

ወደ ቂሊንጦ ስንወርድ የገጠመን አንድ አይነት ነው፤እዛም ፈላጭ ቆራጮቹ የህወሃት ሰዎች ናቸው:: ኦህዴድ ይሁን ደኢህዴን ወይም ብአዴን ቅፅል ነው እንጂ ምንም ስልጣን የላቸውም፤ አድራጊ ፈጣሪዎቹ ህወሃቶች ናቸው:: ዘረኝነት ላይ የተመረኮዘ ጥቃት የሚፈፅሙት፣ ሰው የሚደበድቡትና የሚያሰቃዩት እነሱ ናቸው:: በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ሰው የሚደበድበው፣ አካሉ የሚጎድለውና ቂሊንጦ ነው:: ዞን አራት፣ ዞን አምስት የተባለ ጨለማ ቤት ውስጥ የሚፈፀመው በደል ከባድ ነው::፡

እኛ ገና ቂሊንጦ ስንደርስ ‹‹ግሞ የመነኩሴ አሸባሪ ››እያሉ እየሰደቡ፣ እያንጓጠጡ ነው ያስገቡን:: ለሁለት ወር ያህል እንግዳ መቀበያ የሚባል ክፍል ነው ያስቀመጡን:: ሌሎች እስረኞች ክፍል አንገባም፤ አምስት ስድስት ሰው ነው በደንብ የሚከታተለን:: ከዛ በኋላ ‹‹ስብከት እየሰበካችሁ ነው፣ አድማ እያሳደማችሁ›› ነው በሚል ወንድሜ አባ ገብረየሱስን ወደ ዞን ሁለት ወሰዷቸው፤ “ለምን ትወስዷቸዋላችሁ? እናንተ እኮ አስቀምጡ ነው የተባላችሁት እንጂ ለምን ሰው ታሰቃያለችሁ” ብዬ ጥያቄ ሳቀርብ እኔን ወደ ዞን አምስት ወሰዱኝ::

ህዳር 27 ቀን 2010 ዓ.ም ቀጠሮ አለህ በሚል አወጡኝ፤ ተፈሪ የሚባል ፖሊስ ነው እስረኛ የሚለብሰውን ዩኒፎርም በእጁ ይዞ ‹‹ልብስህን አውልቅና ይሄን ልበስ›› አለኝ በጊዜው ከእሱ ሌላ አራት ዱላ የያዙ ወታደሮች ቆመዋል፤ የሚያናግረኝ በስርአጽ እንኳ ሳይሆን መሬት ለመሬት እየጎተተ ነበር፤ ‹‹ካላወለቅክ እንገልሃለን ብለውኛል›› ገብረ እግዚአብሄር የሚባል የደህንነት ሃላፊ ቆሞ ነው ይሄን ሁሉ የሚያዘው፤ እምቢ ስላቸው መሬት ለመሬት እየጎተቱ፣ እየደበደቡ ተጫወቱብኝ::

ያቺ ቀን የማትረሳ የህይወት ቀኔ ናት:: የጭንቀት፣የሃዘንና የመከራ ቀኔ፤ ልቤን ሁሉ ተመትቼ ለብዙ ቀን ሲያስለኝና ደም ሲያስተፋኝ የቆየሁበት:: የመነኩሴ ልብስህን አውልቅ ብለው ነው ለማመን በሚከብድ ሁኔታ ሰውን ማሰቃየት ምን የሚሉት ነው? በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ብዙ ሰው ተመልክቶ ስለ ነበር ዞን፤ ሁለት ውስጥ ያሉ ወደ ሶስት የሚሆኑ የእነሱ አባል የሆኑ ሰዎች ሁሉ ‹‹ለምን በሐይማኖታችን ትገባላችሁ?›› የሚል ጥያቄ አንስተው ነበር::

በሰአቱ እጄ በካቴና ቢታሰርም መስቀል ይዤ ነበር:: ሲያስደበድበኝ የነበረው ገብረእግዚአብሄር የሚባለው የደህንነቱ ሰው “ማነው መስቀሉን የሰጠህ?” አለኝ፤ እኔም “መስቀሉን የሰጠኝ ታላቁ ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” ስለው ከቦታው ተነስቶ ሄደ:: ከጠዋቱ አንድ ሰአት ተኩል እስከ ረፋዱ አራት ሰአት ድረስ “ልብስህን አውልቀህ የታሳሪዎች ዩኒፎርም ልበስ፣ አለበለዚያ ትሞታለህ እንጂ አንተውህም›› እያሉ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ያለማቋረጥ ሲደበድቡኝ ሲያሰቃዩኝ ነው ያረፈዱት:: በዚህ የተነሳ ሰላሳ ሁለት ቀን በጨለማ ቤት ካሰሩኝ በኋላ ወደ ሌላ ዞን አስገቡኝ፤ አባ ገብረየሱስን ደግሞ ወደ ዞን አምስት ወሰዷቸው::

እዛም በቀን አምስትና ስድስት ጊዜ እየጠሩ ያስፈራሩን፣ ይዝቱብን ነበር:: ‹‹መጀመሪያ ጥይቷ የምትተኮሰው እናንተ ላይ ነው›› እያሉ ያስፈራሩን ነበር፤ ምንድነው የምትፈልጉት ስንላቸው መልስ አይሰጡንም፤ ስለዋልድባ ስናነሳ ነው ፊታቸው የሚለዋወጠው፤ ስለ ገዳማችን ካነሳን አንድ ነገር ሳይፈጠር እኛም

ሳንሰቃይ ያደርንበት ጊዜ የለም:: ቂሊንጦ በዚህ መልክ ነው እስከ መጨረሻው ድረስ የቆየነው::

**ግዮን፡- ለወራት ለሰው ልጅ ከሚሸከመው በላይ የሆነ ከባድ በደል ሲፈፀምባችሁ ፍርድ ቤት ብቻ ነበር የመናገር እድል ያገኛችሁት፤ እዛ የነበረው አካሄድ በራሱ ህዝበ ክርስትያኑን ያሳዘነ ነበር፤ በዚህ ዙሪያ የነበራችሁ ስሜት ምን ነበር?**

አባ ገብረየሱስ፡- በአሁን ሰአት ያለው ፍርድ ቤት የዳኝነት፣የአቃቤ ህግና የጠበቃ ሙያ በተቢው መንገድ የሚታይበት ቦታ አይደለም:: እኛ ፍርድ ቤት ሲባል እውነት የሚፈረድበት፣ ንፁህ ሰው ነፃነቱ የሚረጋገጥበት ትልቅ ቦታ ነበር የሚመስለን፤ ግን አይደለም:: በእኛ ጉዳይ እንዳየነው ስልክ ተደውሎ እንዲህ አድርግ እንዲህ በል እየተባለ ዳኛ የሚታዘዝበት ቦታ ነው:: በራሱ አዕምሮ የሚሰራ ዳኛ አላየንም ፤እውነቱ ፈጦ እያለ የምንባለው ግን ሌላ ነው… እኔ አሁን ስያዝ ምንም አልተገኘብኝም፣ በኋላም እንደዛው:: ግን ማዕከላዊ የእኔ ያልሆነ ነገር አቀረበ… ተው የእኔ አይደለም ብዬው ነበር:: ለምሳሌ ሞባይል፤ የሌላ ሰው ሞባይል የእኔ አድርገው የማዕከላዊ ሰዎች አቅርበዋል:: የእኔ አይደለም የእኔ ከሆነ ባለሙያዎች ስላሉ በእነሱ ይመርመር ብያለሁ:: እኔም ሆንኩ አባታችን ዳዊትና ድርሳነ ሚካኤል ይዘን ነው የተገኘነው::

እኛ እየተከራከርን ያለነው በዋልድባ ጉዳይ ነው::አሁንም ወደፊትም ይሄንን አቋማችንን እንገፋበታለን:: አባገብረየሱስም ሆነ አባ ገብረ ሰላሴ የምንከራከረው ገዳሙ እየታረሰ ነው፣ ቅርሶች እየተዘረፉ ነው በሚል ነው፤ ይሄን መግለፅ አስካለብን ድረስ እንናገራለን:: መቼም ወደኋላ አንልም፤ እኛ እንዴት አሸባሪ ሰው ገዳይ እንባላለን?..ማንን ለማዳን ነው ሰው የምንገድለው? ብለን ለፍርድ ቤት ስንናገር ‹‹አይ ይሄንን በፅሁፍ አቅርቡ፤ ቀጠሮ እዚህ ቀን ሰጥተናል›› የሚል መልስ ካልሆነ በቀር አቃቢ ህግን ለምን እንዲህ አደረግክ? ለዚህ በትክክል ማስረጃ አለህ ወይ? ብለው ዳኞች አይጠይቁም::

ብዙ ጊዜ ሰምታችሁት ይሆናል የሃሰት ምስክር የሚባለውን ነገር፤ የሃሰት ምስክር ፋብሪካው ማዕከላዊ ነው፤ አራት ጓደኞች አስሮ ሁለቱን ምስክር አድርጎ ያቀርባል:: በእኛ ላይ አልመሰከሩም እንጂ እኛ የማናውቃቸው ግን ከእኛ ክስ ያሉ ሰዎች፤ ማዕከላዊ በፅሁፍ ይሄ እገሌ ላይ የምትመሰክሩት ይሄ ደግሞ እገሌ ላይ እየተባሉ ስልጠና እየተሰጣቸው ተቀምጠዋል:: እኛ ደግሞ የምትሉት አሸባሪ አይደለንም:: እንዴት አብረውን እስር ቤት የነበሩ ሰዎች ምስክር ይሆናሉ ብለናል::

በቂሊንጦ ካየነው መሃል በእሳት ቃጠሎው የተነሳ ሟች ብለው "እሱ እንዲህ አድርጎ፣ይሄን ሰርቶ" በሚል አግዝፈው ከሰውታል:: ግን ሞተ የተባለው ሰውዬ በህይወት አለ፤ አይገለፅ ስለተባለ እንጂ:: ሌላው 18ኛ ወንጀል ችሎት በሙስና ጉዳይ ሁለት ፋይሎች አሉ፤ በሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ፈጠው ቁልጭ ብለው ታይተዋል:: አብረው የታሰሩ ሰዎች ከመሃል የተወሰኑትን አወጡና በሚፈልጉት ሌሎች ታሳሪዎች ላይ ምስክር መሆን ይችላሉ በሚል እንዲመሰክሩ ተፈቀደ:: እነ አብዮት ተስፋዬ፣ አበበብርሃኔ የሚባሉ በሙስና የተያዙ ግለሰቦች ናቸው::፣ በሌላ በኩል እነ ጌታቸው የሚባሉ ተከሳሾች ላይ ከእነሱ ጋር አብረው ከታሰሩት መሃል የተወሰኑት ምስክር አድርገው መረጡ:: እንዴት እነዚህ ሊመሰክሩብን ይችላሉ በሚል አቃቤ ህጉን ሲሞግቱ እነዛው ዳኞች "አብረው የታሰሩ ሰዎች ሊመሰክሩ አይችሉም" ሲሉ በየኑ:: አያችሁ ሁለት ዳኝነት፤ በአንድ ጉዳይ:: የፍትህ ስርአቱ ችግር አለበት:: እኛም



ስንገላታና ስንሰቃይ የነበረው በፍትህ እጦት ነው::

በተለይ ዘርአይ ወልደሰንበት የሚባል ዳኛ አለ፤ ይሄ ሰው የህወሃት ሰው ነው:: በተለያዩ ድረ ገፆች ሲፅፍ፣ ስርአቱን ሲያሞካሽ የነበረ ነው:: ወደ አቃቤ ህግነት ቦታ ሲመጣ የአፋር ብሄር ነኝ በሚል የመጣ ነው፤ ከአቃቤ ህግ አልፎ ወደ ዳኝነት ገባ:: አቃቤ ህግ ከሆነ በኋላ ጠበቃ ሆነ፣ ከጥብቅና ተመልሶ ወደ ፍርድ ቤት ገባና ዳኛ ሆነ:: ሆን ተብሎ ጎንደርን ለማጥቃትና ለመምታት ስለተፈለገ የእኛ ጉዳይ የሚታይበት ችሎት ላይ ተቀመጠ::

እኛ፣የወልቃይት ኮሚቴ፣ የባህርዳር ታሳሪዎች በአጠቃላይ በአማራ ክልል ያለን አብዛኛው ሰዎች በ4ኛ ወንጀል ችሎት ነው ጉዳያችን እንዲታይ የተደረገው:: ሌላው በኦሮምያ ያለውና ጠንካራ የተባለው የእነ በቀለ ገርባ ፋይልም እንዲሁ:: ይሄንን ጉዳይ ማየት ያለበት የእነሱ ሰው ስለሆነና ሌላው እየሸረሸረ እንደሚፈልጉት ስላላደረጉላቸው ይሄ ሰውዬ በችሎቱ ላይ ዳኛ ሆኖ እንዲቀመጥ ተደረገ::

በፍርድ ሂደቱ የእኛም ሆነ የወልቃይት ተከሳሾች ማስረጃ ሊገኝብን ስላልቻለና ፍትሃዊ ዳኝነት መስጠት ስላልቻለ ወደእሰጣ ገባና ተራ ስድብ ተገባ:: ሠላማዊ ሂደቱ ቀርቶ ባለበት ሁኔታ የ32 እስረኞች ክስ ተቋረጠ:: እኛና አንድ ነጋ ዘላለም የሚባል ልጅ ቀረን:: ክርክራችን እኛ አላቋረጥንም፤ በተለይ የምንኩስና ልብሳችንን እናቃጥለዋለን እንገላችኋለን እየተባልን ስለቆየን በተደጋጋሚ ለፍርድ ቤቱ አቤት ስንል፤ ያኔ ምን እንደታየው አናውቅም "የሃይማኖት ልብሳቸውን መልበስ እንዳይከለከሉ" የሚል ትዕዛዝ ሰጠ:: ያ ትዕዛዝ ለእኛ አይደለም:: ትዕዛዙ ለቤተክርስትያን ነው፤ እንደዛ በመወኑ እኛ ደስ ብሎናል፤ ግን ሰጠም አልሰጠም እኛ አላወለቅንም፤ አናወልቅም:: በህይወት እያለን እንደማይሆን እነሱም ያወቁታል፤ ይሄ የእምነት ጉዳይ ነውና እኛ ብናወልቀው ውርደቱ ከራሳችን አልፎ ለቤተክርስትያን ነው፤ ነገር ግን በአቋማችን ፀንተን መቆየታችን ለቤተ ክርስትያንም ለህዝበ ክርስትያኑም የሚያኮራ ፍርድ ተሰጥቷል ፤በዚህ የተከበረችው ቤተክርስትያን ናት፡

**ግዮን፡- አባ ገብረስላሴ የሚጨምሩት አለ?**

አባ ገብረስላሴ፡- ፍርድ ቤት ዳኛ ማለት ከህዝብም፣ ከመንግስትም ሳይሆን በገለልተኝነት ከእውነት ፊት መቆም ያለበት ነው ብዬ አምናለሁ:: ከፖለቲካው ነፃ መሆን አለበት:: ነገር ግን እኛ ያየነው ፈፅሞ የተለየ ነው፤ በሽብር ስም ሆን ተብሎ አማራና ኦሮሞን እንዲበቀሉ የተቀመጡ ሰዎች አሉ፤ አንዱ አቶ ዘርአይ ወ/ሰንበት ነው:: በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ሽብር የለም:: በዚህች አገር ላይ እያሸበሩ፣ እየደበደቡና እያሰቃዩ ያሉት እነሱ ናቸው:: ሌላ አይደለም፤ ይሄ ዳኛ በወልቃይት ጉዳይ 4 ገፅ ዝርዝር የያዘ ክስ ቀርቦበታል:: ‹‹አማራ አህያ፤ ምን ታረጋላችሁ?›› እያለ ሁሌ ይሳደበል:: ስለዚህ ‹‹አንተ ዘረኛ ነህ፣ ዳኝነት ማለት ከፖለቲካ የፀዳ ነው፣ አንተ ግን ህወሃት ነህ፣ ልትዳኘን አትችልም›› ብለን ስናቀርብ እየተሳደበና እያንጓጠጠ እስካሁን ድረስ አለ::… የሚገርማችሁ አቃቤ ህግ የእከሌ የእከሌ ክሳቸው ተቋርጧል በሚልበት ቀን አይመጣም፤ ችሎት ላይ አይገኝም::

በነገራችን ላይ እኛ አሁን ለእናንተ የምንገልፀው ያየነውንና ያገጠመንን የሰዎችን ድርጊት እንጂ የምንሰብከው የምንኖረውም ስለፍቅርና አንድነት ነው:: ሁሉንም የሰው ልጅ በፍቅርና በአክብሮት ነው የምናየው፤ ወደፊትም ከዚህ ሃሳብ አንወጣም:: ግን እንደ ህወሃት አስከፊ ድርጊት የሚፈፅሙትን ሰዎች እንጠላለን ስራቸው አሰቃቂ ነው፤ ከድሮ ጀምሮ ቂም ያለባቸው ነው የሚመስሉት:: ፍርድ ቤት ላይ ወሳኙ ከኋላ ነው ያለው እንጂ ዳኞች ለህሊናቸው ብለው የሚፈርዱበት፣ የሚወስኑት ነገር የላቸውም:: አድርጉ የተባሉትን ነው የሚያደርጉት:: ዳኛ የለም፤ ፍትህ የለም፤ በአሁን ሰአት ኢትዮጵያዊ መሆን በራሱ በጣም አስቸጋሪ ነው::

በቂሊንጦና በቃሊቲ ያሉ እስረኞች አብዛኛዎቹ አሁንም ፍትህ አላገኙም:: ኑ እየተባሉ እየተጠሩ እየተደበደቡ፣ እየተሰቃዩ ያሉ በርካታ ናቸው:: ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት ድረስ ምንም ወንጀል የሌለባቸው፤ ግን በፍትህ እጦትና በፈላጊያቸው አካል ያለ በቂ ምክንያት እንዲቀመጡ የተደረጉ አሉ::

**ግዮን፡-በቅርቡ ዶ/ር አብይ አህመድ ጠ/ሚኒስቴር ሆነው ተመርጠዋል፤ከተፈታችሁ በኋላ እሳቸውን ለማነጋገር አላሰባችሁም?… ለእዚህና ሌሎች ጥያቄዎች መነኮሳቱ የሰጡትን ምላሽ በቀጣይ ዕትም ይዘን እንቀርባለን::**

# ‹የአንዷት፣ ገናና› ኢትዮጵያ ራዕይ እና የአጤ ቴዎድሮስ ፍጻሜ



ተረፈ ወርቁ

**«የቋራው አንበሳ፣ አጤ ቴዎድሮስ ሞትን የናቁ፣ ድሎትን የራቁ፤ ኢትዮጵያዊ ጀግና ናቸው ! »**

*(ኢትዮጵያዊው ታሪክ ጸሐፊ ክቡር ዶ/ር ተክለ ጻድቅ መኩሪያ)*

**ቴዎድሮስ «የዘመናዊ ሥልጣኔ ሐሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር።»**

*(ፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ - የታሪክ ምሁር)*

### እንደ መንደርደሪያ

ዛሬ በነጻነት የምንኖርባት ውድ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በብዙ አባቶቻችንና እናቶቻችን ጀግንነትና ከብረት የጠነከረ ወኔ፣ ቆራጥነትና ብርቱ መሥዋዕትነት በክብርና በኩራት የተረከብናት ባለ ታላቅ ታሪክ ሀገር ናት:: ከቅርብ የታሪካችን ዘመን ብንነሣ እንኳን ‹‹የቋራው አንበሳ›› አጤ ቴዎድሮስ ከደባርቅ እስከ መቅደላ ከግብጻውያንና ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተፋልመው፣ አጤ ዮሐንስ ከጉራዕ እስከ ጉንደትና መተማ ድረስ ዘልቀው ከደርቡሾችና ከግብፃውያን ጋር ተናንቀውና አንገታቸውን ለሠይፍ ሠጥተው፣ ‹‹አፍሪካዊው የጦር ጄኔራልና ጀግና›› የሚል ክብርን የተጎናጸፉት አሉላ አባ ነጋ በዶጋሊ ግንባር ከወራሪው ጣሊያን ሠራዊት ጋር በጀግንነት ተፋልመው፣ አጤ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱም ከአምባላጌ፣ መቀሌ እስከ ዐድዋ ግንባር ድረስ- ከበርካታ ውድ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ልጆቿ ያደረጉት የእምቢ ለነጻነቴ ተጋድሎና ያስመዘገቡት አንጸባራቂ ድል ዓለም ሁሉ በአድናቆት የሚመሰክርለት፣ ታሪክ በወርቅ ቀለሙ የከተበው ዕውነታ ነው::

የታሪክ መዛግብት እንደሚመሰክሩትም ይህ የአባቶቻችን የነጻት ተጋድሎ፣ ከብረት የጠነከረ አይበገሬነት፣ ወኔና ጀግንነት ሀገራችንን ኢትዮጵያን- ለአፍሪካ፣ ለአፍሪካ አሜሪካውያን፣ ለመላው ጥቁር ሕዝቦች እና እንዲሁም ነጻነታቸውን ለሚወዱና ለሚያከብሩ የሰው ልጆች ሁሉ የነጻነት ቀንዲልና ፋና የሉዓላዊነት ትዕምርት /Symbol/ እንድትሆን አድርገዋታል::

ስለሆነም ይህን ለአፍሪካ፣ ለመላው ጥቁር ሕዝብና ነጻነታቸውን ለሚያከብሩና ለሚወዱ የሰው ልጆች ሁሉ የጋር ኩራት የሆነ ታሪካችንን በቅንነት ለጋራ ራዕያችን ተሞክሮነት ለማዋል እንነሳ:: ‹‹በመሠረቱ የየትኛውም አገር ታሪክ ከስሕተት፣ ከመከራ፣ ከኢ-ፍትሐዊነት የጠራ አይደለም፤ ሕይወት ራሷ የሌላትን ምሉዕነት ከየት ያመጣዋል?!›› ይላሉ የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያም:: እንደ አሜሪካ ያሉ ትናንትና የተፈጠሩ አገሮች እንኳን ከሙግትና ከብዥታ የጠራ ታሪክ የላቸውም:: ስለዚህ ወደኋላ መለስ ብለን ታሪካችንን ስንቃኝ፣ ትናንትን ለመኮነን ሳይሆን ከትናንት ለመማር መሆኑን አንሳት:: ከታሪክ ሽሚያ፣ ብረዛ፣ ተበቃይነትና አልቃሻነት ተላቅቀን፣ ተሞክሯችንን ለበጎ ዓላማ እናውል::

በእርግጥም በጋራ መኖር የምንችለው የጋራ ራእይ ሲኖረን ብቻ ነው:: ከሁሉ በፊት ስለብሔራዊ ማንነታችን የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረን ያሻል:: ኢትዮጵያዊነት የሚባል ኅብረ ብሔረሰባዊ ማንነት እንዳለን ብቻ ሳይሆን፣ ባይኖር እንኳን ልንፈጥረው የሚገባን የአብሮነት እሴት መሆኑን መገንዘብ አለብን:: ኢትዮጵያዊነት አንድ ቤተሰብነት እንጂ ደባልነት አይደለም:: አንድ ቤተሰብ የሚቆመው በመላ አባላቱ ፍፁም የአካልና የባሕርይ ወጥነት ሳይሆን፣ በውሱን የወል ተመሳስሎና በተለይም አብሮነት በሚፈጥረውና በሚኖረው ፍቅር፣ መተሳሰብና ተስፋ መሆኑን መዘንጋት የለብንም::

ተደጋግሞ እንደተባለውም ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ዓውደ ሰፊና ለመለወጥ ክፍት በመሆኑ እያደር የሚያበለጽግ ሂደት ነው:: ቁምነገሩ ኢትዮጵያዊነት ያለቀለት ጉዳይ ሳይሆን፣ ሁልጊዜም የሚያድግና የሚሻሻል ሂደት መሆኑን እንገንዘብ:: እያንዳንዱ ትውልድ የጎደለውን እያሟላ፣ ያጓደለውን እያቀና፣ የየጊዜውን ነባራዊ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ እሴቶችን ሊያክልበትና የራሱን አሻራ ሊያትምበት ይችላል፤ ይገባልም:: ኢትዮጵያዊነት ትርጉሙ የተሟላ የሚሆነው በየዘመኑ ሚዛን መሆኑን አንሳት::

### 1. የታሪክ መዛግብትና የጥንት ሊቃውንት ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ምን ይላሉ?

ኢትዮጵያ እጅግ ጥንታዊ ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ናት:: ጥንታዊት ብቻም ሳትሆን፣ የሰው ዘር መገኛና ከቀደምት የሥልጣኔ ምንጮች አንዷ እንደሆነችም የሚጠቁሙ በርካታ የታሪክ መዛግብትና ሰነዶች አሉ:: ለምሳሌ ጆን ግላቨር ጃክሰን የተባለው ፓን አፍሪካኒስት የታሪክ ተመራማሪ፣ መምህርና ጸሀፊ፡- ‹‹Ethiopia and the Origin of Civilization›› (1939) በሚል ርእስ ባቀረበው ሒሳዊ ቅኝት፣ ስለ ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ምንጭነት የተጻፉ ልዩ ልዩ የታሪክ ሰነዶችንና ጽሑፎችን በዋቢነት ጠቅሶ ይህንኑ እውነታ ያስረግጣል:: ጃክሰን በዋቢነት ከጠቀሳቸው አያሌ ጸሐፍት መካከል የጥንታዊት ግሪክ ታሪክ ጸሐፍት ሄሮዱተስ እና ሆሜር ይገኙበታል:: በዚህች አጭር ጽሑፍ ውስጥ ለማነሳው ሐሳብ አስረጅ ይሆኑኝ ዘንድ፣ ቀደምት የታሪክ ጸሐፍት ስለ ኢትዮጵያ ከጻፏቸው መጻሕፍት ጥቂቶቹን ለማየት እንሞክር::

የጸሐፍቱን ሐሳቦች መተርጎም ሊያስከትል እሚችለው ‹‹ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ›› እሚሉት ዓይነት ‹ፈተና› ውስጥ እንዳይከተኝ በመሥጋት በተጻፉበት ቋንቋ እንዳሉ ልጥቀሳቸው::

Those piles of ruins, which you see in that narrow valley waters by the Nile, are remains of opulent cities, the pride of the ancient kingdom of Ethiopia. … There a people, now forgotten, discovered, while others were yet barbarians, elements of the arts and sciences. A race of men now rejected from society for their sable skin and frizzled hair, founded on the study of the laws of nature, those civil and religious systems which still govern the universe” (C. F. Volney -1791).

The Ethiopians were the first who invented the science of the stars, and gave names to the planets, not at random and without meaning, but descriptive of the qualities which they conceived them to possess; and it was from them that this art passed, still in imperfect state to the Egyptians.” (Lucian of Samosata 125-180 AD).

Ethiopian was the first established country on earth; and the Ethiopians were the first who introduced the worship of the gods, and who established laws (Stephanus of Byzantium, 6th C. AD).

በጥንታዊትና ታሪካዊት ኢትዮጵያ ግዛተ መንግሥት መካከል ያለውን ቀጣይነት የሚያረጋግጡልን ማስረጃዎችን ከዘመኑ መባቻ አንስቶ እናገኛለን:: ሄሮዶቱስ ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ ከዘገበ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ ግሪካዊው የታሪክ ሊቅ ዲኦዶሮስ ሲኩለስ (ከ፺-፳፩ ዓ.ዓ.) ‹የዓለም ታሪክ› በተሰኘው ዝነኛ መጽሐፉ፣ የኢትዮጵያ አንዱ ክፍል ከግብፅ እስከ መረዌ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከመረዌ



በስተደቡብ ምሥራቅ የተዘረጋ መሆኑን ያመለክታል:: ሌላው ግሪካዊ የመልክዓ ምድርና የታሪክ ሊቅ ስትራቦ (ከ፷፫ ዓ.ዓ.-፳፬ ዓ.ም.)፣ ራሱ ግብጽ መጥቶ ሽቅብ በዓባይ ወንዝ ሽለቆ ተጉዞ የኢትዮጵያን አቀማመጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ከኤሌፋንታይን እስከ ሕንድ ውቅያኖስ መዳረሻ መሆኑን አስተማማኝ ምስክርነት ሰጥቷል:: ሦስቱም ጸሐፍት ዓባይ ከአንድ የኢትዮጵያ ሐይቅ እንደሚመነጭ ጽፈዋል::

የታሪክና መልክዓ ምድር ሊቃውንቶቹ ሮማዊያኑ ፕሊኒም (ከ፳፫-፸፱ ዓ.ም.) ሆነ ክላውዲዎስ በጥሊሞስ (ከ፻-፻፸ ዓ.ም.) ኢትዮጵያን በተመለከተ ድምዳሜያቸው ከግሪካውያኑ ያልተለየ ነበር:: እንዲያውም በጥሊሞስ የኢትዮጵያን ከተሞች አዱሊስንና አክሱምን በካርታ ላይ ጭምር አስፍሯል:: ራሱ የአክሱም ንጉሥ የነበረው ዞስካለስ (፩ኛው ክፍለ ዘመን)፣ ጥርት ያለ ግሪክኛ ተናጋሪ እንደነበር በዘመኑ ከተገኘው ‹ፐረፕለስ ኦቭ ዘኤርትራን ሲ› መረዳት ይቻላል:: ከብሉይ ኪዳን በንጽጽር ሲታይ አዲስ ኪዳን የተጻፈው የኋልዮሽ ባለመሆኑ (ከ፶-፻፶ ዓ.ም.)፣ ‹ኦርጅናሌ› ግሪኩ ነባራዊ ታሪኮችን የሚጠቅስ ነው::

የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያም ‹‹ኢትዮጵያዊነት ሲባል›› በሚል ርእስ ባስነበቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው፤ በዚህ ዘመን መርዌ ተዳክማ በምትኳ አክሱም የመንግሥቱ መቀመጫ በመሆኗ፣ ኢትዮጵያ የሚለው የኩሽ ምትክ ነው ብሎ መከራከር አይቻልም:: ልማዳዊውና ዘመናዊው የኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት አክሱም የኢትዮጵያዊነት እምብርት መሆኗን ቢስማሙም፣ የሁለቱ አክሱም የትየለሌ ናቸው:: “ሳባዊት” አክሱም የጥንታዊት ኢትዮጵያ መናገሻ ስትሆን፤ የኋለኛዋ ታሪካዊት አክሱም ግን ቢበዛ ከ2ኛው ምዕተ ዓለም የሚቀድም ዕድሜ የሌላት፣ የታሪካዊት ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ናት:: የሚል ሐሳባቸውን ጥንታዊ የሆኑ የታሪክ ድርሳናትንና ጸሐፍትን ዋቢ አድርገው ያስረዳሉ::

በመሠረቱ ይላሉ ዶ/ር ቴዎድሮስ ሐሳባቸውን ሲያጠናክሩም፤ በዘመናዊ ታሪክ ጥናት ለኢትዮጵያዊነት የመጀመሪያው አገራዊ ፍንጭ ተደርጎ የሚወሰደው፣ “ኢትዮጵያ” እና “ሐበሻ” የሚሉት ስያሜዎች የጽሑፍ ማስረጃ የተገኘላቸው በዘመነ ኤዛና አክሱም በአራተኛው መቶ ዓ.ም. ነበር:: አክሱማውያን እንዲያው በድንገት በዚህ ዘመን ራሳቸውን ኢትዮጵያውያን ብለው መጥራት አልጀመሩም:: ሌላው ዓለምም ቀድሞም በሚያውቃቸው መጠሪያቸው እንጂ፣ ኢትዮጵያውያን ነን ስላሉ ብቻ አልተቀበላቸውም:: የዚህ ዘመን ኢትዮጵያና የቀድሞዋ ኢትዮጵያ አንድነትም በግልጽ የታወቀ ነበር:: የኤዛና የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ የተገኘ ብቸኛው አገራዊ ሰነድ ነው:: በአካባቢው ዓለም ስለዚያን ዘመን ኢትዮጵያ የሚገኘውን የማያወላዳ የግሪክ፣ ላቲንና ዐረብኛ ማስረጃ ስናጤን፣ ችግሩ የሰነድ እንጂ የታሪክ መቋረጥ እንዳልሆነ እንረዳለን::

የታሪክ ምሁራን እንደሚስማሙበት አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለታሪካዊ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ መሠረት የጣሉ በርካታ ክስተቶች በስለው የታዩበት ዘመናት ነበሩ ማለት ይቻላል:: ለምሳሌ በሮም እንደተስተዋለው ክርስትና በኢትዮጵያም በመንግሥታዊ ሃይማኖትነት የተተከለው በዚሁ ክፍለ ዘመን ነበር:: የግዕዝ ፊደል አናባቢው ተሟልቶለት ከንግግር ወደ ብሔራዊ የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-አምልኮ ልሳንነት ያደገው በዚህ ወቅት ነበር:: “የዓለም ቋንቋ ሁሉ በየነገዱ ስም ሲጠራ፣ ግዕዝ ብቻ በማንም ነገድ ስም አልተጠራም፤ በራሱ በገንዘቡ እንጂ” ይላሉ አለቃ ኪዳነወልደ ክፍሌ (1948፤ 10)::

ተከታዮቹ ሁለት ምዕተ ዓመታት ደግሞ ቤተ ክህነት በፍጥነት የተስፋፋችበት፤ ገዳማት በአገሪቱ ወርድና ቁመት የተተከሉበት፤ መጽሐፍ ቅዱስ ወደግዕዝ የተተረጎመበት፤ የዜማ፣ ቅኔ፣ ጽሑፍ፣ ሥዕል፣ ወዘተ ሥነ-ጥበባዊ ባህል ያበበት ዘመን ነበር:: ይኽንን ከይሁዲነት ወደ ክርስትና፣ ከሳባ ወደ ግዕዝ የተደረገ ሽግግር፣ እንደ ሁለተኛው የተሳካ የባህል ማወራረስ ሂደት አድርገን ልንወስደው እንችላለን:: ዘመኑ መንግሥተ ኢትዮጵያ ወደ ሁለገብ ሥልጣኔና ገናናነት የተሸጋገረበት ነበር::

ኢትዮጵያውያን ታሪካዊና ባህላዊ እትብታቸውን በማሰብ፣ የጥንቱ ግዛታቸውን መረዌን የወረሩበት፣ ባሕር ተሻግረውም በደቡብ ዐረብያ የተስፋፉበት ነበር:: እዚህ ላይ በመካከለኛው ምሥራቅ የተተከለው የኢትዮጵያ ግዛተ አፄ በ፯ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ተዳክሞ ወደ እናት ምድሩ ሲያፈገፍግ ኢትዮጵያም አንድ ተጨማሪ ብሔራዊ ቀለሟን እስልምናን ወረሰች:: እስልምና በ፯ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ በምድረ ኢትዮጵያ መሠረት ሳይጥል እንዳልቀረ ይገመታል:: ነገር ግን በሚቀጥሉት ሁለት ክፍለ ዘመናት ከሰሜናዊው ጠረፋማ ስፍራዎች መሃል ለመሃል እየሰነጠቀ፣ እስከ ማዕከላዊው ምድረ ሸዋ ድረስ ለማበብና ለመስፋፋት ችሏል::

ክርስትና በተወሰነ መልኩ የይሁዲነት ቀጣይ በመሆኑ፣ በኢትዮጵያ ከመጤነት ወደነባርነት ያደረገው ሽግግር አስቸጋሪ አይመስልም:: እስልምና ግን ከነባሩ የኢትዮጵያዊነት ርዕዮት ጋር የማይጣጣምና ሥር ነቀላዊ ባዕድነት ስለነበረው፣ አንዱ ሌላውን ለመዋጥ የሚሞክርበት ሁኔታ መፈጠሩ አልቀረም:: ነገር ግን ይኽ ፍፁም መሸናነፍ ያልተቻለበት ረዥም ትግል፣ የታሪካዊት ኢትዮጵያን ብሔራዊና ነባራዊ ሕልውና ቋሚ ተጽዕኖ አሳደረበት:: እስልምና በሂደት ከባላንጣነት ወደ አዎንታዊ የኢትዮጵያ ኃይልነት መሻገሩ አይቀሬ ነበር:: ነባርነትና መጤነት የጊዜም ጉዳይ በመሆኑ፣ ቀዳማዩ ደኃራዩን እያለመደ፣ እየገራና እየተቻቻለ አብሮ የሚኖርበት የኢትዮጵያዊነት ገዥ መንፈስ ተጠናከረ::

## 2.ገናናዋን አንዲት ኢትዮጵያን ዳግመኛ ዕውን የማድረግ የአጤ ቴዎድሮስ ሕልም

በመግቢያዬ ላይ በአጭሩ ስለ ጥንታዊቷ፣ ታሪካዊቷና የገናና ሥልጣኔ ባለቤት ስለሆነችው ኢትዮጵያ ከታሪክ መዛግብትና የምሁራን የጥናት ድርሰት በወፍ በረር ለማየት ሞክረናል:: ነገር ግን ይህች በታሪኳ፣ በአንድነቷ፣ በገናና ሥልጣኔዋና ልዑላዊነቷ ትታወቅ የነበረች ሀገር በግዛት ተበጣጥሳ፣ ከሥልጣኔ ማማ ወድቃ የእርስ በርስ ጦርነትና ግጭት ምድር ሆና ነበር:: ‹‹ዘመነ መሳፍንት›› ተብሎ በኢትዮጵያ ታሪክ የሚታወቀው የታሪክ ዘመን ኢትዮጵያ ሀገራችን የነበራት የግዛት አንድነት ተሸርሽሮ፣ በመኳንትና በመሳፍንት ተከፋፍላ አንዱ አንዱን አሸንፎና አስገብሮ የበላይ ለመሆን እጅግ ደም አፋሳሽ የሆኑ በርካታ ጦርነቶች የተካሄዱበት የጨለማው ዘመናችን አንድ የታሪክ ምዕራፍ ነው::

በታሪክ ገናና የሆነችውን፣ በጥንት ስልጣኔዋ ቀደምትና አንቱታን ያተረፈችውን ሀገራቸው ኢትዮጵያ እንዲህ በግዛት ተበጣጥሳና ተከፋፍላ መኖሯ እጅግ እንቅልፍ የነሳቸው አፄ ቴዎድሮስ ገናናዋንና ታላቂቷን ኢትዮጵያን እንደገና በዓለም መድረክ ከፍ ብላ ትታይ ዘንድ ትልቅ ራዕይ አግንበው የተነሡ ሰው ነበሩ:: ይህ የትናንትናዋን ባለ ገናና ታሪክና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነች ሀገር ኢትዮጵያን በማይመጥን ደረጃ የመገኘቷ የታሪክ እውነታ የፈጠረው ቁጭት ነበር የቋራው አንበሳ ካሣን እረፍት የነሳቸውና የእግር እሳት የሆነባቸው::

ከአፄ ቴዎድሮስ ንግሥና ዘመን የምትነሳው ዘመናዊት ኢትዮጵያ ከመቼውም የላቀ ፈጣንና ተለዋዋጭ ፈተናዎች የተደቀኑባት ነበረች ማለት ይቻላል:: ቋረኛው ካሣ ኃይሉ የየጁዎችን አገዛዝ የገለበጡት፣ የአገሪቱን ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ አንድነት፣ የዘውዱን ሥልጣንና ግርማ፣ እንዲሁም የታሪካዊውን ብሔረ ኢትዮጵያ መልሶ ለማቆም ቃል በመግባት ነበር::

‹አጤ ቴዎድሮስ› የሚለው ስመ መንግሥታቸው ራሱ ይኽንን ሕልማቸውን የሚያትት ስያሜ ነው:: ከሁሉም በላይ ቴዎድሮስ ለአገራቸው አዲስ ፈር ለመቅደድ የታጠቁ ባለራዕይ ንጉሥ ነበሩ:: የዘመናቸውን የአንድነት ፍላጎት ያዋለዱ፣ ተሸንፈውና ሞተው የኢትዮጵያን አባትነት ድል የተቀዳጁ፣ የዘመናዊት ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ብሔራዊ ጀግና ናቸው:: ሆኖም የቴዎድሮስ ሕልም ፈር የያዘው እርሳቸውን በተከተሉት ሦስት ነገሥታት ነበር:: አፄዎቹ ዮሐንስ፣ ምኒልክና ኃይለሥላሴ በወቅቱ የተደቀነውን የአውሮፓ ቅኝ ገዥነት አደጋ የተገነዘቡ፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ህልውና አብነቱ የአውሮፓን ሥልጣኔ የታጠቀች አንዲት አገር ናት ብለው የሚያምኑ ነበሩ:: እውነትም አገሪቱ በታሪኳ አይታው የማታወቀው ተደጋጋሚ ዓለም ዐቀፍ ጦርነት በመቅደላ፣ ጉንደት፣ ጉራዕ፣ ዶጋሊ፣ መተማ፣ አድዋ፣ ማይጨው ብሔራዊ ህልውናዋን ክፉኛ ፈትኗታል:: ስለዚህ ዘመናዊነት የውዴታ ምርጫ ጉዳይ ብቻ አልነበረም::



# የታምራት ደስታ
## ያልተሠሙ ዕዉነታዎች

አስራ አምስት አመት ወደኋላ እንመለስ:: 1995 ዓ.ም በወርሃ ጥር በኤሌክትራ ሙዚቃ ቤት አሳታሚነት ለበገበያ የቀረበው የጥበቡ ወርቅዬ "የዘላለሜ ነሽ" አልበምን ፕሮሞሽን ለመስራትና እግር መንገድም ቃለመጠይቅ ላደርግለት አንድ ምሽት ላይ ቀጠሮ ይዘናል:: በሰአቱ ጥቤ በቦታው ሲደርስ ብቻውን አልነበረም፤ አንድ በጣም ቀጭን ወጣት አብሮት ነበር::

የተገናኘንበትን ጉዳይ ጨርሰን ስንሰነባበት "ቀጣዩ ተረኛ እሱ ነው፤በቅርቡ አልበሙን ይጨርሳል" ሲል ጥበቡ ከከሲታው ልጅ ጋር አስተዋወቀኝ:: ልጁ ፍፁም ትሁት ነው የክ/አገር ልጆች ከውሃ ጋር በተያያዘ በጥርሳቸው ላይ ከሚከሰተው ብልዝ ከለር መሃል የሚፈልቀው ፈገግታም እውነተኛ ነበር... በርግጥ ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ ትውውቃቸው አስመሳይነት ሊስተዋልባቸው ይችላል፤ ይህ ሰው ግን ከዛ በኋላ ባሉት ዘመናትም ከመልካም ስብዕናው የተለየ አልነበረም::

በዚህን መሰሉ የትውውቅ መንገድ ግኑኝነታችን የተከፈተው ድምፃዊ ታምራት ደስታን ለበርካታ አመታት በቅርበት አውቀዋለሁ:: በተለይም ሁለተኛው እና ከህዝብ ጋር ያስተዋወቀው "አንለያይም" አልበሙ የበለጠ አቀራርቦናል:: ከስራ ውጪም በጋራ ጓደኞቻችን አማካይነት ብዙ አሪፍ ጊዜያትን አሳልፈናል:: ድንገት እንደወጣ የቀረው ታሜን በዚች መጠነኛ ፅሁፍ መግለፅ ከባድ ቢሆንም የማውቀውን ያህል ያልተሰሙ እውነቶቹን ልነግራችሁ ፈቀድኩ::

የጥቁር ውሃው ልጅ

ታምራት ደስታ ለቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ ነው:: ከሻሸመኔ አልፎ አዋሳ መግቢያ ላይ የምትገኘው የጥቁር ውሃ ፍሬ... እናትና አባቱ ሶስት ወንዶች ወልደዋል:: እሱ መሃለኛውን ቦታ ይዟል:: ታላቁ ከመወለዱ በፊት ለበርካታ አመታቶች ወላጆቹ አይናቸውን በአይናቸው ለማየት ተቸግረው ነበር:: የለመኑትን የማይነሳው ፈጣሪ ዘግየት ብሎ ሶስት የአዳም ዘር ጀባ ብሏቸዋል::

አብሮ አደጎቹ ሲያወሩ እንደሰማሁት ከሆነ ታሜ የልጅነት አመሉ አብሮት አድጓል:: “ያኔም ልክ እንደ አሁኑ ነበር” ይሉሉ ድሮ የሚያውቁት::፣ በተለይ በኪነጥበቡ አለም በወጣትነት እድሜያቸው ወደ እውቅና ማማ የሚወጡ በርካታ ወጣት ሙያተኞች የሚቸገሩበት ባህሪይ ታምራት ደስታ ላይ አይታይም:: ይዞት ያደገው ባህሪውን አጎልብቶና በውስጡ አስርፆት ነው የተለየን::

እንደ አብዛኛዎቹ ድምጻዊያን ሙዚቃን በት/ቤትና በተለያዩ የአካባቢው ክበቦች ውስጥ የጀመረው ታሜ በተሻለ ደረጃ ራሱን ለማስቀመጥና በስራው ስኬታማ ለመሆን አዲስ አበባ በመምጣት በተለያዩ ምሽት ክበቦች ውስጥ ሰርቷል::(በመሀል ድሬደዋ የተወሰነ ጊዜ ቆይቷል) በዚሀ ሂደት ውስጥ ደግሞ ራሱን ገርቷል፤ሙያዊ ብቃቱን አሻሽሏል:: ታሜ ከሰራባቸው ክለቦች የአራት ኪሎው ኪነ ቤት፣የሃይልዬ ታደሰ ፋልኮን ክለቦች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ::

ታሜ ስለ አራት ኪሎ ናይት ክለብ ስራው ብዙ ጊዜ አጫውቶኛል:: ገና አፍላ ወጣትነት እድሜ ላይ ሆኖ ያየውን መከራና ፈተና ሁሌም ይናገራል:: ለምን እንደሆነ ባይገባኝም ለእዛ አካባቢ የተለየ ስሜት አለው:: በርግጥ ብዙ ተፈትኖበታል:: በ1990ዎቹ መጀመሪያ ስመ ገናና በነበረው በዛ ናይት ክለብ ለአንድ ተራና ብዙም ልምድ ለሌለው ድምፃዊ የሚከፈለው ገንዘብ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፤ የቤት ኪራይ ላለበት ሰው ደግሞ ትርጉመ ቢስ ይሆናል::

ወጣቱና ቀጫጫው ታሜ ያኔ በደንብ ራሱን ፈጥሯል:: ከአላማው ላለመዛነፍ አነሰኝ በዛ ሳይል የተሻለ እስኪገኝ ደክሟል:: የአካባቢው ወጣቶችም በጣም ባለውለታዎቹ እንደሆኑ እሰማለሁ:: እሱም ‹‹አብልተውኛል፤አጠጥተውኛል›› ብሏል:: በደረቅ ሌሊት ከብርድና ከሰካራም ጋር እየታገሉ ስራን መስራት ከባድ ቢሆንም በ1994 ዓ.ም ለገበያ የቀረበውና ብዙም የማይታወቀው ‹‹ሐኪሜ ነሽ›› የተሰኘው የመጀመሪያ አልበሙ የተጠነሰሰው በአራት ኪሎ ነበር::

በጊዜው በገበያ ረገድ ያልተዋጣለት ይህ ስራ ለድምፃዊው ብዙ ነገሮች ቆም ብሎ እንዲያስብና ከስህተቶቹ እንዲማር ረድተውታል:: ለዚህም ይመስላል በሐብታሙ ቦጋለና ብስራት ጋረደው ግጥምና ዜማ ደራሲነት (የእሱም ፈጠራዎች ተጨምረውበት) በዳግማዊ አሊ አቀናባሪነት የተሰራው “አንለያይም” አልበሙ በቀናት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ገበያውን የጠቆጣጠረው:: ታሜ በዚህ ሁለተኛ አልበሙ ውስጥ የበኩር ስራውን “ሐኪሜ ነሽ” የተሰኘ ተወዳጅ ዘፈኑን በድጋሚ ሪአሬንጅ አድርጎ በመስራት አካትቶታል::

አራት ኪሎ የታሜ የስራ መሰረቱ ብቻ አይደለችም:: የህይወቱ መስመር ገፅታም ናት:: በአራት ኪሎ አፍቅሯል፤ በፍቅር ማዕበል ተንሳፏል፤ ‹‹የማይረሳ ጊዜ ነበረኝ›› ይላል የልጅነት ጊዜውን ካነሳ፤ ‹‹እንደውም እንደሰው ሰው ለመሆን የተንደረደርኩበት በዛው መጠን የተፈተንኩበት ነበር›› ይላል አራት ኪሎ በተለምዶ ግንብ መደዳ ተብሎ የሚጠራው



አካባቢ ቆይታውን ባጫወተኝ ወቅት::

የጊርጊሮ ሰፈርን ያሀል ባይሆንም ታምራት ደስታ በካዛንቺስ ብዙ ትዝታ አለው፤ ፋልኮን ክለብ በሚሰራበት ጊዜ እኔም በርካታ ጓደኞች በቦታው ስለነበሩኝና በተደጋጋሚ በመሄድ ወዳጅነታችን በመጠንከሩ በርካታ እውነታዎችን ከመስማት ባሻገር የማየት እድሉም ነበረኝ... በተለይ “አንለያይም” አልበም ሊወጣ ሲል የነበረው ጭንቀት አሁን ድረስ ይታወሰኛል:: በስራው እሱ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ብንተማመንም፤ ታሜ ግን የመጀመሪያው ታሪክ እንዳይደገም በጥቂቱም ቢሆን ፍራቻ ነበረው:: ከጅምሩ በነጠላ ዜማነት የተለቀቀው “እኛን ነው ማየት” ዘፈን ግን ይህንን ፍርሃት ያስወገደ አብሪ ጥይት ነበር ማለት ይቻላል::

የግል ስብዕና

ብዙ ጊዜ ሰው ከሞተ በኋላ ነው መልካም ጎኑ የሚነሳው ይባላል:: በርግጥም የሞተ ሰው ነው ማመስገንና ማድነቅ የሚቀናን፤ ግን ታሜ የምር ሊነገሩ የሚገቡ ብዙ መልካም ባህሪያት አሉት:: አመለ ሸጋነቱ ጥያቄ ምልክት ውሰጥ የሚገባ አይደለም:: ሲበዛ ለሰው ይጨነቃል፣ ትንሽ ትልቁን አክባሪ ነው:: በጣም ከሚገርሙኝ ባህሪው ውስጥ ብዙ ጊዜ በእሱ ደረጃ ካሉ ሙያተኞችና ሌሎች ትላልቅ ሰዎች ጋር መሆን እየቻለ የእሱ ምርጫ ግን ሁሌም ዝቅ ብሎ መመልከት ነበር:: ይህ አይነቱ ባህሪው ትንሽ የበዛ ነው የሚል አመለካከት ያላቸው አርቲስቶች አስተያየታቸውን ሲነግሩት አጋጥሞኛል፤ እሱ ባይቀበላቸውም::

ታምራት ደስታ መዝፈን ብቻ ሳይሆን መጫወትም ይችልበታል:: የቀልድ አድናቂ ነው “ምን አዲስ ነገር አለ” የምትል ባህሪው ትመቸኛለች:: የአምስት ልጆች አባት ቢሆንም እኔ ሳውቀው ዘና ማለት የሚወድ፣ ሰው ሲቸገር የማይመቸው፣ ያለውን ለማካፈል ወደኋላ የማይል ነው፤ እንደውም በርካታ ጀማሪ ድምፃዊያንና ሙዚቀኞች ‹‹ታሜ ፈታ ያለ ሰው ነው›› በሚል ቃል ነው ይሄን ስብዕናውን የሚገልፁት::ለእንቅልፍ ያለው ፍቅር ግን ሁሌም ግርም ይለኛል::

ታምራት በናይት ክለብ ስራ ላይ እያለ በተደጋጋሚ ውጪ ሰው ይፈልግሃል መባሉ የተለመደ ነው፤ እሱም የሄደበትን ጉዳይ ቋጭቶ ሲመለስ ሁሌም ፈገግ እንዳለ ነው፤የመሰላቸት ምልክት አይቼበት አላውቅም፤ ይሄ ደግነቱ በአካባቢው ከነበሩት ሌሎች የሙያ ባልደረቦቹ ለየት ባለ መልኩ እንዳየው አድርጎኛል:: በዛ ደረቅ ሌሊት እሱን ብለው የሚመጡት በተለያየ መንገድ የሚያውቃቸው ሰዎች ተስፋ ያደረጉት እሱን በመሆኑ ጉዳዩ ቢከብደው እንኳን ይህንን ተስፋቸውን ሊነጥቃቸው ፈፅሞ አይሞክርም ነበር::

አንድ ምሽት ሁለት ሴቶች መጥተው “ታምራትን እንፈልጋለን” አሉ፤ በሰአቱ ታሜ ከእኛ ጋር ራት ሌላ ቦታ በልቶ እየገባ ነበር፤ መልዕክቱ ሲደርሰው በቀጥታ ወደ ልጆቹ ሄደ የሚያውቃት አንደኛዋን ነበር፤ ረጅም ጊዜ እንዳልተያዩ ያስታውቃል፤ እሱ ግን ልጅቷን በማግኘቱ ከመጠን በላይ ተደስቷል:: የሚሆነውን ነበር ያጣው:: ስራ ከተጀመረ በኋላ እንኳን ብዙውን ሰአት ያሳለፈው ከእነሱ ጋር ነበር::

ይህች ወጣት ከሁለት ቀን በኋላ ስትመጣ ታሜ ዝም ብሎ አልሸኛትም፤ እንድትመጣ የቀጠራትም እሱ ነበር:: በሰአቱ ብዙ የሚባል ገንዘብ አዘጋጅቶ ነበር፤ ያንን ሲሰጣት የኑሮ ጉዳት ፊቷ ላይ የሚንፀባረቀው ወጣት ስቅስቅ ብላ ስታነባ አይተናል::... ዘግየት ብሎ ሲያጫውተን ልጅቷን አራት ኪሎ ነው የሚያውቃት፤ ምንም ባልነበረው፣ ባዶ ኪሱን በሆነበት፣ ለእራት መግዣ ሳንቲም አጥቶ አንጀቱ በታጠፈበት የችስታነት ዘመኑ:: በዛ ሰአት ታድያ ይህች ሴት ያኔ ቅቅል እንቁላል በውድቅት ሌሊት በየመጠጥ ቤቱ እያዞረች ትሸጣለች፣ ተራው እስኪደርስ ድረስ ደጅ ብርድ ላይ ኩርምት ብሎ አስፋልቱን የሚቃኘው ሲንቢሮው ታምራት ደስታ ያሳዝናታል:: ሙዚቀኞች የሚያገኙትን ገንዘብም ስለምታውቅ በራሷ ወጪ ቅቅል እንቁላሉን ልጣ በዳቦና በሚጥሚጣ አድርጋ ትጋብዘዋለች::

“ይህች ልጅ ችግሬ፣ረሃቤ፣ጥጋቤ፣ገመናዬ ጭምር ናት” ነበር ያለን:: ታምራት ደስታ ለብዙ ጊዜያት ባላት አቅም እየተንከባከበችው ከነበረችው ወጣት ጋር ስራ ሲቀይር ከተለያዩ ከአመታት በኋላ ጭምቱ ወጣት ዝነኛ፣ ከሲታው ታሜ ወፍሮና ደም ግባቱ ሞልቶ ተገናኙ:: እሱን አስታውሳ የመጣችውን ያቺን ወጣት ታምራት ማድረግ ከሚገባው በላይ አድርጎላታል:: በኋላ ላይ እሱ በሰጣት ገንዘብ ለተሻለ ህይወት ባህር ማዶ መሄዷን ሰምቻለሁ::

በርግጥም ታሜ እንዲህ አይነት ሰው ነው:: ያሳለፈውን የነበረበትን የማይረሳ፣ውለታ መላሽ ጭምር:: አንድ ቀን ስለ ድምጻዊ እዩብ መኮንን ሞት ስናወራ “ደግ ሰው እኮ ምድር ላይ አይበረክትም” ብሎኝ ነበር:: ታምራት ደስታ የምር ልክ ነበር “ደግ ሰው አይበረክትም” አሁን ተራው የእሱ ሆኗልና::



መስፍን ጌታቸው

# ይድረስ ለፌስቡክ ጸሐፊያን ወገኖቼ



ከሁሉ በፊት ከልብ የመነጨና ወንድማዊ የሆነ የአክብሮት ሠላምታዬን ከብዙ ትህትና ጋር ላቀርብላችሁ እወዳለሁ:: ይሄ መልዕክት እናንተን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ጸሐፍያንና የሚዲያ ሠራተኞችን የሚመለከት በመሆኑ ሁሉም ጆሮአቸውን አይነፍጉኝም ብዬ አምናለሁ:: በተለይ የፌስ ቡክ ጸሐፍያንን የጠቀስኩበት ምክንያት የዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው ሀሳብ በብዛት የሚስተዋለው እዛ መንደር ላይ ስለሆነ ነው::

እስኪ በግልፅ እንነጋገር.....እውነት ስድብ አልበዛባችሁም? የሰውን ክብር የሚያዋርዱ ክፉ የስድብ ቃላት ግሽግሽ አላደረጋችሁም? የጠላትነት ፍትጊያና ጦርነቱስ አላስመረራችሁም? እኔ ግን በጣም እጅግ በጣም አስመርሮኛል::

ታላላቅ ወንድሞቻችን ወይም ደግሞ የዛ የትውልድ አባላት ላለፉት አርባ ምናምን ዓመታት የአንድ እናት ልጆች የአንድ አፈር ፍሬዎች መሆናቸውን በመርሳት ጎራ ለይተው በክፉ የጠላትነት ስሜት እርስ በርስ ሲሰዳደቡ፣ ሲከዳዱና ሲገዳደሉ ኖረዋል::

አንዱ ወገን ድል ቀንቶት ስልጣን ከያዘ ወዲህም ስድብና ማዋረዱን አደራጅቶና አስፋፍቶ በሁሉም የመንግሥት የሚዲያ ተቋማት አማካኝነት ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ትክት እስኪለን ድረስ በግድ ሲግተን ኖሯል::

እኛም ከቅርብ ግዜያት ወዲህ “የነሱን ፈለግ” በመከተል በጠላናቸው ወገኖቻችን ሁሉ ላይ ሰብዐዊ ክብራቸውን በእጅጉ የሚያዋርድ የስድብ መዓት ስማቸውን ጠቅሰንና ፎቶግራፋቸውን ለጥፈን በተከታታይ ማዋረዱን ተያይዘነዋል::

እኔ የነሱም ሆነ የኛ ክፉ ድርጊት ትውልድ ከመመረዝ፣ ብዙ ቂምና ጥላቻ ከመፈልፈል፣ አገር ከማውደም፣ የብዙ ንጹሐን ወንድምና እህቶችን ነፍስ ከማጥፋት፣ መልካም ስነ-ምግባርን ከመግደል፣ መረን የለቀቀ ሥግብግብነትና ሌብነትን ከማንገስ፣ ጥርጣሬና አለመተማመንን ከማብዛት፣ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ክፉና መጥፎ የሆኑ የጥፋት ፍሬዎችን በተቀደሠች አገር ሠማይ ሥር ከመዝራት ባለፈ ምንም ያተረፍነው መልካም ፍሬ እንደሌለ ነው የሚሰማኝ::

ጥላቻ ክፉ ነው:: ከሚጠላው ሰው ይልቅ የጠይውን ሰው ልብና አዕምሮ ሠቅዞ በመያዝ ጠዋት ማታ ቂምና በቀልን እያመነዠከ እንዲኖር በማድረግ ደስታን አሳጥቶ ውስጥ ውስጡን እየበላ የክፉ ሀሳብ ምርኮኛ አርጎ በማስቀረት ክፉኛ ይጎዳል:: ለዚህም ነው “ጥላቻ በሌሎች ሰዎች ጥፋት እራስን መቅጣት ነው” የሚባለው::

ስድብም ከንቱ ፍሬ ቢስ ተግባር ነው:: ከተሰዳቢው ሰው ይልቅ የሰዳቢውን ሰው ክብር ዝቅ በማድረግ ክፉኛ ያዋርዳል::

ታዲያ ከጥፋት ይልቅ ምንም ጠብ የሚል ነገር ሳናገኝ ለምን ጠዋት ማታ ደስታችንን የጥላቻ ባሪያ አድርገን በማይረባ የስድብ ውርጅብኝ እራሳችንን እናሳንሳለን?

አንድን ጥሩ ያልሆነ መጥፎ ሀሳብ በሌላ መልካም የሆነ ጥሩ ሀሳብ ማሸነፍ ትልቅ ሥልጣኔ ነው:: ሀሳቡን በሌላ ምክንያታዊ ትንታኔ ብትንትን አርጎ ዕርቃኑን በማስቀረት ምን ያህል አይረቤና ጎጂ መሆኑን ማሳየት ብቻ ሳይሆን የተሻለውን ሀሳብ በውብ ቋንቋ መተንተን የበለጠ ከፍ ያለ ዋጋ ያለው መሆኑን

በጨዋነት መግለፅና ማሳየት የአንባቢውን ዕውቀት በእጅጉ ያሳድጋል:: ጤናማ ለሆነ የሀሳብ ፍትጊያ በር በመክፈትም በአገራችን የውይይትና የክርክር አውድ ላይ የራሱን በጎ የሆነ አሻራ ያሳርፋል::

በእኔ እምነት ኢትዮጵያ ሀገሩን የሚወድ ሰው በጠቅላላ ኢትዮጵያዊ ወንድሙን ከልቡ መውደድ አለበት:: አንድን አገር አገር የሚያሰኘው ወንዙ፣ ሸንተረሩ፣ ጋራው መሬቱ ወዘተ ብቻ አይደለም:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች አገርን አገር የማሰኘት ዋጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ አገር ትልቁ መገለጫና መታወቂያው ግን ፈጣሪ በአምሳሉ የፈጠረውና የአገሩ ባለቤት የሆነው ሰው ነው:: ከሁሉ ተለይቶ “ኢትዮጵያዊ” ተብሎ በክብር የሚጠራው ዜጋው ነው ተደማምሮ አገር የሚሆነው::

ታዲያ ወንድሙ የሆነውን የአገሩን ዜጋ በፍቅር ከመውደድና ከመደገፍ ይልቅ ጠዋት ማታ በስድብና በጥላቻ ማዋረድን የሚመርጥ ሰው እንዴት ሆኖ ነው እሱ አገሬን እወዳለሁ ሊል የሚችለው?

በዓለማችን ታሪክ ለትልቅ ዕድገትና ብልፅግና የበቁ አገራትን ለስኬት ካበቋቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ይሄ ለአገራቸው ያላቸው ሁሉ ዓቀፍ ፍቅር እና እርስ በርስ የተሳሠሩበት ወንድማዊ መዋደድ ነው::

የትም አገር ቢሄዱ የአገራቸው ዜጋ የሆነን ሰው ሲያገኙ የሚያሳዩት ፍቅርና ክብር በጣም የተለየና እጅግ ለወንድምነት የቀረበ ነው:: ሊገዙ የፈለጉት ማንኛውም ዓይነት ነገር ያሉበት አካባቢ ላይ ረከስ ባለ ዋጋ ሊገኝ እንደሚችል ቢያውቁም በጣም ሩቅ የሆነ ቦታ ድረስ በመጓዝ ያንኑ ዕቃ የአገራቸው ዜጋ ከሆነ ሰው ድርጅት በውድ ዋጋ መግዛትን ይመርጣሉ::

ወደ እኛ ስንመጣ ግን ታሪኩ የተገላቢጦሽ ነው:: እርስ በርስ ከመዋደድና ከመከባበር ይልቅ በጥላቻና በጥርጣሬ መገለማመጣችን ይበረታል:: እንኳን ራቅ ያለ ቦታ ድረስ ተጉዘን በውድ ዋጋ ልንገበያይ ቀርቶ “ይሄ ሰው ሊበልጠኝ እኮ ነው” በሚል ስጋት መጠላለፋችን ይገናል:: እና ደግሞ ከማንም በላይ አፋችንን ሞልተን አገሬን እወዳለሁ ለማለት እንሽቀዳደማለን::

እናም በዚህ ስሌት ወንድሙን የሰደበ የገዛ አገሩን እንደሰደበ፣ እህቱ ያዋረደ እናቱንና አገሩን እንዳዋረደ በማመን ይሄን ጥላቻን በማጥፋት ከፍቅር የሚያጎለንን ስድብና ንቀት በመተው ስህተታችንን በጨዋ ቋንቋ እየተራረምን በወንድማዊ መዋደድ ተረዳድተን አገራችንን ዳግም ከፍ ለማድረግ በርትተን ብንሠራ የሚሻል ነው የሚመስለኝ::

ወደድንም ጠላንም መጠሪያ ስማችን አንድ ነው:: የአንዳችን ውድቀት የሁላችንም ነው:: ወንድሙ ተርቦ እሱ ፍሪዳ የሚጎትት ሰው ጥጋቡ ትርጉም አልባ ነው:: በታረዙ እህቶቿ ፊት በወርቅ አልማዝ ተንቆጥቁጣ የምትመላለስ ቆንጆ ያሰበችውን ያህል ደምቃ ልትታይ ቀርቶ የነበረ ውበቷ በእጅጉ ይጎላል:: የሚላስ የሚቀመስ ያጡ ጎናቸውን የሚያሳርፉበት መጠለያ የሌላቸው ሚሊዮኖች ባሉበት አገር ውስጥ በሺህ የሚቆጠሩ ሚሊየነሮች ቢፈጠሩ ሀብታቸው የወል መጠሪያችን በሆነው የደሀ ደሃ የሚል ስም ከመጠራት አያድናቸውም::

አዎ መጠሪያ መታወቂያ ስማችን አንድ ነው:: ለዚህ ነው አትሌቶቻችን ድል ሲያረጉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ፤ አትሌቶቻችን ድል ሲያረጉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በክብር ከፍ ብሎ የሚነሳው:: ለዚህ ነው በሰው አገር አንድ ኢትዮጵያዊ ሠርቶ ሲገኝ ኢትዮጵያዊያን ሌቦች ናቸው በሚል ሁላችንም በአንድ የምንፈረጀውና ስማችን የሚቆሸሸው::

ኢትዮጵያ የምትጠግበው ሁላችንም መብላት ስንችል ነው:: ኢትዮጵያ የምታምረው የሁላችንም ገላ በልብስ ሲሸፈን ነው:: የአንድ ሚሊየን ሀብት ትርጉም የሚኖረው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቢያንስ መሠረታዊ ፍላጎቱን ማሟላት ሲችል ነው::

በጥንቱ የሮማዊያን የሥልጣኔ ዘመን አንድ ሮማዊ ጀነራል ጦርነት አሸንፎ ሲመጣ ህዝቡ በነቂስ ከአደባባይ እንዲወጣ ይደረግና አሸናፊው ጀነራል ግልፅ መኪና ላይ ከነሙሉ የማዕረግ ልብሱ ተቀምጦ በሆይታና በፉጨት አገሩን ባቀለጠው ህዝብ ፊት በኩራት ሠላምታ እየሠጠ እንዲያልፉ ይደረጋል::

ታዲያ በዚህ ወቅት ጨኸትና አድናቆቱ በጣም የበዛ ስለሆነ አሸናፊው ጀነራል ሰው መሆኑን ረስቶ ፈጣሪ የሆነ እንዳይመስለው “but you are a man” /ቢሆንም ሰው ነህ/ እያለ በተደጋጋሚ የሚነግርና የሚያስታውሰው አንድ ባሪያ አብሮት እንዲቀመጥ ይደረግ ነበር::

እኛም በንግዱም ሆነ በየትኛው የስራ መልክ ዓለምን ጉድ ያሰኝ ስኬት ብናስመዘግብ፤ በታላላቅ ከተሞች አዳራሽ ሙሉ የሳይንስና የቴክኖሎጂ አቅጣጫ በማስቀየር አሥር እርምጃ ወደፊት ማስፈንጠር የቻለ የጥናትና የምርምር ውጤት አቅርበን አዳራሹን በጋለ የምሁራን ጨኸትና ጭብጨባ ለማንቀጥቀጥ ብንችልም፤ አንድ ጥግ ላይ ተቀምጦ “but you are an Ethiopian” /ቢሆንም ግን ኢትዮጵያዊ ነህ/ በማለት አንገታችንን በሐፍረት የሚያስደፋን ሸቃባ ሰው አናጣም::

አንድን አገር አገር የሚያሰኘው ወንዙ፣ ሸንተረሩ፣ ጋራው መሬቱ ወዘተ ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች አገርን አገር የማሰኘት ዋጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ አገር ትልቁ መገለጫና መታወቂያው ግን ፈጣሪ በአምሳሉ የፈጠረውና የአገሩ ባለቤት የሆነው ሰው ነው

ይህ ባይሆን እንኳን ዜናውን የሚዘግቡ ዓለም ዓቀፍ የሚዲያ ተቋማት ዘገባቸውን “እራሷን መቀለብ ካልቻለች አንዲት የደሀ ደሃ አገር እንዲህ ዓይነት ታላቅ ሳይንቲስት ማግኘት በጣም የማይታመን ነው” በማለት ጀምረው ወይም ደግሞ አንዱን ጉምቱ ሳይንቲስት በማቅረብ “ኢትዮጵያ ከምትባልና መብላት ብርቅ ከሆነባት አገር እንዲህ ዓይነት ታላቅ ሳይንሳዊ ግኝት እናያለን ብለህ ጠብቀህ ነበር” የሚል ጥያቄ በመጠየቅ በሞቀ ደስታችን ላይ ውሃ መቸለሳቸው አይቀርም::

“but you are an Ethiopian” ወይም ቢሆንም ግን ኢትዮጵያዊ ነህ የሚል ቃል ስንሠማ አንገታችንን በሐፍረት የምንደፋው አገራችን የምታሳፍር አገር ስለሆነች አይደለም::

ይልቁንም ላላፉት ሃምሳ ያህል ዓመታት ልጆቿ ፍፁም በሆነ ወንድማዊ ፍቅር ተሳስረን የህዝባችንን ስቃይና መከራ በአንድነት ለማጥፋት ከመጣር ይልቅ ስራ ለይቶ መሰዳደቡ፣ መጠላለፍና መገዳደሉ ላይ አትኩረን ጉልበታችንን በከንቱ በማባከን ለዘመናት ተጣብቀን የኖረውን የረሃብተኝነት ታሪክ መቀየር ባለመቻላችን ነው::

እናም ወንድሜ ገጣሚው ስንኝ ቋጥሮ በዜማ እንዳስደመጠን ያንተ ቤት ሲንኳኳ የኔም ቤት አብሮ ይንኳኳል:: አንዳችን ያለ ሌላችን ምንም ማለት ነን:: እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው::

አንተ ቀና ማለት ስትጀምር እኔ መልሼ ቁልቁል የምዘፍቅህ ከሆነ፣ እኔ ወደፊት ለመራመድ ስቃጣ አንተ ጠልፈህ ልትጥለኝ የምትታትር ከሆነ እኔም ብቻዬን አልወድቅም አንተም ለብቻህ አትዘፈቅም::

ዓለም ዓይናችን ስር በአስገራሚ ፍጥነት በዕድገት ሽቅብ እየተንደረደረ እኔና አንተ ግን ተለያይተን ሳይሆን ተያይዘን አፈር ድሜ ስንግጥ ነው የምንኖረው::

ስለዚህ እኔ ላንተ አንተ ለኔ በነብስ የምንፈላለግ ጠላት ሳንሆን የሞት መድኃኒት መሆናችንን ከልብ አምነን በመቀበል እርስ በርስ በፍቅር መተሳሠሩ ነው የሚበጀንና መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን የሚያድነን::

በዚህ የምንስማማ ከሆነ የምንጽፋቸው መጣጥፎች በጠቅላላ ይሄን ወንድማዊ መዋደድ የሚያንፀባርቁና እስካሁን በአጉል የጠላትነት ስሜት እየተፋተግን ስላባከንነው ወርቃማ ጊዜ የሚሠማንን ቁጭት የሚያሳዩ ነው መሆን አለባቸው::

ጥሩ ያልሆነ ሀሳብ ሲመጣ ሃሳቡን በተሻለ ሀሳብ በጨዋ ቋንቋ ማሸነፍ ነው እንጂ ዐቅም እንዳጣ ሰው የገዛ ወንድማችንን በስድብ ማዋረድ እኛን አይመጥነንም::

ይሄ ማለት ግን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መጥፎ ድርጊት ላይ የተሠማሩ 24 ሠዐት ሙሉ አገራችንን የሚያዋርድና የሚያጠፋ ድርጊት የሚፈፅሙ ወገኖችን “ወንድም” ናቸው በሚል ዕምነት በየዋህነት እናልፋቸዋለን ማለት አይደለም::

በሥርዓቱ መክረርና ገስፀን ካልሆነም በጨዋ ደምብ ወንጀላቸውን በይፋ በመግለፅ ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙ ነው ማድረግ የሚኖርብን::

እናም ስናጠቃልል ፍቅርና አንድነቱን አብዝተን ስድብና ጠላትነቱን እናጥፋ:: “ኢትዮጵያ” በሚለው የቴዲ አፍሮ ዜማ እኩል በሲቃ የምንዘለውን ያህል ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ውድቀትና ጥፋት ሳይሆን ለዕድገቱ ቀበቶአችንን አጥብቀን እንሩጥ እንላለን::

ያኔ አፋችንን ሞልተን አገሬን እወዳለሁ ብንል በጣም እጅግ በጣም ያምርብናል::

## ስለ ወልቃይት የማንነት ጉዳይ ዙሪያ አቶ አታላይ ዛፌ የተናገሩት

•የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት አስመላሽ ኮሚቴ አባል ነኝ:: ጥያቄአችን በይፋ ይታወቃል:: እኛ ወልቃይቶች ጠገዴዎች ጠለምቶች ድሮም አማራ ነን አሁንም አማራ ነን ለዘላለም አማራ ነን:: የዚህ ማረጋገጫችን አንደኛው በህገ መንግሥት የተቀመጠልን መሥፈርት አለ:: የህዝብ ለቅሶ፣ ሐዘን፣ እንጉርጉሮ ቋንቋ እና በተለያዩ ነገሮች የምንጠቀምበት ባሕላችን የሚገልፀን ሲሆን ወልቃይት ብዙ ስቃይ ይፈፀማል። በአማርኛችን እንኳ መዝፈን አንችልም። አስከሬን በወጉ መቀበር አንችልም። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ብዙ ሄደናል:: ከወረዳ እስከ ፌደራል ድረስ ሄደናል:: ከ2007 ዓም ታህሳስ ወር ጀምሮ ሰነዶች በየቢሮው ገብተዋል:: ለትግራ ክልልም፣ ለአማራ ክልልም፣ ለደቡብ፣ ለኦሮሚያም አድርሠናል:: ሠነዶቻችን እዛው ይገኛሉ እንዲታይልን እፈልጋለሁ:: ሰብዐዊ መብቶችም ተቀብለውታል:: መጋቢት 27 ቀን 2008ዓ.ም ከፌዴሬሽ የተፃፈልን ደብዳቤ አለ:: ለትግራይ ክልል የወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ጉዳይ መልስ ይሠጥበት ተብሎ ታዟል:: ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው መሠረት ከሁለት አመት በኂላ ፌዴሬሽን ገብቶ እንደሚጠይቅ ይታወቃል:: ሆኖም ግን በነዚህ ዓመታት መካከል ሐምሌ 5 ቀን 2008 ዓ.ም በዚህ ጉዳይ ላይ ያለን ኮሚቴዎችና አባላት በክልላችን በዞናችን በቤታችን እያለን በራችን ተሠብሮ ሌላም ችግር ተፈጥሮ እናንተ የምታውቁት ክስተት ተፈጥሯል::

•አሁንም ወንድማችን ኮሎኔል ደመቀ ወደዚህ መድረክ ይዘነው እንድንመጣ የህዝቡ ፍላጎትና ስሜት ቢሆንም እናንተ አልፈለጋችሁም በዚህ ቅር ብሎናል:: የመጣነው እኔ፣ አቶ ሽፈራው ፣ አቶ ጌታቸው አደመ፣ አቶ ተሻገር ወ/ሚካኤል አቶ ወረታው አዛናው ሌሎችም አብረን መጥተናል:: ለዓመታት ጥያቄዎቻችን የተሠጠን መልስ የመታሠር የመደብደብ የመገደልና የመፈናቀል ነው:: ይሄ ለእኛ ብቻ አይደለም በመላው የአማራ ክልል በመላው የኦሮሚያ ክልል ነው ወጣቶች መስራት ማምረት አገር መገንባት ሲችሉ በየአስፓልቱ በሥርዓቱ ወታደሮች ወድቀዋል:: የአንድ እናት የአንድ አባት ልጆች አደባባይ ላይ ደማቸው ፈሷል ይሄ እንዲታወቅ እንፈልጋለን:: ገዳይና ሟች የአንድ ቤተሠብ ልጆች ናቸው:: አሁንም በወልቃይት ጉዳይ እስር ቤት የሚገኙ አሉ። በወልቃይት ጉዳይ 9 ወጣቶች በቅርቡ ተከሠዋል። እኛ ትግሬ አንጠላም፣ እነሱ ግን አሁም ያሳድዱናል። ለምን ያሳድዱናል? የወልቃይትን ጥያቄ ያነሳው ዲያስፖራ አይደለም። ዲያስፖራም ቢሆን ከባህር አሳ፣ ከኮንቴነር ሞት ተርፎ የተሰደደ ወገናችን ነው፣ ሲሞት አስከሬኑ ታሽጎ የሚላክልን ወገናችን ነው። ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱልንም እንፈልጋለን። ነገር ግን እኛ በዳያስፖራ አንመራም::

•የወልቃይትም ሆነ የሌሎች የአማራ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ዓመታትን የተሻገረ እንጂ ከፌስ ቡክ መምጣት በኂላ የተነሳ አይደለም:: የወልቃይት ጉዳይ የተጀመረው ፌስቡክ ከመጀመሩ ከሰላሳ ዓመታት በፊት በ1972 ዓ.ም. ነው:: የህዝቡ ጥያቄ በሠነድ ተጠርዞ ቢሯቸው ውስጥ አለ:: የአርማጭሆና የወልቃይት ህዝብ እየጮኸ ያለበት ጉዳይ እኮ በግልጽ በሠነድ የተቀመጠ ነው:: ጥያቄው ዛሬ አሊያም ፌስ ቡክ ከመጣ ቡሀላ የተጀመረ አይደለም:: በወልቃይት ህዝብ ላይ በልዩነት በደል እየደረሠ ነው:: ወልቃይትን ትግራይ ነህ ይሉታል ፤ እርሱ ደግሞ አይደለሁም አማራ ነኝ ይላል::

### ስለ ኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበር

•የጎንደርና የሱዳን ድንበር የዘመናት ችግር ያለው ነው:: አንዳንድ መሪዎቻችን ኃላፊነት የማይሰማቸው ዛሬ ግን የሚቀረቁራቸው በአንድ ወቅት በግዴለሽነት የሠሩት ስራ አለ:: ይሄ ዛሬ ጥያቄ እያመጣ ነው:: ይሄን ጥያቄ እያነሱ ያሉት እኮ ከ30ዓመት ወዲህ የተወለዱ ልጆች ናቸው:: ወጣቶች ታሪክ አንብበው ጠይቀው ነው የሚጠይቁት:: ከእንግዲህ በኂላም የሚወለዱት ልጆች ይሄን ጥያቄ አያነሱም አይባልም:: ስለዚህ ይሄ የማያዳግም መፍትሄ ካልተበጀለት የመሪነት ቅቡልነታችን ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀርም::

### ስለ አማራ ክልል ልማት

•የአማራ ክልልና ህዝቡ አንገቱን ደፍቶ የሚተክዝበት አንድ መሠረታዊ ችግር አለ:: ክልሉ ሠባት ታላላቅ ወንዞች አሉት:: አንድም ወንዝ ግን ክልሉን ጠቅሞ አያውቅም:: ወንዞቹ መብራት ያመነጫሉ ሀይቃችን መብራት ያመነጫል መብራት ግን የለንም:: ይሄ ብቻ አይደለም መብራት መንጭቶ ወደ አገር አቀፍ መስመር ተከፋፍሎ ይገባል እሰየው ነው የኢትዮጵያ ሐብት ነው:: ግን ይሄ መብራት 17 ማሠራጫ ጣቢያ ሲተክል እና 240 እና በላይ ኢንደስትሪ በአገሪቱ ሲቋቋም አማራን ምን በላው? ምን በደለ?

•በአማራ ክልልና በጎንደር ያለው የልማት ስራ የለም እንዳልለው የተጀመረና የቆመ አለ:: አለም እንዳልለው ደግሞ አልቆ በታሪክነቱ ታይቶ ልጆቻችን ሲጠቀሙ አላየንም:: ምን እንደምል ራሱ ግራ ይገባኛል:: በጎንደር አንድ ዳሽን ብቻ ነው ያለን ፋብሪካ ዳሽንም ደግሞ በራሱ የፖለቲካ ወገንተኝነት ውስጥ የተያዘ ነው:: በገንዘባችን ከፍለን እንጠጣዋለን እንጅ ጥቅሙን አላገኘነውም::

### ስለ አማራ ሕዝብ እንግልት

• አማራው እንደ አማራነቱ መከበር አለበት:: ይችን አገር የደሙ የአጥንቱ ውጤት ናት:: የአማራ ታሪካዊ ቦታዎች ወደነበሩበት መመለስ አለባቸው:: አማራ ነፍጠኛ ነው እየተባለ ለዓመታት ተገፍተዋል:: አማራ ነፍጠኛ ነው? አዎ ነፍጠኛ ነው:: አገሩን በአጥንቱ በደሙ አፅንቶ ያቆመ:: ከነጭ ወራሪ ጋር ታግሎ አገር እንደ አገር የመሠረተ ህዝብ እስከሆነ ድረስ ነፍጠኛ ነው:: በነፍጡ ነው የአማራ ህዝብ ኢትዮጵያን ሲያፀናት የነበረው::

•የአማራ ህዝብ አሁን በተከለለት የአማራ ክልል ብቻ አይደለም የሚኖረው:: በመላው አገሪቱ ተበትኖ የሚኖር ህዝብ ነው:: አማራ ናቸው፤ ነፍጠኛ ናቸው፤ መጤዎች፣ ትምክህተኛ እየተባለ ሲገደል፣ ሲጠቃ፣ ንብረቱ ሲወድም፣ ሲፈናቀል የኖረ ህዝብ ነው:: ነገር ግን አማራ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ወንድም ህዝቦች አልተገደሉም አልተጠቁም ንብረታቸውም አልወደመም:: እንዲያውም የራስ ገገዝ አስተዳደር ተብሎ ራሳቸውን በራሳቸው በክልሉ ውስጥ ያስተዳድራሉ:: ስለዚህ ከአማራ ክልል ውጪ የሚኖረው የአማራ ህዝብ መብትና ማንነቱ ሊጠበቅለት ይገባል:: የራስ ገዝ አስተዳደር በየክልሎች ያስፈልገዋል::

### ስለ አኖሌ ሐውልት

•በአገራችን ብዙ ሐውልቶች አሉ:: እኔ እስከማውቀው ድረስ አንድነትን የሚሠብኩ፤ ፍቅርና ጀግንነትን የሚያውጁ ሐውልቶች ናቸው በአደባባይ መቆም ያለባቸው እንጂ ጥላቻና ቂምን የሚሠብኩ መሆን የለባቸውም:: ለምሣሌ የኔ የመጀመሪያው አጎቴ የደርግ ሠራዊት ነበር:: አሁን በሕይወት የለም ምፅዋ ላይ ተሰውቷል:: ታናሽ የሆነው አጎቴ ደግሞ የኢህአዴግ ሠራዊት ነበር ደርግን ተዋግቶ አሸንፏል በሕይወት አለ:: ስለዚህ ወንድምና ወንድም ስለተገዳደሉ ሐውልት ማቆም አንድነትና ፍቅርን አያመጣም:: ከአማራ ክልል ውጪ ያሉ አማራዎች እንዲፈናቀሉ ትልቁን አስተዋፅኦ ያደረገው በኦሮሚያ የተገነባው የአኖሌ የሀሠት ታሪክ ሐውልት ነው:: ስለዚህ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኢትዮጵያዊነትን ደጋግመው ሲሠብኩ ስለሠማሁ የአኖሌ ሐውልት አማራና ኦሮሞን የሚያቃቅርና ጥላቻንና ቂምን የሚያመነጭ እስከሆነ ድረስ መላ ሊበጅለት ይገባል::

### ስለታሠሩ አማራዎች

•በተለያዩ የአገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ ዕንቁ የአማራ ህዝቦች ፍትሕ ሠላም አንድነትና ዴሞክራሲ ስለጠየቁ ብቻ በየእስር ቤቱ የሚሰቃዩ፣ ቶርች የሚደረጉ፣ አንተ አማራ ነህ እየተባሉ እየተሰደቡና እየተደበደቡ ብሎም ብልታቸውን እስከማኮላሸት ጥፍራቸውን እስከመንቀል የተደረሠ አሠቃቂ ለህሊና የሚከብድ ወንጀል እየተፈፀመባቸው የሚገኙ እልፍ የአማራ ህዝብ በየማጎሪያው ታጭቀው ይገኛሉ:: እነዚህ ንፁህ ዜጎች ነፃ እስካልወጡ ድረስና ከህዝባቸው ጋር ተቀላቅለው ሠለማዊ ኑሮ እስካልኖሩ ድረስ የኢትዮጵያም ሆነ የአማራ ክልል ሠላም አደጋ ውስጥ ነው::

*****

### የጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር ዐብይ ምላሽ

እንደምታውቁት ኢትዮጵያ የሁላችንም መኖሪያ መመኪያ እናት ናት:: ይሄ ክብሯ መመለስ አለበት:: ይሄን ክብሯን ለመመለስ ግን ሌላው ኢትዮጵያዊ እያስከፋን እያቆሰልን እንዳይሆንብን ግን ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: የፍላጎታችን መራራቅ የሀሳባችን መራራቅ የስሜታችን መራራቅ እንዴት ተደርጎ እንደሚሰበሰብ ይጨንቀኛል::

ሶስት ጉልበታም ግለሠቦች የሞተ በድን ያገኛሉ:: አንደኛው ጉልበተኛ “ማንነቱ አለ ይታያል አጥንቱ ተሠባበረ እንጂ ማንነቱን አላጣም:: አጥንቱን በየፈርጁ መገጣጠም እችላለሁ” ሁለተኛው “አንተ እንደዚህ የምታደርግ ከሆነ እኔ ደግሞ አፈር የሆነውን ስጋውን መልሼ አለብሰዋለሁ:: ያንተ አጥንት ይበተን እንጂ ይታየል የኔ ስጋ ግን አፈር ሆኗል አይታይም ስለዚህ እኔ እበልጠሃለሁ እሱን እመልሳለሁ” አለ:: ሶስተኛው ጉልበተኛ ደግሞ “ሁለታችሁ እንዲህ ከቻላችሁማ ያንተም ስጋ አፈር ሆነ እንጂ ይታያል የማትታየውን፤ የት እንዳለች የማትታወቀውን ነፍስ እኔ እመልሳታለሁ በዚህም ከሁላችሁም እኔ እበልጣለሁ” አላቸው::

ሶስቱ ጉልበታሞች በገቡት ቃል መሠረት የመጀመሪያው አጥንቱን ሰብስቦ የበድኑን ቅርፅ እንደነበር መልሶ ሠራው:: ሁለተኛውም አፈር የሆነውን ስጋ መልሶ አለበሰ:: ሶስተኛው በቃሉ መሠረት የበድኑን ነፍስ መለሠ:: ህይወት ዘርቶ የተነሳው አንበሳ ነበርና ሶስቱንም ሰዎች በላቸው::

ስላነበብን ስለሠማን ስላወቅን ስላየን ብቻ በዕልህ ማድረግ የምንፈልገው ነገር መልሶ

ይጎዳናል:: ለኢትዮጵያዊነት የምትንገበገቡ ሰዎች አንገታችንን ለእናት አገሬ እንስጥ የምትሉ ሰዎች ኢትዮጵያን የሚያፈርስ ስራ ከመስራት በፊት ቆም ብሉ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ልመክራችሁ እፈልጋለሁ:: የብዙ አገር ልምድ እንደሚያሳየው ዕልህ ቂም ስሜት የምትፈልገውን ነገር የሚያሳጣ መሆኑን ተረድቻለሁ:: በተለይ ወጣቶች ትንሽ ሰከን ብላችሁ በጊዜ ሂደት እየተስተካከለ መልስ እያገኘ ለሚሄድ ጉዳይ ጉልበት አታባክኑ::

አቶ አታላይ ያነሱት የወልቃይት ጉዳይ ከትግራይ ህዝብ ጋር በነበርኩበት ወቅት በጣም ደስ የሚል ድባብ ለአማራም ለኦሮሞም ህዝብ ልዩ ክብር ፍቅር እንዳላቸው የሚያሳይ ጊዜ ነበር:: ስለ ወልቃይት የማንነት ጥያቄ በፍፁም አላነሱልኝም:: አንድ ወንድም ቦታ ሳይጠቅሱ ግጭት የሚቀሰቅሱት ዲያስፖራዎች ናቸው የሚል ጥያቄ ሲያነሱ መልስ ስሰጥ ዲያስፖራ ሀገሩን አይጠላም በሚል የወልቃይትን ጉዳይ ሜንሽን አድርጊያለሁ:: ከዛ ጋር የተያያዘ እንጅ ከማንነት ጋር አይደለም:: መከፋቱም ከዚህ የመጣ ነው:: በዚህም ምክንያት ሕዝብ አኩርፎብሃል አትሂድ ተብዬ ነበር:: እኔም ቢበዛ ቆንጥጠው ቢያስተምሩኝ ነው ብየ መጥቻለሁ::

ይሄ ጉዳይ ከማንነት ጋር ተያይዞ እዛ አካባቢ ያለውን ህዝብ እንዲያሳዝን በፍፁም አልፈልግም:: የወልቃይት የቅማንንት የጠገዴም ሆነ የሌሎች በየቦታው የተፈጠሩ የማንነት ጥያቄዎች ህግና ህገመንግስቱን ተከትሎ ብቻ ይፈታል:: በስብሰባ፣ በአዋጅም በአንድ መሪም ንግግር የሚመለስ ጉዳይ አይደለም::

ከሱዳን ጋር ያለው ጉዳይ መንግስታት የተፈራረቁበት ያልተፈታ ጉዳይ ነው:: በሱዳን በኩልም ጥያቄው ከረር ያለ ነው በእኛም በኩል እንዲሁ:: ከሱዳኑ ፕሬዝዳንት ጋር ባህርዳር ነገ ስንገናኝ ላነሳላቸው የምችለው ጉዳይ ከዚህ ወዲያ ያለው ስፍራ የኛ ስለሆነ ልቀቁ አይደለም:: የማነሳላቸው ከእርስዎም ከእኛም ወገን ወታደር ይሸሽ ህዝቡም በሠላም እየኖረ ሌላውን ደግሞ በጋራ ኮሚሽን ተዋቅሮ መፍትሔ እናበጅለት ነው የምላቸው::

ወሬ በዛ ንግግር በዛ የሚለው ሀሳብ ትክክል አይደለም የተግባር ምንጩ ሀሳብ ነው:: ከሀሳብ ቃል ይወጣል:: ቃል ጉልበታም ነው ቃል ይተክላል ቃል ይነቅላል:: ቃል ነው እንደዚህ ዓይነት ቂም ጥላቻ በውስጣችን እንዲኖር ቁስል እንዲሆንብን ያደረገው:: ሳይጮህ ሳያስብ ሰው ሳይናገር ተግባር የሚባል ነገር ግልብ ነገር ነው:: መጀመሪያ ቀና ቀናውን ማሠብ ደግደጉን መናገር የተናገርነውን ተደምረን መፈፀም ነው:: ቃልን የማራከስ ሀሳብ በውስጥ ብዙ ጉዳይ ስላለው እንድታስቡበት ብዬ ነው::

መናገር ቀላል ነው የተባለው መናገር ቀላል አይደለም:: መናገር በጣም ከባድ ነው:: እዚህ እናንተ ጋር እኮ ስናገር ስንት የሚያኮርፍ አካል አለ መሰላችሁ:: ብንደማመጥ ብንግባባ የበለጠ የሚገርፍ የበለጠ የሚሰቅል ንጉስ ሊሾም እንደሚችል ስለሚያውቁ ሁለት አማራጭ ለኔ አስቀምጠውልኛል:: የኔ ሀሳብ የእነ አባ እና ሸሁ ፀሎት ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ፀሎታቸውንም እንደማይለየኝ አምናለሁ:: የሆነ ሆኖ ልጅ የፈለገውን ሁሉ አባት አይሠጥም:: ህዝብ የጠየቀውን ሁሉ መንግስት አይመልስም:: ብዙ ግራና ቀኝ ማየት የሚገባን አንዳንዶች በይደር የምናቆያቸው ጉዳዮች መኖራቸው እንደማይቀር ለማስገንዘብ እወዳለሁ::

የኢትዮጵያ ፍቅርና አንድነት እንዲህ እያንገበገባችሁ መልሳችሁ ደግም አማራ አማራ እያላችሁ ታፈርሱታላችሁ:: አማራ ክብር ይገባዋል አማራ ደምቷል ሞቷል ማንም ይናገረዋል:: እውነትም መነገርም አለበት ግን ይቺን አገር ብቻውን አላቆማትም ብቻውንም አልሞተም:: ከወንድሞቹ ጋር ሞተ ከወንድሞቹ ጋር ይቺን አገር አቆመ:: አሁንም ትርፍ አልጠየቀም ከወንድሞቹ ጋር ዕኩል እንሁን ነው ያለው:: እዛኛው ጋር ስትሄድ ይቺ አገር በእኔ ነው የቆመችው ካለ፤ እዚህ ስትመጣ እኔ ነኝ የዚች አገር ካስማዋ የሚል ከሆነ እንዴት አንድ ልንሆን እንችላለን? ለኢትዮጵያ ያልደማ ያልሞተ ያልቆሰለ የለም:: ለኢትዮጵያ ተጎድተናል፣ ተሠደናል፣ ታርደናል፣ ክፋት በዝቶብናል እውነት ነው:: ይሄ ጉዳይ ይስተካከል ከሆነ እኔም እስማማለሁ:: ግን አማራው ቁጥሩን ከፍ አድርጎ የሚናገር ኦሮሞውም ቁጥሩን ከፍ አድርጎ የሚተርክ ከሆነ ሌላውም እንዲሁ ወደ ራሱ ጥግ የሚዘምት ከሆነ ልንግባባ አንችልም:: እንደዚህ ባይሆን ባንካረር ትንሽ የሚዘልቀውን ነገር እያሠብን ብንወያይ መልካም ነው::

የኛ ሀሳብ አይጠቅመንም ከንቱ ነው የምትሉ ትደራጁና ትታገላላችሁ:: በሀሳብ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ያለንን ለህዝቡ እናቀርባለን ህዝቡ የፈለገውን ይመርጣል:: ካሸነፋችሁ በደስታ እለቅላችኋለሁ::

ከኦሮምያ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አንስታችኋል ትክክል ነው ኦሮምያ ውስጥ ችግር ነበር ከአማራም ከሌላውም ብሔር ኦሮምያም በጣም ተበድያለሁ ብሎ የሚያስብ ህዝብ ስለሆነ አሁን ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆንኩ በኋላ ለምን ታነሳላችሁ? ከመሆኔ በፊት እኮ ይሄ ጉዳይ ይቁም ብለን ህዝብ ይዘን ጣና ድረስ መጥተ ከናንተ ጋር ተወያይተን የሚያስደንቅ ፍቅር እኮ ነው ያለው አሁን እሱ እንዲፈርስ ነው የምትነግሩት? ይሄን እየቆጠርን ከሆነ አይሆንም የኦሮሞ ህዝብ የትግራይ ህዝብ የአፋር ህዝብ ወንድሜ ነው ተሳስቻለሁ ባለበት ዘመን ይሄ መልካም ሀሳብ ይዝለቅ ይቀጥል እንዳይመለስ አጠናክረው ብትሉኝ ሞራል ይሰጠኛል:: የተሠራውን እንደሌለ ካሰባችሁ ግን መጥፎ ነው:: ለምን ችግር ተፈጠረ የሚል ሀሳብ ስህተት ነው:: ወደፊትም ይፈጠራል ግን ያንን ችግር የምንረዳበትና የምንፈታበት ቀና ሀሳብ ይኑረን:: እኔ ከአማራም ከኦሮሞም በላይ ሱዳናዊ ከመጣ ጀርመናዊው ከመጣ እንደ ሰው የሚከብርበትና ሰው ክቡር መሆኑን የምናስብበት ጊዜ ይምጣ ባይ ነኝ:: ሰው ክቡር መሆኑን ስናስብና የአማራ የኦሮሞው የሌላው ጉዳይ እያነሰ ነው የሚሄደው:: አሁን ሰው ነው ክብር ያጣው:: ሰው እየተዋረደ ነው እኔ ባደኩበት ሰፈር ግሪኮች ነበሩ የጣሊያኖች ጋራዥ ያላቸው ነበሩ:: በኢትዮጵያ ጫፍ፣ በእኛ መንደር በሰውነቱ ብቻ የሚኖርበት አካባቢ ነበረን:: አሁን ችግሩ የየመንና የግሪክ ሳይሆን የአማራና ትግራይ ኦሮሞ ሆኖ አሳፋሪ ደረጃ ደረሰ ማለት ነው::

ዓለም ለሁሉም ሰው መዘዋወሪያ ስትሆን ጥሩ ነው:: አሜሪካን አገር ተሰደው ተቸግረው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ትንሽ እንደቆዩ ዜጋ ይባላሉ:: እዚህ ተወልደው እዚሁ አድገው እንግሊዝኛን በቅጡ የማይናገሩ ሰዎች ኢትዮጵያዊ ነህ አንተ ጥቁር ነህ ሳይባል ዜጋ አድርጎ አቅፎ የሚያኖር ዓለም ባለበት፤ እንዴት ኢትዮጵያዊያን በደም በጋብቻ በዝምድና የተቋለፉ ዜጎች ኢትዮጵያውያን ሄዶ መኖርን ዋና አጀንዳ መነጋገሪያ ይሆናል?

ይሄንን ዘር ዘር አድርጌ ላለመናገር አንድ ምሣሌ በመጥቀስ ላጠቃለው:: ዲያቆን ዳንኤል ክብረት የሚባል በጣም ታዋቂ ጸሐፊ አለ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን የሚጽፍ:: በአንድ ወቅት የጻፈው ሀሳብ ላይ ያነበብኩት የሚገርመኝ ለእኛም ኢትዮጵያዊያን የሚበጅ ነገር ልክ አሁን እኛ ጋር እንዳለው ስሜት በአንድ ወቅት ጫካዎችም ያምፃሉ:: ቀስቃሾቹ ጥድና ባህር ዛፍ ናቸው:: ከቀሰቀሱ በኋላ ሌሎች ገራገር ዛፎች አልተከራከሩም:: ወይራ ግን በባህሪው ትንሽ አርቆ አሳቢ ስለሆነ ጥያቄ አነሳ:: ተው ይሄ ነገር አይጠቅምም በኛ ውስጥ ያሉት እንሰሳት ብዙ ባይጠቅሙንም ከእነሱ የሚፈጠረው ነገር ለእኛ ምግብ፣ ማዳበሪያ ነው አብረን ብንኖር ብዙ አልተጎዳንም ተው ይቅርብን አላቸው:: አንተ ክፉ አንተ ቀጫጫ እያሉ የርግማን ናዳ አወረዱበት ሠደቡት በድምፅና በጩኸት ብዛት ወይራን አሸነፉት:: ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚደረገው በጭብጨባ ብዛትማለት ነው:: እውነትን በጭብጨባ በድጋፍ በማሸነፍ አይችሉም የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው:: ወይራ ላይ ጮኹበት እንደተባለውም አዋጅ ታወጀ ከዛሬ ጀምሮ በጋራ አንድ ሆነን በውስጣችን ያሉ የሚበዘብዙን በእኛው ውስጥ ተደብቀው የሚኖሩትን እናጥፋ ተባለ:: ጠዋት በቅርንጫፎቻቸው አርጩሜ እየገረፉ ሲያስጮሁ ዝንጀሮም ጦጣም አንበሳም ነብርም አዲስ ነገር ተፈጠረ ብለው ግርታና ጩኸት ሲበዛባቸው ተሠደዱ:: እናም ዛፎች ጨፈሩ ባህር ዛፍና ጥድም አሸነፉ:: የአሸናፊነት አመራር አካሂደን ከውስጥ ጠላቶቻችን ሸሹ ብለው ፎከሩ::

ግን አልቆዩም ከጊዜ በኋላ ሰው እዚህ አካባቢ የነበሩ አስፈሪና አደገኛ እንሰሳት እንደሄዱ ስለሚያውቅ መጥረቢያውን ይዞ ወደ ጫካ መጣ:: ይሄንንም ያዩት ባህርዛፍና ጥድ ናቸው ረዘም ያሉ ስለሆኑ ጉድ ፈላ ጠላት መጣብን ብለው ወይራ ጋር ሄዱ:: ያ የተገፋው ወይራ በጭብጨባና በጩኸት የተወገዘው ወይራ ቀን ወጣለትና ምን ይሻላል የሚል አቤቱታ ቀረበለት:: አሁን እኔም ተገለጠልኝ ያኔ የነበሩት የዱር እንሰሳት ለኛ ጥቅማቸው ከነሱ የሚወጣው ነገር ብቻ ይመስለኝ ነበር:: አሁን ሲገባኝ ከዚያ የበለጠ ጥቅማቸው ጎልቶ ታየኝ:: ለካ ጠባቂዎቻችን ማስፈራሪያዎቻችን ጌጦቻችን እንደነበሩ አላወቅሁም ነበር አሁን አልፎበታል አለ:: ሰውም ለመጥረቢያ ያንን ጫካ ጨፈጨፈው:: እዚህ ጋር ዳንኤል ከፃፈው ትንሽ ለማሻሻል የዚህ ሰው ጉልበትም ጊዜያዊ ነበር:: መጥረቢያውን በያዘ ጊዜ ደኑን ጨፈጨፈ የጊዜ ጉዳይ ነው:: እነሱም የአየር ንብረት አዛብተው መልሰው ጨፈጨፉት::

ሰውን በጨፈጫፊነት በጉልበት በኃይል ዘላቂ ድል ማረጋገጥ አይቻልም:: ዘላቂ ሠላም ፍቅር አንድነት የምናስብ ከሆነ ከሁሉም በላይ የይቅርታን ልብ ሊኖርን ይገባል:: የይቅርታ ልብ ሳንይዝ ለመተው ሳንዘጋጅ ስንት ያቆሳሰለን ነገር ባለበት አገር ታሪካችን በሙሉ በብዙ ቁስል ውስጥ ያለፈ ነው:: በዚህ ጊዜ እንዲህ አድርገሃል እያልን እየተወቃቀስን አይሆንም:: ኢትዮጵዊነት ተክዷል ብዙዎች አይፈልጉትም መጠገን አለበት:: ሰው ሆኖ እንዴት ኢትዮጲያዊነት ይክዳል ልትሉ ትችላላችሁ:: ሰው እንኳን ኢትዮጵያን አምላኩን ይክዳል ሰው ሠይጣን ከአምላክ እንደማይሻል እንደማይበልጥ ያውቃል ግን ይክዳል:: ኢትዮጵያዊነት ተክዷል መታከም መጠገን ካለበት ጊዜ ያስፈልገዋል:: በአንድ ጀምበር በአዋጅ ይሆናል ብላችሁ አታስቡ:: አድካሚ ሥራ እንደሆነ ብትረዱ መደጋገፍ እንደሚስፈልግ ብታስቡ::

እኛ የበቃ ሰው የለንም የበቃ መሪ የለንም የበቃ መሪም የለንም:: የበቃ መሪ የሚያፈራ ሥርዓትም የለንም:: የሚኮረኩም እንጅ መሪ የሚሆን ሥርዓት አልነበረንም:: የሾምናቸው ሰዎች ተለማማጅ ተማሪዎች ናቸው:: የኛን ፍላጎት ብቻ ጭነን ስለማንዘልቀው የሌላውን ፍላጎት አቅፈን ለመሄድ የጋራ መድረክ ስፈልጋል የሚለውን ነገር አምንበታለሁ ይሄን እናደርጋለን::


# “15 ዓመት እንደሚፈረድብኝ ከዳኞች በፊት ደሕንነቶች ነግረውኛል”

## አቶ ኦልባና ሌሊሳ

*ኦልባና ሌሊሳ ኦልጀና በምዕራብ ሸዋ ጨሊያ ተብላ በምትጠራው ከተማ ነው የተወለደው:: ዕድገቱ ግን አምቦ ከተማ እንደሆነ ይናገራል:: ከበርካታ የፖለቲካ ሰዎች ለየት ባለ መንገድ ነው ወደ ሠላማዊ ትግሉ መድረክ የተቀላቀለው፤ ከልጅነቱ ጀምሮ በትውልድ አካባቢው ላይ ሰዎች ኃይልና ሥልጣንን ተጠቅመው ንፁሃንን ሲበድሉ ሲመለከት ዐቅሙ የፈቀደውን ከማድረጉ ወደኋላ ብሎ አያውቅም::*

*ወደ ስራ ዓለም ከገባ በኋላ በሚገጥሙት አንዳንድ ነገሮች ላይ የሚሰጠው ጠንከር ያለ አስተያየት በኃላፊዎች ዘንድ “ተቃዋሚ” “ፀረ ልማት” የሚሉ ስያሜዎች አሰጡት:: ዘግየት ብሎም ኦሮምያ ውስጥ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በበቂ ሁኔታ መገንዘብ በመቻሉ የሲቪል ስራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ በ1992 ዓ.ም ኦብኮን (የአሁኑ ኦፌኮ) ተቀላቀለ::*

*ከሰባት አመት በፊት በድርጅቱ ውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ተከትሎ በተመሰረተበት የሽብርተኝነት ክስ የአስራ አንድ አመት እስርና የአራት አመት እግድ ተፈርዶበት ሰባት አመታትን በማረሚያ ቤት ካሳለፈ በኋላ በቅርቡ መንግስት ለፖለቲካ እስረኞች በሰጠው ምህረት ተፈትቷል:: እኛም በእስር ቆይታውና በተለያዩ ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪይ እንዲህ ባለመልኩ አነጋግረነዋል::*



**ግዮን፡-በ2003 ዓ.ም ለእስር የተዳረግክበት ጉዳይ ምን እንደነበር በማስታወስ ውይይታችንን ብንጀምር?**

ኦልባና፡- የተያዝኩት ነሐሴ 2003 ዓ.ም ነው፤ እናንተ እስር ብትሉትም ለእኔ ግን ያ ሁኔታ እስር አይደለም:: በጊዜው ከእነ በቀለ ገርባ ጋር ነው አብረን የታሰርነው:: በቀለ የእኔ አባሪ ነበር:: ወደ እኔ እይታ ስንመጣ መያዜ ለእኔ የስራ አድራሻ ለውጥ እንጂ እስር አልነበርም:: እንደውም እንደታሰርኩ የተሰማኝ ከተፈታሁ በኋላ ነው:: እኔ ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ አንድ ባህል አለ፤ አብሮ ገበያ የሄደን ሰው ጥለህ አትገባም:: ብትውልም ብታድርም ይጠብቅሃል:: ተያይዘው የወጡ ሰዎች ተይይዘው ነው የሚገቡት:: እኛን ተከትለው ሰላማዊ ትግል ያደረጉ ብዙ የኦሮሞ ልጆች እኛ ስንፈታ እነሱ አሁንም አልተለቀቁም::

ሚቼ ጠ/ሚኒስትርም ሆነ የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ‹‹እኛ ጉዳያችን ከላኪዎቹ እንጂ ከተላላኪዎች አይደሉም›› ይሉ ነበር:: ለዘመናት በስፋት ሲናገሩ የነበረው መታሰር ያለባቸው ዋናዎቹ ናቸው እያሉ ነበር:: አሁን ደግሞ ነገሩ ተገለበጠና.. የህዝቡ ጫና ሲበዛ፣ የእኛ ስም በየሚዲያው ሲነሳ ፤በእነሱ ተልካችሁ ነው የመጣችሁት ያሏቸውን ልጆች ይዘው እኛን ለቀቁ፤ ይህ ሁኔታ ነው ከተፈታሁ በኋላ ነው የታሰርኩት ያስባለኝ::

ወደ እኔ የተያዝኩበት ነጥብ ስንመለስ በጊዜው የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰብአዊ መብት ጉዳይ መረጃ እየሰበሰቡ ነበር:: ከደቡብ በየነ ጴጥሮስን ጠየቁ፣ ከኦሮምያ ዶ/ር መራራ ጉዲናን ሲፈልጉ በጊዜው እሱ ስላልነበረና የሚቀጥለው ሰው እኔ ስለነበርኩ መረጃውን ለመስጠት ቢሮ ተቀጣጠረን መጡ:: ከባህር ማዶ ሰዎች ጋር ብዙ ጊዜ በኦሮምያ ውስጥ ስላለው ችግር ተነጋግረን ምንም መፍትሔ ስላልሰጡን እኔ በሰአቱ መረጃውን ከማቅረብ ውጭ ብዙም አልተነጋገርኩም:: እንዳይጠራጠሩ ደግሞ የተወሰኑ ሰዎችን የችግሩ ባለቤት ናቸው አነጋገሯቸው ብዬ አቀረብኩ:: ያኔ የደህንነት ሰዎች እነሱ ሲገቡ እየቀረፅዋቸው ነበር:: እኔም ከዛ በፊት በየጊዜው ከኋላዬ ስለሚከታተሉኝ ብዙም አልተገረምርኩም፤ የአምንሲቲ ሰዎች ሃሙስ ነው የመጡት ፤እኔ ቅዳሜ ጠዋት ተያዝኩ::

**ግዮን፡- የት ቦታ ላይ ነው የያዙህ?**

ኦልባና፡- በእለቱ መጀመሪያ ላይ ሲቪል የለበሱ ሰዎች ቢሮ አካባቢ ነበሩ:: ገንዘብ ለሰራተኞች የሚከፈል ከባንክ ለማውጣት ስሄድ አብረውኝ ሄዱ:: ያው የተለመደው ክትትል መስሎኝ አብሬያቸው ሄድኩኝ:: ገንዘቡን አውጥቼ ስመለስ መንገድ ላይ ቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስትያን ጋር ነው የያዙኝ:: አያያዛቸው ላይ ምን እንደፈለጉ አላውቅም:: መያዣ ወረቀት የያዙ ሰዎች እኔ ጋር አልመጡም:: እኔም ያለ ማዘዣ ወረቀት አልያዝም ብያቸው አምባጓሮ ተፈጠሮ ነበር:: በኋላ መያዣ የያዙት ሰዎች ከሌላ ቦታ በመኪና መጡ:: በቀጥታ ቤቴ ሄደው ፍተሻ ጀመሩ፤ እዛ ባደረጉት ብርበራ ምንም ነገር ሊያገኙ አልቻሉም:: ሲፈተሽ የነበሩት አካላት በስልክ ሪፖርት ሲያደርጉ ቤት ውስጥ ምንም የለም፤ መፅሃፍ ቅዱስና የመዝሙር ሲዲ፣ከእጮኛዬ ጋር በኦሮሞ ባህል ልብስ የተነሳነው አንድ ፎቶ እንዳገኙ፤ሌላ ነገር ግን እንደሌለ ይገልጻሉ:: በኋላ ላይ አንድ ትግረኛ ተናጋሪ ፖሊስ መጣና የሆነ ወረቀት አውጥቶ ይሄ ከአንተ ቤት የተገኘ ነው አለኝ፤በጊዜው የወረቀቱን ይዘት ስላላወቅኩ ያለመግባባት በመሃላችን ተፈጠረ… ወደ ቃሊቲ ከወረድኩ በሁዋላ ስመለከተው ወረቀቱ ከኢንተርኔት የወረደና ቀደም ሲል የተያዙ የእኛ አባሎች የክስ ወረቀትና እኛ ያወጣነው መግለጫ ነበር::

**ግዮን፡- በማዕከላዊ የነበረህ የምርመራ ሂደት ምን ይመስል ነበር? እግረ መንገድ የተመሰረተብህንም ክስ በዝርዝር ብትገልፅልን?**

ኦልባና፡- ክሱ ያው የተለመደና ሁሉም የፖለቲካ ሰው ላይ የሚለጠፈው የሽርብርተኝነት ክስ ነው:: ከኦነግ ጋር ግንኙነት አለህ ገንዘብ ትቀበላለህ፣ መሳሪያ ታዘዋውራለህ አባሎች ትመለምላለህ፣የሽብር ተግባር ለመፈፀም ስትንቀሳቀስ ደርሰንብሃል የሚል ነው:: እኔም የሚሉትን ነገር እንደማላውቅና በኦሮምያ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ግን ከድርጅቱ ጋር በሰላማዊ መንገድ እየታገልኩ መሆኔን ገለፅኩ::

በምርምራ ረገድ እኔ ላይ በቀጥታ ምንም ነገር አላደረጉም፤ ግን በተዘዋዋሪ እኔ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ሞክረዋል:: አብረውኝ የታሰሩ ልጆችን በየቀኑ ማታ ማታ እየወሰዱ በመግረፍና በማሰቃየት እኔን ለመረበሽ ሞክረዋል:: ልጆቹ የሚፈፀምባቸው በደል በጣም ዘግናኝ ነው፤ ሰውነታቸው ተበላሽቶና ራሳቸውን ስተው በደም እንደተለወሱ እኔ ጋር ይመልሷቸዋል:: በርግጥ የልጆቹ ስቃይና ልቅሶ፣ የሚደርስባቸው ግፍ ውስጥህን ይበላዋል:: አንጀትህ ይንሰፈሰፋል፤ ሁሌም የሚያንገበግበኝ በሰዎች ላይ የሚደርሰው በደል ነው::

ከተያዝኩ በኋላ ቤተሰቡም ሆነ ሌላ ሰው እንዳይጠይቀኝ ተደርጎ ነበር:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ባለቤቴ እንድታየኝ ተደረገ:: ሆን ብለው ያቀዱት ስራ ነው… ወጥቼ ገና ስታየኝ ፊቷ ላይ ያየሁት ሃዘን፣ብሶትና እንባ እስካሁን ድረስ በእድሜዬ ማንም ሰው ላይ አላየሁም:: ወደፊትም አላይም… ከቁጥጥር ዉጭ የሆነ የብሶት ልቅሶ ታለቅሳለች:: ምን እንዳደረጓት አላውቅም፤ ከእስር ቤት ሳትወጣ አልነግርህም ብላኝ ነበር:: እኔ ስፈታ ደግሞ “እዚህ አገር መኖር አልቻልኩም” ብላ አገር ለቃ ሄዳለች:: ግን ምን እንዳደረጓት እስካሁን ድረስ አላወቅኩም:: በዚህ መንገድ ቤተሰቤን በመበተን፣ ሌሎች የኦሮሞ ልጆች ላይ በሚፈፀሙ ስቃይ እኔን ቶርች ለማድረግ ሞክረዋል::

ግዮን፡- በሌሎች እስረኞች ላይ ከሚደርሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት አኳያ በማዕከላዊ ምን ታዘብክ?

ኦልባና፡- በማዕከላዊ አርባ ሁለት ቀን ነው በእስር የቆየሁት:: እኔን ለምርመራ የጠሩኝ ሁለት ቀን ብቻ ነው… ግን በእነዛ ቀናት ብዙ ሰዎች በምርመራ ሰበብ ተገልብጠው ተገርፈዋል፤ ህገ ወጥ የሆነ ዘግናኝ ድብደባ ተፈፅሞባቸዋል፤ሰብአዊ ክብራቸው ተጥሷል፤ሰዎች አካላቸው ይጎድላል፤ ብዙ ወጣቶች ገላቸው ርህራሄ የለሽ በሆኑ የማዕከላዊ ገራፊዎች ተበላሽቷል፤ የሰው ልጅ ላይ ሊደረጉ የማይገቡ ለዛውም የአገር ዜጋ በሆኑ ሰዎች ላይ መፈፀም አሳፋሪ ነው:: አሁን ኢህአዴግ ዘጋሁ የሚለው ይሄን ተቋም ነው::…ግን መረሳት የሌለበት ጉዳይ ሌሎች ሰባትና ስምንት ድብቅ ማዕከላዊ እስር ቤቶች አሉ፤ ከዚህ ያልተናነሰ በደል የሚፈፀምባቸው:: ዜጎች የሚሰቃዩባቸው ድብቅ እስር ቤቶች… ብዙ ጊዜ ሰው ተይዞ ወደ እነዚህ ስፍራዎች ነው የሚወሰደው፣እዛ ተደብድበህ አጋጣሚ ሆኖ ብትድንና ብትተርፍ ነው ወደ ዋናው ማዕከላዊ የሚያመጡህ::

በማዕከላዊ ትልቅ፣ ወጣት ሳይባል ሁሉም እስረኛ ነው የሚሰቃየው፤ አንድ አብረውኝ የታሰሩ ትልቅ ሰውዬ የነገሩኝን ነገር ላጫውትህ:: በምርመራ ወቅት ደብድበውኝ፣ደብድበውኝ ምንም ነገር አላገኝ ሲሉ አንዱ የበሬ ማኮላሻ ይዞ መጣ አሉ:: ይህ ሰው ማን እንደሆነ ከመነሻው ስለማውቀው ብዙም አልገረመኝም፤ ዛሬ ትልቅ ባለስልጣን ነው:: የፖለቲካ ሰው ነኝ ብሎ መድረክ ላይ ቁጭ ብሎ የሚነጋገር ሰው ነው፤ በጣም አስከፊ በደል የሚፈፀምበት ይህ ተቋም ከመዘጋቱ በዘለለ በሰራተኞች ላይ ነው የአስተሳሰብ ለውጥ መምጣት አለበት:: አንዱን ዘግተህ ዘጠኙን በድብቅ ብትከፍት ምንም ዋጋ አለው:: የምር ለመወለጥ ከታሰበ በትክክል ሁሉንም መዘጋት ያስፈልጋል::

ግዮን፡- በቂሊንጦና በቃሊቲ ቆይታህስ ምን አይነት ነገሮች ገጠሙህ?

ኦልባና፡- እዛ ከቤተሰብ እንዳልገናኝ፣ ህክምና እንዳላገኝ ተደጋጋሚ በደሎች ተፈፅመውብኛል:: ይሄ የሚጠበቅና የተለመደ ነገር ስለሆነ ብዙም አልተገረምኩም:: ሌሎች እስረኞች ግን በእነዚህም ቦታዎች በስቃይና በችግር ውስጥ ነው ያሉት፤ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው የምትመለከተው፤ ለምሳሌ አንድ በጥይት ተመትቶ የታሰረ ወጣት ታሪክን ልንገርህ… አሁን በእስር ላይ ወደ አስራ ሶስት አመት ሆኖታል:: በጊዜው በጥይት ተመትቶ ነው ፖሊስ የያዘው፤ ልጁን ጥይት ይምታውም ፈንጂ ላይ ይውደቅ ግን አንድ እግሩ ነው የተጎዳው፤ ይሄን ልጅ ፖሊስ ይዞት ሆስፒታል ሲወስደው ሐኪም ደህነኛውን እግሩን ቆርጦታል:: በህክምና ስህተት ነው እንዳይባል ጥይት የመታውና ጤነኛ እግር እንኳን ለዶክተር ለማንም ግልፅ ነው፤ አሁን ይህ ወጣት ሁለት እግሩ ተቆርጧል:: ቃሊቲ ዞን አራት ብትሄድ ታገኘዋለህ:: ከበደ የሚባል የኦሮሞ ተወላጅ ነው፤ እኛ ስንፈታ እንኳይሄ ልጅ አልተለቀቀም፤ ምን አደርጎ ነው እንዲህ የሚሰቃየው?

ከዚህ ውጪ 25 አመት ሙሉ ሞት ተፈርዶባቸው ከዛሬ ነገ ሞታቸዉን የሚጠባበቁ እስረኞች አጋጥመውኛል:: ሃያ አምስት አመት ሙሉ፤ ቢያንስ ወደ እድሜ ልክ ቢደረግላቸው እንኳ አምስት አመት ትርፍ ይኖራቸው ነበር:: በብሄር ጉዳይ ብቻ አስርና አስራ አምስት አመት የተፈረደባቸው እስረኞች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው፤ እንግልት፣ድብደባና ስቃዩ ሳይረሳ ማለቴ ነው::

ግዮን፡- የተከሰስክበት ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ከተዛወረ በኋላ ያለውን የህግ የበላይነት እንዴት አገኘኸው?

ኦልባና፡- እኔ መጀመሪያ ከሰባት አመት በፊት ፍርድ ቤት ስቀርብ የቀረቡብኝ ማስረጃና ምስክሮች በሙሉ የሃሰት ስለነበሩ፣ ፍርድ ቤቱም በትክክል ፍትህን ይሰጠኛል ብዬ ስላለመንኩ ችሎት ላይ ‹‹እኔ ገና ስያዝ ከአራት ወር በፊት 15 አመት እንደሚፈረድብኝ፣ አንዳንድ ነገሮችን ካደረግኩ ደግሞ ወደ 10 አመት ዝቅ እንደሚልልኝ በደህንነቶች በግልፅ ተነግሮኛል:: ስለዚህ እናንተ ታዛዥ ከሆናችሁ እኔም አልመላለስ፣ ቤተሰቤም አይልፉ የተባለውን ነገር ወስኑብኝና ወዳስቀመጣችሁኝ ቦታ ልመለስ›› ስል ዳኞች እንዴት እንዲህ ትላለህ በሚል ቡራ ከረዩ አሉ… ግን መጨረሻ ላይ እንደተነገረኝ 13 አመት እስርና የአራት እመት ገደብ ነው የጣሉብኝ:: በኋላ ይግባኝ ብዬ እንደ መጀመሪያ ውላችን …(ሳቅ) አስራ አምስት አመት እንዲሆን ባልኩት መሰረት አስራ ሶስቱ ወደ አስራ አንድ ዝቅ ሲል ገደቡ ግን ባለበት ፀና…እንግዲህ የእኛ አገር የህግ የበላይነት ይሄ ነው፤ የእስርህ መጠን ቀድም ተብሎ በደህንነት ይነገርሃል::

ግዮን፡- በቅርቡ ዶክተር አብይ አህመድ ጠ/ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል:: እንደ አንድ የፖለቲካ ሰው የኢትዮጵያ ቀጣይ እጣ ፈንታ ምን ገጽታ ይኖረዋል?

ኦልባና፡- ሰው በተፈጥሮው የመለወጥ የመድከምና የመጠንከር ባህሪይ አለው፤ ስለዚህ ሰዎችን እንደ ሰውነታቸው ለብቻ፤ኢህአዴግን እንደ ኢህአዴግነቱ ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል:: ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ማዕከልነትን የሚጠብቅ ድርጅት ነው፤ አንድ ሰው ኢህአዴግ ውስጥ ሆኖ ከኢህአዴግ ፍላጎት ውጪ ማሰብና መንቀሳቀስ ይችላል? የሚለውን ነገር ሁለችንም በደንብ መመልከት ያለብን ይመስለኛል:: የሰውዬውን ፐርሰናሊቲ ትተን ማለት ነው:: ከዚህ በፊት እነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣አንዳርጋቸው ፅጌ፣ እነ ከማል በድሪ ከኢህአዴግ ጋር ነበሩ፤በኋላ ጥለው ወጡ፤ እንደሰው ሲያንገሽግሽህ ጥለህ የምትሄደው ነገር አለ፤ ኢህአዴግ ግን የመለወጥ ፍላጎት የለውም፤ ስርአቱ አምባገነንነት መለያው ስለሆነ:: አምባገነኖች በምንም ተአምር 180 ዲግሪ መዞር አይችሉም::

አምባገነኖች ወደ ኋላ መመለስን፤ ዞሮ ማየትን አይፈልጉም:: እግዚአብሄር ለፈርኦን ብዙ ተአምራቶችን አሳይቶት ነበር፤ ግን አልተመለሰም ፤እስከ የት? እስከክ ባህር ድረስ፤ የመመለስ ቻንስ ያለው ሰው ግን በጣም ልዩና እድለኛ ሰው ነው፤ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከምድራዊ መሪ ይሄን ያደረገው ንጉስ ዳዊት ብቻ ነው::… አንድ ጊዜ በወንጀል ቀጠለ፤ የሆነ ቦታ ላይ 180 ዲግሪ ወደኋላ ዞሮ ነገሮች ስህተት መሆናቸውን ተገነዘበ:: መጽሐፍ ቅዱስ ጠቢብ ብሎ የመሰከረለት ንጉስ ሰለሞን እንኳን ወደኋላ መመለስ አልቻለም::

ስለዚህ ዶክ/ር አብይ ቢመረጡም ኢህአዴግ ከገባበት መስመር ይወጣል ብዬ ተስፋ አላደርግም:: ወደ ንግግር ይዘቱ ስንመጣ እኔ በግል አቶ መለስ ዜናዊ በሚናገሩት ንግግርም ቢሆን በአብዛኛው እስማማለሁ:: ችግሬ ከሚሰሩት ጋር ነው ፤የሚናገሩትና የሚሰሩት ለየብቻ ነው:: በመሆኑም ዶክተር አብይ አሁን የሚናገሩት ነገር የራሳቸው አቅም ነው፤ የድርጅታቸው አቅም ነው የሚለው ሌላ ጉዳይ ቢሆንም ንግግራቸው በጣም ያማረና እንከን የማይወጣለት ነው፤ ስለዚህ በመጡበት መንገድ አሁንም ለመራመድ የሚያስችላቸው ክፍተት ከተፈጠረላቸው ወደ ፊት ብዙ ነገር ይሰራሉ ብዬ እንድገምት ያስገድደኛል:: ግን ላለፉት 27 አመታት የሃይል ሚዛኑን ይዘው ከቆዩት ሰዎች ጋር እንዲህ በቀላሉ ሊግባቡና ሙሉ የበላይነቱን በእጃቸው ሊያስገቡ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጉዳይ አሳሳቢ ነው፤ ይህ ቢሆንም ዶክተር አብይ እንዲህ በቀላሉ የህዝብ አመኔታን አሳልፈው ይሰጣሉ፤ ነገሮች ሲበላሹ እጃቸውን አጣጥፈው ቁጭ ብለው ይመለከታሉ ብዬ አላስብም::

ግዮን፡- አዲሱን የካቢኒ ምስረታስ እንዴት አገኙት?

ኦልባና፡- ከተቃዋሚ ፖርቲዎች ጋር እንደራደር እያለ በሌላ ጎን እንደ ልብ እንዳይንቀሳቀሱ የሚገድበውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጡ ግለሰቦች ናቸው እየተሾሙ ያሉት፤ የመለወጥ ነገር በኢህአዴግ ላይ አይታይም ያልነውን የሚያጠናክር ነው:: የካቢኔው ሹመት ብዙም ለውጥ የለውም:: የተለሳለሰና የተመሳሰለ ነው፤ እኔ በግል የተለየ ነገር አይቻለሁ ማለት አልችልም፤ የነበሩት ሰዎች ቦታ ነው የተቀያየሩት፤ትንሽ ጥሩ ጎን ቢኖረውም::

ይሄ በአንድ በኩል ኢህአዴግ ተተኪ አለኝ የሚለውን ጉዳይ ቆም ብሎ እንዲመረምር ያደርገዋል ባይ ነኝ:: ሲጀመር ኢህአዲግ ራሱ በሙስና የተፈጠረ ነው፤ በእኛ ክልል ብትሄድ ኦህዴድ ወስጥ የገባ ወጣት ወይ በጥቅም ተደልሎ፣ወይ በአንድ ነገር ተታልሎ የተገኘ እንጂ ድርጅቱን ፈቅዶና ወዶ አባል የሆነ አንድ ሰው አታገኝም:: እኛ ጋር የሚመጡ ወጣቶች በሙሉ ኦሮሞ በመሆናቸው መብታቸውን በመጠየቃቸው እየተደበደቡ እየተሰቃዩ አብረናችሁ እንሁን ብለው ይጠይቁናል:: ቆይ እናጣራ ስንላቸው ‹‹መብቴ ነው፤ መዝግቡኝ ሰላማዊ ትግሉን እቀላቀላለሁ::›› ነው የሚሉት፤ ኦህዴድ ቤት አንድ ሰው በዚህ መንገድ የመጣ አታገኙም:: ሌሎች ድርጅቶችም ጋርም እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ያለ ነው የሚመስለኝ::

ት/ቤት አትመዘገቡም፣ ስራ አታገኝም፣ አትደራጅም እየተባለ አባል በሚሰበሰብበት ድርጅት ውስጥ እንዴት አዲስና የተሻለ ሰው ማግኘት ይቻላል? ስለ እዚህ አዲሱ ካቢኔ በአጠቃላይ የተለወጠ ቢመስልም ኢህአዴግ ባለበት የሚቀጥል ድርጅትና ቅድም እንደገለፅኩት ከህዝቡ ጋር ረጅም ርቀት ለመጓዝ በተገቢው መንገድ ራሱን ያላዘጋጀ ድርጅት መሆኑን በይፋ የሚያረጋግጥ ነው ብዬ አስባለሁ::

ሁላችንም እንደምናስበው ኢህአዴግ ነገሮችን ለመቀየርና እራሱን ለማስተካከልም ምቹ አጋጣሚ የተፈጠረለት በዚህ ወቅት ነበር:: ግን እጅግ በጣም አስገራሚ በሆነ መልኩ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንኳን ለማንሳት አልሞከረም:: የሚገርምህ ነገር እኛ ስንፈታ የቄሮዎች እንቅስቃሴ ቆሟል፤ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችም ሲለቀቁ ይሄ ነገር በግልፅ ታይቷል:: ህዝቡ የሚፈልገውን ካገኘ ደግሞ ወደ ብጥብጥ እንደማይገባ ግልፅ ነበር:: ከፀደቀ በኋላ አንዳችም ጊዜ አዋጅ ማፅደቁ ፈፅሞ አያስፈልግም ነበር፤ከሆነ በኋላም ሳይነሳ ባለበት መቀመጡ ኢህአዴግ ሁሌም አምባገነን ሆኖ መኖር እንደሚፈልግ ያመላከተ ድርጊት ነው::

ግዮን፡- አመሰግናለሁ::



# “የኦሮሞ ምሁራን የግዕዝ ፊደላትን እንዲጠቀሙ ጥሪ አቀርባለሁ”

## ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው

ከዓመታት የአሜሪካ ቆይታ በኋላ በተደረገልኝ ጥሪ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ አመራሁ:: ከቀናት በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመካሄድ ላይ ባለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አብዮት ውስጥ የራስዎ ሥፍራ እንዲኖራት ያደረገውን ለዓመታት የለፋሁበትን የምርመራ ውጤት ለህዝቡ ይፋ ለማድረግ በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል በተዘጋጀ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኘሁ::

የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ላይ ታች ይላሉ እኔም ኮምፒዩተሬን እና ፕሪንተሬን ይገኙ በሥፍራው በመገኘት ሁሉንም ዝግጁ አድርጌ የፕሮግራሙን መጀመር እየተጠባበቅኩ እያለ በድንገት ሆቴሉ መትረየስ ጠመንጃ ባነገቡ ወታደሮች ተወረረ:: በድንጋጤ ምን ተፈጠረ ብዬ አንዱን አስተባባሪ ጠየቅኩ ጓድ ፕሬዘዳንት በዝግጅት ላይ ለመገኘት እየመጡ ነው አለኝ:: ይሄን ጊዜ በአያሌ የአሜሪካ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ የመንግስቱ ኃይለማሪያም አገዛዝ በመቃወም በርካታ መጣጥፎችን እያዘጋጀሁ ለንባብ ማብቃቴ ትዝ አለኝ:: ይሄንን ድርጊቴ የመንግስቱ ደህንነቶች ደርሰውበት ከሆነ የምቀበለውን መከራ እያሰብኩኝ በስጋት ውስጥ ገባሁ::

በዝግጅቱ ላይ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በሙሉ ቦታ ቦታቸዉን ይዘዋል:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ኮሎኔል መንግስቱ በባልደረቦቻቸው ታጅበው ወደ አዳራሹ ገቡ:: ይሄን ጊዜ ምን ማድረግ አለብኝ እያልኩ ሳሰላስል ኮሎኔል መንግስቱ በቀጥታ ወደ እኔ በመምጣት እንኳን ለአገርህ አበቃህ ብለው ሞቅ ያለ ሠላምታ ሠጡኝና እውነት ነው የተባለው ሲሉ ጠየቁኝ:: አዎን የተከበሩ… አልኩና ኮምፒዩተሬ ፊት ቁጭ ብዬ የኮምፒዩተሬን ኪቦርድ ላይ ጣቶቼን እያፈራረቅኩ በመምታት “ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር!” የሚል መፈክር በመፃፍ ፅሁፉን እንዲያትም ፕሪንተሩን አዘዝኩ በሴኮንዶች ውስጥ መፈክሩ የተፃፈበት ወረቀት ወጣ ለፕሬዘዳንቱ አንስቼ ሰጠሁ::

መንግስቱ ፊታቸው በፈገግታ አበራ አድናቆት ተሞልተው ስለ ግኝቴና ወደፊት ምን ማድረግ እንዳሰብኩኝ ጠየቁኝ:: ምላሽ ሰጠኋቸው ይህንን የስራዬን ውጤት ለህዝብ እንዲደርስ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ትብብር እንዲደረግልኝ መመሪያ እንደሚሰጡ ገለፁልኝ:: የተባለው ትብብርና እገዛ ግን አልተደረገልኝም ከዚያ ይልቅ ከተለያዩ ወገኖች ዛቻና ማስፈራሪያ በተለያዩ መንገዶች ይደርሱብኝ ጀመር ይላሉ የመጀመሪያውን የአማርኛ ፊደላት በመቅረፅ ፕሮግራም በመፈልሠፍ የሚታወቁት ኢንጂነር ፍስሀ አጥላው::

በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዉ ዘርፍ የመጀመሪያውን የአማርኛ ሶፍት ዌር የፈለሠፉት ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው በካሊፎርኒያ የሐውት ፖካርድ ኩባንያ ማይክሮኦቨን ቴክኖሎጂ ኢኒጂነሪንግ ዲቪዥን ማናጀር ላለፍት አስራ አመስት ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ዲቨሎንመንት ኢንጅነሪንግ ሳይንቲትስት እና ዳሽን ኢንጂነሪንግ የተባለ ኩባንያ መስራችና ባለቤት ናቸው:: ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በኢኒጂነሪንግ የማስተርስ ዲግሪ አግኝተዋል:: በመቀጠልም ወደ አሜሪካ በማቅናት በኔብርስካ ዩኒቨርሲቲ በአፕላይድ ማቲማቲክስ የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል::

ገና በአስራ ሁለት ዓመታቸዉ በውስጣቸው በነበረው የሥነጽሑፍ ፍቅር አንድ ኖቬል ጽፈው አሳትመዋል:: በአስራ አምስት ዓመታቸው

ድራማ ጽፈው በዕውቁ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድን የድራማውን ጽሑፍ አይተው በሐገር ፍቅር ቲያትር ቤት እንዲታይ ማድረጋቸው ታዳጊውን ህፃን የፈጠራ ችሎታ በተመለከተ በወቅቱ የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ ላይ ሠፊ ዘገባ ታትሞ እንደነበር ወደኋላ በትዝታ መለስ ብለው ያስታውሱታል ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው::

## የፈጠራው መንሥዔ ምክንያት

ኢንጅነር ፍስሀ አጥላው ለተጨማሪ ከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካን ሲያቀኑ ውስጣቸው ሲንጣቸው የነበረው የሥነጽሑፍ ፍቅር ተሠጥኦቸው አብሯቸው ውቅያኖስ ባህር ተሻግሮ ነበር::

ይህንን ውስጣቸው የሚተራመሠውን የሥነጽሑፍ ፍላጎት ለማርካት መጻፍያ ታይፕ ራይተር አስፈለጋቸው ስለዚህም ከኢትዮጵያ የአማርኛ ታይፕራይተር ገዝተው እንዲላክላቸው ያደረጉት ሙከራ በወቅቱ በስልጣን ላይ የነበረው የደርግ መንግሥት ጥብቅ ቁጥጥር ምክንያት ሳይቻል ቀረ የሚሉት ፍስሀ አጥላው::

ፍላጎቱን ለማሳካት አልቪቲ እና ኦሎምፒያ የተባሉ ኩባንያዎች ጋራ በመፃፃፍ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ባላቸው የስራ ስምምነት ምክንያት ሊሸጡልኝ እንደማይችሉ አሳወቁኝ:: በዚህ ምክንያት የአማርኛ ፊደላት ፎንት ለመቅረፅና ኮምፒዩተራይዝድ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮጀክት ነድፌ መንቀሳቀስ ጀመርኩ ይላሉ::

ከ30 ዓመት በፊት በስልኮንቫሊ እምብርት ላይ ሆኖ የአማርኛ ታይፕራይተር ባለማግኘቴ የአማርኛ ፊደላትን ቀርፆ ለማዘጋጀት ሶፍትዌር ለመፈብረክ የጀመርኩት ሥራ አልጋ በአልጋ አልሆነም ብለው የሚያስታውሱት ፍስሀ ለዚህ ስራው በወር 380 ዶላር የኪራይ የአይቢኤም ኮምፒዩተር ዶትማትሪክስ ፕሪንተር ተከራየሁ ይላሉ::

ለአንድ ዓመት ያህል እጅግ ፈታኝ ውጣ ውረድ የሚጠይቅ ሥራ ከተሠራ በኋላ ህልሜ ዕውን ሆነና የአማርኛ ፊደላት ተቀርፀው ከኮምፒዩተሮች ጋር እንዲጣጣሙ የሚያደርገው የመጀመሪያው የአማርኛ ሶፍት ዌር ተፈለሠፈ::

ይህንን ግኝት በስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ በሚገኝ አዳራሽ በርካታ እንግዶች በታደሙበት ሥነሥርዓት ላይ ይፋ ሆነ:: በወቅቱ በአሜሪካ በስራ ጉብኝት ላይ የነበረ የኢትዮጵያ መንግስት ልዑካን ቡድን ተገኝቶ ነበር:: በግኝቱ የተደሰቱት የልዑካን ቡድኑ መሪ ኢንጂነር ፍስሀ አጥላውን ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ጥሪ አደረጉላቸው::

ግኝቱ በተመለከተም በአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል በመቅረብ ፍስሀ አጥላው ስለሶፍትዌሩ፤ የሶፍት ዌሩ መፈልሠፍና ለኢትዮጵያ ያለውን ፋይዳ በስፋት አብራሩ:: ይህንን ተከትሎ ነው ወደ አገር ቤት ተመልሰው ግኝታቸውን ኮሎኔል መንግስቱ በድንገት በታደሙበት ሥነሥርዓት ላይ ለኢትዮጵያዊያን ያስተዋወቁት::

ኢኒጂነር ፍስሀ አጥላው አገር ቤት በሒልተን ሆቴል የመጀመሪያውን የአማርኛ ሶፍት ዌር መፈብረክና ኮምፒዩተሩ ጽፎ ለኅትመት የሚያበቃውን ግኝት ካስተዋወቁ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ነበር በአገር ውስጥ ከየአቅጣጫው ማስፈራሪያና ዛቻ ይደርሳቸው ጀመረ:: የቅርብ ወዳጆቹና ዘመዶቹ በአስቸኳይ ወደ አሜሪካ እንዲመለስ በመምከር ለደኅንነቱ ያላቸውን ስጋት ገለፁለት:: ያን ጊዜ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣናት ከጥቂት ስዊድናዊያን ባለሙያዎች ጋር ሁለት ሚልየን ብር ተመድቦ "ኢትዮጲክ ኮምፒዩተር" የሚል ምስጢራዊ መጠሪያ የሰጡት ፕሮጀክት ትግበራ አደናቅፎናል ብለው በጠላትነት እንደፈረጁኝ ደረስኩበት በዚህም ምክንያት እቃዬን ሸክፌ ወደ አሜሪካ ተመለስኩ:: የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንም በሁለት ክፍል የሚተላለፍ ቃለምልልስ አድርጎልኝ ነበር:: ቃለምልልሱም እንዳይተላለፍ ተደረገ::

ወደ ካሊፎርኒያ ተመልሼ በዜክሮስ ኩባንያ ተቀጥሬ ከባልደረባዬና የረጅም ጊዜ ወዳጄ ከጆይ ቤከር ጋር በመቀናጀት የኮምፒዩተር ሶፍትዌሮች ሙሉዕ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያደርግ ደረጃ እንዲኖራቸው ዩኒኮድ የተባለ ኮምፒዮተራይዝድ ፕሮግራም በመቅረፅ "ኢትዮጲክ" የተባለው ስያሜ የያዘ ሶፍትዌር ፕሮግራም ማጎልበት ቻልን:: ግኝቴን ይበልጥ ለማዘመን የሚያስችሉ የማሻሻያ ተግባራት እያከናወንኩ እያለ የቮይስ ኦፍ አሜሪካ ሬድዮ ዜሮክስ የተባለውን ኩባንያን በሬድዮ ጣብያው የሚተላለፉ ቋንቋዎች መገልገያ የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች ሶፍትዌር እንዲሠራለት ከስምምነት ላይ ይደርሳል:: ሬድዮ ጣብያው እንዲሠራለት ከጠየቃቸው ቋንቋዎች የአማርኛ ቋንቋ መፃፍያ ሶፍትዌር ፕሮግራም አንዱ ነበር::

በዚህ ስራ ላይ እንደ አይ ቢ ኤም፣ ጎግል፣ ኢንስ ማይክሮሶፍት፣ አማዞን፣ የተውጣጡ የኮምፒዩተር ኢንጂነሮች ተካፋይ ነበሩ፡ እኔም በስራው ላይ የተሳተፍኩት እሠራበት የነበረው የሒዋት ፓካርድ የተባለ ኩባንያ እና ራሴ የመሠረትኩት ዳሽን ኢንጂነሪንግ ኩባንያን ወክዬ ነበር:: አሁንም ቢሆን ኢትዮጲክስ ሶፍትዌርን በማዘመን ረገድ ብዙዎች የየበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ እንደሆነ የሚናገሩት ኢንጂነር ፍስሀ አጥላው በያዝነው ዓመት የ2010 የኢትዮጲክ ሶፍትዌር በዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሶፍትዌር ወደ መሆን ተሸጋግሯል ይላሉ::

በዓለም ዓቀፍ ገበያ ላይ ያሉ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር አፕሊኬሽኖች 90 ፐርሰንቱን በኢትዮጲክስ ሶፍትዌር መገልገል የሚችልበት ደረጃ ላይ እንገኛለን:: ይህንን ስል በአማርኛ ቋንቋ ትርጓሜ በተለይ በጎግል ብሮውዘር እንዲሁም በአማርኛ የተጻፈ ኦፕቲካል ካራክተር ሪኮግኒሺን (COCR) በመተርጎም ኤዲት ማድረግ የሚያስችል አፕሊኬሽን እንዲኖረው ተደርጓል:: ይህ ማለት ብዙ ዕድሜ ጠገብ ስካን ተደርገው የተቀመጡ የፒ ዲኤፍ ዶክመንቶችን በመቀየር ልክ እንደ አዲስ ጽሑፍ ኤዲት ማድረግ ያስችላል:: ኮምፒዩተራችሁ ወይንም ሞባይላችሁ ላይ የተጫነ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍትን ወደ ድምፅ በመቀየር የሚያነብ ፕሮግራም አለው:: በኮምፒዩተር ወይንም በስልኩ በድምጽ የተናገራችሁት ወደ ጽሑፍ በመቀየር ሊያስነብብ የሚችል ፕሮግራም ያሟላ ነው::

ሌሎች የዘመኑ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚያስችል የተሟላ ሶፍትዌር ሆኖ አገልግሎት ላይ ውሏል ይላሉ ኢኒጂነር ፍስሀ አጥላው:: በተጨማሪም ፕሮግራሙና ሶፍትዌሩ ለሞደርን ግራፊክስ ዲዛይን፤ ለአኒሜሽን እንዲሁም ለቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መገልገያ የሆነ የዘመኑ አፕሊኬሺኖች መጠቀም በሚያስችል ቁመና ላይ እንደሚገኝ በመግለፅ የዛሬ ሠላሳ ዓመት በእሱ ፋናወጊነት የተጀመረውን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አብዮት ውስጥ ኢትዮጵያ በአማርኛ ቋንቋ ተጠቃሚ የመሆንዋ ጅማሮ ዛሬ የደረሰችበትን ደረጃን በኩራት ያወሳሉ::

አሁን በርካታ ወጣት ኢትዮጵያዊያን እንደ ሜታኦፔዝ፣ ኢትዮ ክላውድ፣ አገርኛ የመሳሰሉ አፕሊኬሽኖችን የሚያጎለብቱ ለአገልግሎት የሚውሉ ፈጣን እጅግ ድንቅ ተሰጥኦ ያላቸው ወገኖች በዓለምአቀፍ ደረጃ በሚደረገው ውድድር ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ በመሆኑ መጪው ጊዜን በተስፋ ነው የምጠብቀው ብለዋል ፍስሀ አጥላው::

ኢንጂነር ፍሰሐ አጥላው ለበርካታ ዓመታት የአፋን ኦሮሞ ቋንቋን በባዕዱ በላቲን ፊደላት ከመጠቀም ይልቅ በኢትዮጵያ ፊደላትና ሆህያት ለምን አይጠቀሙም የሚል የውይይት ሃሳብን በተመለከተ ግላዊ አስተያየታቸውን ሠጥተዋል::

ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት የተወሠኑ የኦሮሞ ልሂቃን አፋን ኦሮሞን በኮምፒዩተራይዝ ሲስተም ለመጠቀም በላቲን ፋይል መጠቀም ይገባናል ብለው የወሠኑት ውሳኔ እረዳለሁ:: ግን አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘና ደረጃውን የጠበቀ የኢትዮጲክ ሶፍትዌር የላቲን ፊደል ለመጠቀም አስገዳጅ የነበሩ ክፍተቶችን ያሟላ ሆኖ በመፈብረኩ በጎግል ትራንስሌት ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያስችላል:: ስለዚህ የኦሮም ምሁራን ይህንን ትልቅ የበለፀገ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋን ከላቲን ፊደላት ከመጠቀም ይልቅ በግዕዝ ሆሄያት መጠቀም እንዲጀምሩ ጥሪዬን አቀርባለሁ::

የኦሮሚፋን ቋንቋ በቁቤ በላቲን ፊደላት መጠቀም በመተው በግዕዝ ፊደላት ያለዕንከን መጠቀም እየቻሉ እንደ ፖለቲካ ጉዳይ... ማየት የለባቸውም:: ይህንን የሚያደርጉት ለቀላል ቴክኒካል ምክንያት ነው:: ይኸውም ልክ እንደ አድዋ ድል ሁሉ የኢትዮጲክ ፊደላት የሁላችንም የኢትዮጵያዊያን ሀብት ስለሆነ ነው::

በኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ ዘርፍ በርካታ ተሥፋ የሚጣልባቸው ወጣት ኢንጂነሮች የኢትዮጲክስ ሶፍትዌር ለተለያዩ የቴክኖሎጂ ፕላትፎርሞች መጠቀም እንዲያስችል በማድረግ እያሳዩት ያለ ጥረት እና ያስመዘገቡት ውጤት መጪው ጊዜን የበለፀገች የታፈረች ኢትዮጵያን ለመገንባት ያለውን ተሥፋ ዕውን እንደሚያደርጉ አመላካች ነው::

አሜሪካን አገር በንብራስካ ግዛት በሚገኘዉ የንብራስካ ግዛት ዩኒቨርስቲ (University Of Nebraska) ዉስጥ በሒሳብ እና በምህንድስና (Mathematics and Engineering) በማስተርስ ዲግሪ ተመርቀዉ የመጀመሪያ ሥራቸዉን ሒውለት ፓካርድ (Hewlett-Packard) ወይም በተለምዶኣዊ HP እየተባለ በሚጠራዉ የኮምፒዩተር ካምፓኒ ዉስጥ የምኅንድስና ሳይንቲስት (Engineering Scientist) ተቀጥረዉ ይሠሩ የነበሩ ናቸዉ::

እኚህ ኢትዬድያዊ ሳይንቲስት የኢትዬድያን ፊደላትን በመጠቀም እራሳቸዉ በመሰረቱት "ዳሽን ኢንጅነሪንግ ካምፓኒ" አማካኝነት የ "ዳሽን" የኢትዬድያ ቋንቋዎች የኮምፒዉተር ፕሮግራምን በዶስ (DOS) በመጻፍ (Coding) አማርኛ ኮምፕዩተር ላይ በወርድ ፕሮሰሰር ዓይነት ሆኖ እንዲሠራ በእኛ ዘመን አቆጣጠር በ1977 ዓ.ም. ፈጥረው የሠሩት አቶ ፍስሀ አጥላው ናቸው:: አቶ ፍስሀ በርከት ያሉ ጥንታዊ የአማርኛ መጽሐፍን በመስብስብና ማንበብ ለሚፈልግ ሁሉ ለጋሽም እንደሆኑ ተግባራቸዉ ይመሰክራል:: በተለይም Good-amharicbooks.comየጐበኘ ሰዉ የአቶ ፍሰሀን የመጽሐፍ በረከቶች ያያል::

ይህ ዘገባን ለማጠናከር የተለያዩ ድረ ገፆችን በዋቢነት በምንጭነት ተጠቅመዋል:: ስለኢትዮጵክ ሶፍትዌር የፈበረከው የግኝቱ ባለቤት የሆነውን ፍስሀ አጥላውን ማግኘት የሚፈልግ fesseha Atlaw - fessh@optmax.com ብሎ ማግኘት ይችላል::

# ቃኘው ሻለቃ በኮሪያ

## አንዱ ለሁሉም ሁሉም ለአንዱ



ብሩክ መኮንን

ለክ በዛሬዋ ቀን በቀሩት በፊት በብዙ ሺህ የሚቆጠር የአዲስ አበባ ነዋሪ ህዝብ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ዲፕሎማቶች የኢትዮጵያ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ በመስቀል አደባባይ በመገኘት ወደኮሪያ ልሳነ ምድር የሰላም አስከባሪነት ግዳጅ ለመወጣት የዘመተውን የቃኘው ሻለቀ አሰነባበት ተደርጎ ነበር::

ከ60 አመት በፊት ልክ በዛሬዋ ቀን እልም አለ ባቡረ ወጣት ይዞ በሙሉ የተሰነውን ተወዳጅ ዜማን ያቀነቀነው ካሳ ተሰማ ተስፋዬ ሳህሉን ያካተተው ዘማቹ የቃኘው ሻለቃ ጦር ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍሮ ጅቡ ከተማ በሁለት ቀናት ከቆዩ በኂላ ደኔራል ማክራይ በተባለ የአሜሪካ ጦር መጓጓዣ መርከብ ተሳፍረው ወደኮሪያ ለመረድረስ የ21 ቀን የባህር ላይ ጉዞን ጀመሩ::

አፄ ሃይለ ስላሴ የአባታቸው የራስ መኮንን የፈረስ ስም ቃኘው ብለው የሰየሙት ከንጉስ ነገስቱ የክብር ዘበኛ ጦር የተውጣጣ ሻለቃ ጦርን የዘመቻ አርማ በሰጡበትና በድል ተመለሱ ብለው ባሰናበቱበት የስንብት ስነስርአት ላይ “ሩቅ በሆነ ሃገር እንድትዋጉ ስትላኩ የምትታገሉት ለነፃነትና ለራስ መግገዛት ብቻ ሳይሆን በህብረት የአለም ሰላምና ፀጥታ የሚረጋገጥበትን የኮሌክቲቨ ሴኩሪቲ የተባለውን ኢትዮጵያ ለዘላለም የምትተማመንበትን ተግባራዊ እንዲሆን የምትሰራበት መርህን ለማክበርና ለማረጋገጥ ነው” ብለው ነበር ተናግርው የነበሩት::

የኮሪያ ጦርነት መንስኤ

ሰኔ 25 ቀን 1950 እኤአ 60.000 የኮሚኒስት ወታደሮች 38ኛውን ፖራኦል ተሻግረው በከሪያ ላይ ወረራ ፈፀሙ:: ወረራው በተፈፀመ በ24 ሰአት ውስጥ የአሜሪካ የሩቅ ምስራቅ ወታደራዊእዝ ኤፍ 51 ተዋጊ ጀት አውሮፕላኖች ወደኮሪያ በመላክ ወረራውም ለመቀልበስ አፋጣኝ እርዳታ መስጠት የጀመረው::

ሰኔ 26 ቀፀ 1950 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምር ቤት ወረራውን ለመቋቋም ለማህበሩ አባል አገራት ሁሉ አፋጣኝ ድጋእርዳታ እንዲሰጡ ጥሪ አደረገ::

የአሜሪካው ፕሬዘዳንት ትኮማን የአሜሪካፀ አየር ሃይልና ባህር ሃይል የኮሚኒስቶችን ጥቃት ለማስቆም እንዲንቀሳቀሱ አዘዙ ከአምስት ቀናት በኂላ የመጀመሪያው የአሜሪካ ጦር ደቡብ ኮሪያ ደረሰ::

ሐምሌ 8 ቀን ጄኔራል ዳግላስ ማክአርተር በኮሪያ ዘመቻ የሚለካው የተባበሩት መንግስታት ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሆነው ተሾሙ:: በቀጣዮቹ ሳምንታትና ወራት መረዳዳትና የጋራ ቃል ኪዳንን የጋራ ደህንነት መርህን ለማስጠበቅ የወሰኑ የተባበሩት መንግስታት አባል አገራትን ጦራቸውን ወደ ኮሪይ ልጣነ ምድር መላክ ጀመሩ::

ቀዳማዊ ሃይለስላሴ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ብርጋዴር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊን በመጥራት ወደ ኮሪያ የሰላም አስከባሪ ጦረ ለመላክ መወሰናቸን ለዚሁ ግዳጅ ዝግጁ የሚሆን አንድ ሻለቃ ጦር እንዲያደራጁ አዘዙ::

በወራት ውስጥ አንድ ሻለቃ ከክብር ዘበኛ ጦር የተውጣጣ ጦር ለግዳጅ ዝግጁ ሆነ:: መጋቢት 25 ቀን 1951 የመጀመሪያው በኮሎኔል ከበደ ገብሬ የሚመራው ቅድመ ሁኔታ የሚያመቻች የኢትዮጵያ ጦር አባላትን የያዘ ቡድንወደኮሪያ አቀና::

ዋናው ዘመቻ ቃኘው ሻለቃ በሌትና ኮሎኔል ክፍሌ እርገቱ ዋና አዛዥነት ከአደስ አበባ ባቡር ተሳፍቶ ወደ ጅቡቲ አመራ ከጅቡቲም በመርከብ ተጉዞ ከሶሰት ሳምንት አድካሚ ጉዞ በኂላ ፑሳን ወደብ ደረሱ::

በፑሳን ወደብ የደቡቡ ኮሪያው ፕሬዘዳንት ጨምሮ ከፍተኛየአሜሪካ ጦር አዛገሮች የከተማይቱ ህዝብ ደማቅ የሆነ አቀባበል ተደረገለት::

በጊዜው ዘጠኝ ማይል ርቀት ተጉዘው ኮሪያ የደረሱ የቃኘው ሻለቃ ተዋጊዎችን በተመለከተ የዘገቡ መገናኛ ብዙሃን ተክለሰውነታቸው በስፖርት የዳበረ የፊታቸው ቆዳቸው ፀሃይ ያቃጠለው መዳብ የመሰሉ… ጠይም አይኖቻቸው ትኩር ብለው ሲያዩውስጥን መርመረው የሚያዩ የሚመስሉ ንቁ እጅግ የተረጋጉ ቆፍጣና ወታደሮች በአሜሪካ 7ኛው እግረኛ ባታሊዮን ስር ተዋቅረው በኮሪያ ምድር ሰላምና ፀጥታን በማስከበር ግዳጅን መወጣት ጀመሩ ይላል::

በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ በሚካሄዱ የሰላም ማስከበር ግዳጆች ላይ ሰራዊትዋን በማሰማራት ግንባር ቀደሞ ተርታ የተሰለፈችው ኢትዮጵያ ለአለምሰላምና የጋራ ደህንነት መርሆች መከበር የበኩልዋን ድርሻ መውጣት የጀመረችው በኮሪያ ልሳነ ምድር ከዛሬ ስድስት አስርት አመታት በፊት በዚህ ሰሞን ነበር::

በኮሪያ ልሳነ ምደር ለአምስት አመታት በግዳጅ ላይ የቆየው የኢትዮጵያ ጦር በቃኘው ሻለቃ በሁለቱ አገሮች የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ውስጥ በደም የተሳሰረ ዝምድና እንዲናኖር በማድረግ ኢትዮጵያ በአለም አቀፋዊ ወንድማማችነት መርህ በባህልም ሆነ በታሪክ በፍፁም ለማይታዋወቁ ህዝቦች ነፃነት ሉአላዊነት አጥንታቸውን በመከስከስ ደማቸውን በማፍሰስ ጉልህ ታሪክ ፅፈዋል::

ከ0 በታች 30 ዲግሪ ሴንትግሬድ ድረስ አየሩ በሚቀዘቅዝበት ወንዞች ሁሉ ወደ ግግር በረዶነት ተቀይረው የትኛውም ካባድ መኪናን ከነጓዙ የማርመሰመስባቸው አውራጎዳናነት በሚቀየሩበት ከላይቤሪያ እየጋለበ የሚመጣው ጠንካን በረዶ ያዘለ ንፋስ በሚጋረፉበት ቆፋናም የኮሪይ የክረምት ወራት የቃኘው ሻለቃ አባላት የሆኑ ኢትዮጵያዊን የተሰጣቸውን ግዳጅ በብቃተ መወጣታቸውን ከጦርነ በኂላ ስለጦርነቱ የተፃፉ የጦር አዛዥች ባዬ ግራፊያቸውን ያሳረፉባቸ መፅሃፍት ታላቁንና አኩሪውን የኢትዮትያዊያን የተጋድሎ ታሪከ አስነብቧል::

ከግንቦት 7 ቀን 1951 እስከ መጋቢት 29 ቀን 1952 በሌተና ኮሎኔል ተሾመ እርገቱ ዋና አዛዥነት በኮሪያ ግዳጁን በብቃት የተወጣውና ከመጋቢት 29 ቀን 1952 እስከ ሚያዝያ 1953 በሌተና ኮሎኔል አስፋው አንዳርጌ የሚታዘዘው ሁለተኛው ቃኘው ሻለቃ ግዳጁን ጨርሶ በምትኩ ከሚያዝያ 5 ቀን 1953 እስከ ሐምሌ 10 ቀን 1954 በሌተና ኮሎኔል ወልደዮሃንስ ሽታ የተመራው ሶስተኛው የቃኘው ሻለቃ ግዳጁን በብቃት ተወጥቶ ሲያጠናቅቅ ለቀጣይ አንድ አመት ማለትም ከሐምሌ 10 ቀን 1954 እስከ ሐምሌ 9/1955 በሌተና ኮሎነል አስፋ ሃይለማሪያም በመቀጠልም አምስተኛው የኢትዮጵይ ሰላም አስከባሪ ጦር በሻምበል ዮሃንስ ምስክር አዛዥነት በኮሪያ ለአመታት ቆይታ አድርጎ በደሙ ደማቅ ታሪክ ፅፏል::

ከግንቦት 1951 እስከ ህዳር 1954 ድረስ በኮሪያልሳነ ምድር የተሰጠውን የሰላም ማስከበር ግዳጅ ለመወጣት 6073 የንጉሰ ነገስቱ የክብር ዘበኛ ምርጥ ኢትዮጵያዊያን ወታደሮች ዘምተዋል::

የኢትዮጵያው ቃኘው ሻለቃ ጦር በቆይታው ለ253 ውጊያዎች ላይ የተከፈለ ሲሆን አንድ መቶ ሃያ ወታደሮች የህይወት መስዋዕትነት ሲከፍሉ 536 ወታደሮች ከባድ ቀላል የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል::

“አንዱ ለሁሉም ሁሉም ለአንዱ” የሚል መርህን የግዳጅና የተልዕኮው ቁልፍ አላማ አድርጎ የዘመተው ቃኘው ሻለቃ በሰላም ማስከበር ግዳጅ ላይ የተሰማው የተለያዩ አገር ወታደሮች ውስጥ አንድም አባሉ ያልተማረከበት የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ አባላቱ አስክሬን አንድም ጊዜ በጠላት ወረዳ ትቶ ያላፈገፈገ ወስዶ በክብር የቀበረ አኩሪ ታሪክ ያፃፉ ጀግናና በአለምአቀፍ ደረጃ ሁልጊዜም ሲታወስ የሚኖር ገድል የፃፈ ታሪክ ሰሪ ሰራዊት ነው::

በኮሪያ ወታደራዊ ግዳጅ ከመወጣት በአለፈም በዛሬውየደቡብ ኮሪያ ዋና ከተማ በሲኦል ለሚገኝ ወላጆቻቸውን በጦርነቱ ላጡ ህፃናት ለመርዳት ባህዋ የህፀናት ማሳደጊያ ድርጅት ከሰራዊቱ የምግብ ራሽን ላይ በፈቃደኝነት እየቀነሰ ገንከብ እያዋጣ ለወራት እርዳታና ድጋፍ አድርጓል::

በኮሪያ የዘመተው ቃኘው ሻለቃ በፖርካችን ሔል ጦርነት የፈፀመው ጀግንነት በወዳጅም ሆነ በጠላት የሚዘከር በሁለቱ ህዝቦች ወዳጅነት ትብብር ላይ ደማቅ ታሪክ ፅፏል::

ለበርካታ አስር አመታት ደቡብ ኮሪያውያን ኢትዮጵያን ወታደሮች የከፈሉት መስዋዕትነት በመርዳት የቃኘው ሻለቃ አባላትን ለመርዳት ፈርጀ ብዙ ድጋፍና እግዛ እያደረጉ ነው የደቡብ ኮሪያ የኢትዮጵያ ህዝቦች በደም የተሳሰረ ታሪክ እነሆ ከስድሳ አምስት አመት በኂላ እንዲህ በወፍ በረር ለመዳሰስ የሞከርኩበትን ታሪክ ዳሰሳ እዚህ ላይ አበቃ::

Flintstone Homes for you®

Leading by example




Call: 8188
Click: www.flintstonehomes.com
Addis Ababa,Ethiopia